ጠንቅ ሰይፎች
ከመርማሪ መሠረት

ዶሬሽ ፕሬሽስ

Foundation For Righteous Living Copyright 1993
Derek Prince Ministries - International

ለዚህ መጽሐፍ ያለምትን አስተያየት
የማነብርሃን እንዳለ
የመ. ሣ. ቁ. 21980
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ብለው ይፃፉ

E-mail ora. international @ telecom. net. et

«ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ
መሠረት ሊመሠረት
አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ
ክርስቶስ ነው።»

1ኛ ቆሮንቶስ 3:11

አጠቃላይ ማውጫ

ገጽ

ክፍል I የእምነት መሠረት . . . 18

ክፍል II ንስሐ መግባትና ማመን . . 86

ክፍል III የአዲስ ኪዳን ጥምቀቶች . . 149

ክፍል IV የጳንጠቆስጤ ዓላማዎች . . 243

ክፍል IV እጆችን መጫን . . . 321

ክፍል VI የሙታን ትንሣዔ . . . 347

ክፍል VII ዘለዓለማዊ ፍርድ . . . 401

ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ 13

ስለፀሐፊው 15

የመጽሐፉ አቀነባበርና ጠቀሜታዎቹ . . 17

ክፍል I: የእምነት መሠረት

የክፍል I መግቢያ ስለመጽሐፍ ቅዱስ . . 19

ምዕራፍ 1: የክርስቲያኖች እምነት መሠረት . 21

- ክርስቶስ የማዕዘን ዓለት
- ፊት ለፊት መቋቋም
- መንፈሳዊ መገለጥ
- እምነትን ማወጅ
- ሐቁን መናዘዝ

ምዕራፍ 2: በመሠረቱ ላይ መገንባት. . . 30

- መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት መሠረት
- የደቀ መዝሙርነት ማስመስከሪያ

- ፍቅርና ፈተናው
- የመገለጥ ዓይነቶች

ምዕራፍ 3: የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን . . 38

- መጽሐፍ ቅዱስ በጽሑፍ የሰፈረ የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ስለመሆኑ
- ዘለዓለማዊና ፍጹልጣን ያለው ስለመሆኑ እርስ
- በእርሱ የማይቃረን ምሉዕ እና ብቁ ስለመሆኑ

ምዕራፍ 4: የእግዚአብሔር ቃል አሠራር ቅደም ተከተሎች 46

- ለቃሉ የሚኖረን ምላሽ ወሳኝነት
- እምነት
- አዲስ «ዳግም» ልደት
- መንፈሳዊ ምግብ

ምዕራፍ 5: የእግዚአብሔር ቃል የሚያቀዳጃቸው አካላዊና መንፈሳዊ ተሐድሶዎች . 54

- ሥጋዊ ፈውስ
- እአምሮአዊ አብርሖት

ምዕራፍ 6: የእግዚአብሔር ቃል ድል አድራጊነት . . 63

- ድል በኃጢአት ላይ
- ድል በሰይጣን ላይ

ምዕራፍ 7: የእግዚአብሔር ቃል የማንጻት ኃይል . . 71

- ከኃጢአት መንጻት
- ቅድስና

ምዕራፍ 8: የእግዚአብሔር ቃል ገላጭነት . . 78
- መስታወታችን ነው
- ፈራጃችን ነው

ክፍል II: ንስሐ መግባትና ማመን

የክፍል II: መግቢያ መሠረታዊ አስተምህሮዎች . . . 87

ምዕራፍ 9: ንስሐ 89

- ከግሪክና ከዕብራይስጥ ምንጮች አንጻር ኃጢአተኛው እግዚአብሔርን ሊያገኝ ሊያደርግ የሚገባው
- ንስሐ ከጸጸት የተለየ ስለመሆኑ ወደ እውነተኛ እምነት የሚያመራው ብቸኛ መንገድ

ምዕራፍ 10: የእምነት ባህርያት 96

- ከምኞትና ከተስፋ የተለየ ስለመሆኑ
- በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ ስለመመስረቱ
- ንስሐ በመግባት ስለመገለጹ

ምዕራፍ 11: የእምነት ልዩ ገጽታዎች. . . . 104

- ለጽድቅ ሕይወት ብቸኛው መሠረት
- የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳናት ስለማቀዳጀቱ

ምዕራፍ 12: እምነትና ለደህንነት 112

- የአዲስ ኪዳን አራቱ አውነታዎች
- ለትዕዛዛቱ ስለመገዛት

ምዕራፍ 13: እምነትና ምግባር 119

- ደህንነት በእምነት ብቻ ስለመሆኑ
- የሕያው እምነትና የሞተ እምነት ንፅፅር

ምዕራፍ 14: ሕግና ጸጋ 127
- ወጥ የሆነው የሙሴ የሕግ ሥርዓት
- ክርስቲያኖች ከሕግ በታች አይደሉም

ምዕራፍ 15: ሕጉ የተሰጠበት ዓላማ 135

- ኃጢአትን ለማመልከት
- የለውን ደካማነትና አራሱን ለማዳን አለመቻሉን
- ለማሳየት
- ስለክርስቶስ መምጣት ለመተንበይ
- እሥራኤልን ለመጠበቅ
- ሕጉ በክርስቶስ መምጣት ስለመፈጸሙ

ምዕራፍ 16: እውነተኛው ጽድቅ 142

- ሁለቱ ታላላቅ ትዕዛዛት
- ፍቅር - የሕግ ሁሉ ፍጻሜ
- የአዲስ ኪዳን የመታዘዝ አምሳያ

ክፍል III: የአዲስ ኪዳን ጥምቀቶች

ምዕራፍ 17: «ማጥመቅ» ስለሚለው ቃል . . . 150

- የቃሉ ሥር መሠረትና ትርጉሙ
- ታሪካዊ ገጽታው
- አራቱ የጥምቀት ዓይነቶች

ምዕራፍ 18: በዮሐንስና በክርስትና ጥምቀቶች መካከል ያለው ልዩነት 157

- የዮሐንስ ጥምቀት - ኃጢአትን መናዘዝና
- ንስሐ መግባት
- የክርስትና ጥምቀት-ጽድቅን ሁሉ መፈጸም

ምዕራፍ 19: ለክርስትና ጥምቀት ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎች 163

- ንስሐ መግባት
- እምነት
- ንጹሕ ኅሊና
- ደቀመዛሙርትነት
- ስለ ሕፃናት ጥምቀት
- መሠረታዊ ትምህርቶች

ምዕራፍ 20: የክርስትና ጥምቀትና መንፈሳዊ ዕሴቶቹ. . 172

- የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገለጽባቸው መነሣሣት
- ክክርስቶስ ጋር መሰቀልና መነሣት
- ከሞት በኋላ ትንሣዔ

ምዕራፍ 21: በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ . . . 181

- ለባት የአዲስ ኪዳን ማመሳከሪያዎች
- ከላይ የሚመጣ ጥምቀት
- ገሃዳዊ ምልክቶቹ

ምዕራፍ 22: መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበል . . . 190

የሐዋርያት አርአያነት
በመንፈስ ቅዱስ መሞላት
የኢየሱስ ትምህርቶች

ምዕራፍ 23: በልሣናት መናገር ለሁሉም ይቻላልን? . . 199

- በልሣናት መናገር ስጦታዎች
- የመንፈስ ፍሬ ማረጋገጫቸው ነው?

ምዕራፍ 24: የሚያስከትለው አካላዊና መንፈሣዊ ተጽእኖ. 207

- ስሜታዊ ለውጦች
- አካላዊ ለውጦች
- ሦስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች

ምዕራፍ 25: የመንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳን . . . 215

- በእያንዳንዱ አማኝ ላይ ለዘለዓለም ስለማደሩ
- የእግዚአብሔር አብ ቃል ኪዳን

- በክርስቶስ መዋጀት የተቀዳጀነው ሰማያዊ ማጎተም
- ሰማያዊ ማጎተም

ምዕራፍ 26: መንፈስ ቅዱሱን ለመቀበል የሚያስችሉ ሁኔታዎች. 223

- በእምነት ጸጋን በመቀዳጀት
- ስድስቱ የእምነት ደረጃዎች
  - እምነትን ጥምቀት
  - መጠማት
  - መጠየቅ
  - መጠጣት
  - ራስን ማስገዛት

ምዕራፍ 27: ለአዲስ ኪዳን ደህንነት የብሉይ ኪዳን አርኣያዎች 231

- የብሉይ ኪዳን አርያያዎች
- ደህንነት በደም ስለመገኘቱ
- ሁለት ጥምቀቶች
- የደመና ውስጥ ጥምቀት
- በባሕር ውስጥ ጥምቀት
- የደህንነት ተምሳሊነት
- መና ከሠማይ የወረደ
- ከድንጋይ ሥር የፈሰቀ ምንጭ

ክፍል IV: ዘመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ዓላማዎች

ምዕራፍ 28: መንደርደሪና ማስጠንቀቂያ . . . 244

- መንፈስ ቅዱስ ፈላጭ ቆራጭ አይደለም
- በእግዚአብሔር ስጦታዎች በሙሉነት መጠቀም
- አዲስ ዓይነት መንፈሳዊ ግምት

ንዑስ ክፍል ሀ: በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው አማኝ

ምዕራፍ 29: ኃይልና ክብር 253

- የመመስከር ኃይል
- ክርስቶስን ማክበር

ምዕራፍ 30: በመንፈሳዊ ዓለም ደረጃ . . . 260

- ወደ መንፈሣዊው ዓለም መግቢያ በር
- በመንፈስ የተሞላ ጸሎት
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጦች

ምዕራፍ 31: የማያቋርጥ ምሪትና የተትረፈረፈ ሕይወት. . 268

- ዕለታዊ ምሪት
- ሙሉዕነትን የተቀዳጀ ሕይወት

ምዕራፍ 32: በመለኮታዊ ፍቅር መጥለቅለቅ . . 276

- የእግዚአብሔር ፍቅር ባህርይ
- ከምንም ነገር ፍቅር ይበልጣል

ንዑስ ክፍል ለ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ጉባዔ

ምዕራፍ 33: የተገታ ነፃነት 284

- በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር
- ለእግዚአብሔር ባሪያዎች ሳይሆን ልጆቹ ነን
- ጊዜና ወቅት

ምዕራፍ 34: የምዕመናን ሙሉ ተሳትፎ . . . 292

- በመቅረዝ ላይ የተቀመጠውን መብራት
- መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ

ንዑስ ክፍል ሐ: በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ሰባኪ

ምዕራፍ 35 ዘላለማዊነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ማተኮር 302

- ኃጢአት፣ ጽድቅና ፍርድ
- መንፈሳዊውን ሰይፍ መታጠቅ

ምዕራፍ 36: መንፈሳዊ ምስክርነት 312

- በተዓምራት የተደገፈ ምስክርነት
- መንፈሳዊ መገለጥ በተዓምራት ስለመደገፉ

ክፍል IV: እጆችን መጫን

ምዕራፍ 37: በረከትን፣ ሥልጣንና ፈውስን ማስተላለፍ. . 322

- ሦስት የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች
- ሁለት ፈውስን የተመለከቱ የአዲስ ኪዳን ሕግጋት
- ፈውስን የማግኛ መንገድ

ምዕራፍ 38: መንፈስ ቅዱስና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች. 331

- መንፈስ ቅዱስን ማገልገል
- መንፈሳዊ ስጦታዎችን ማጋራት
- የጢሞቴዎስ አርአያነት

ምዕራፍ 39: አገልጋዮችን ማሠማራት . . . 339

- የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን
- የጳውሎስና የባርናባስ መላክ
- ዲያቆናትና ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ

ክፍል VI የሙታን ትንሣዔ

ምዕራፍ 40: ስለ መጨረሻው ዘመን . . . 349

- ዘለዓለማዊነት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት
- ሁለቱ ፍርዶች

ምዕራፍ 41: ከሞት በኋላ 354

- ሦስቱ የሰው ባሀርያት
- መንፈስና ሥጋ ስለመለየታቸው
- ጻድቃንና ኃጥአን ስለመለየታቸው

ምዕራፍ 42: ክርስቶስ - አርአያችንና መተማመኛችን. . 359

- በሞትና በትንሣዔ መካከል
- የክርስቲያን ሞትና ዕጣ ፈንታው
- የትንሣዔ አካልና የምድራዊ አካል ተመሳሳይ

ምዕራፍ 43: ትንሣዔ - በብሉይ ኪዳን . . . 365

- በመዝሙረ ዳዊት፣በዘፍጥረት፣በመጽሐፈ ኢዮብ
- በትንቢተ ኢሳይያስ፣በትንቢተ ዳንኤል፣ በትንቢተ ሆሴዕ
- አማኞች በክርስቶስ ትንሣዔ ስለመታቀፋቸው

ምዕራፍ 44: ክርስቶስ አርኣያችን 373

- የትንሣዔ ሦስቱ ተከታታይ ገጽታዎች
- የበኩርነት መለያው

ምዕራፍ 45: የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና አማኞች . . 381

- የእውነተኛ አማኞች መለያዎች፣
- የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አምስት ምክንያቶች
- የአማኞች መነጠቅና ትንሣዔ
- ምስክሮችና ሰማዕታት

ምዕራፍ 46: የመጨረሻው ዘመን 388

- በሺህ ዓመቱ መንግሥት ማብቂያ ላይ
- የመጨረሻው ትንሣዔ
- ሞትና ሲያል ስብዕና ያላቸው ስለመሆኑ

ምዕራፍ 47: የአሁኑ ሥጋችን ይለወጥ ይሆን . . 394

- የአህል ዘር ምሳሌነት
- የትንሣዔ ልዩ ጢቃሜታ

ክፍል VII: ዘለዓለማዊ ፍርድ

ምዕራፍ 48: የሁሉም ዳኛ እግዚአብሔር . . . 403

- እግዚአብሔር ይቅር ባይ አምላክ ነው
- እግዚአብሔር አብ፤እግዚአብሔር ወልድና ቃል
- ቃሉ የሚፈርድባቸው አራት ሁኔታዎች

ምዕራፍ 49: የእግዚአብሔር ፍርድ በታሪክ ውስጥ. . 412

- የታሪካዊና የዘለዓለማዊ ፍርዶች ንፅፅር
- የታሪካዊ ፍርድ ምሳሌዎች

ምዕራፍ 50: የክርስቶስ የፍርድ መንበር . . . 419

- በቅድሚያ ክርስቲያኖች ለፍርድ ይቀርባሉ
- የሚቀርቡት ለሽልማት ይሆናል
- በእሳት መፈተን

ምዕራፍ 51: የክርስቶስ የፍርድ ወንበር . . . 427

- የክርስቲያናዊ አገልግሎቶች መመዘኛ
- መላእክት ኃጢአንን ያስወግዳሉ

ምዕራፍ 52: የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ፍርዶች . . 435

- በታላቁ የመከራ ዘመን የእስራኤል ፍርድ
- የአሕዛብ መንግሥታት ፍርድ
- ታላቁ ነጭ ዙፋን

መ ግ ቢ ያ

ያለፉትን ሃምሳ ዓመታት ያሳለፍኳቸው ከተለያዩ ብሔሮችና አብያተ ክርስቲያናት ለተውጣጡ እልፍ አእላፋት ክርስቲያኖች ተገቢውን መንፈሣዊ ትምህርት በመስጠት፣ አስፈላጊውን ምክር በመለገስና በመጸለይ ነበር። ታዲያ ልክ ከተለያየ ማኅበረሰብና ታሪካዊ ዳራ የተውጣጡ እንደመሆናቸው መጠን የችግራቸው ውስብስብነትም በዚያ ልክ ነበር። ያም ሆኖ ግን በሁሉም ዘንድ የሚንጸባረቅ አንድ ተመሳሳይ ድክመት ነበር። ያም ድክመት ጤናማ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመምራት ያለመቻላቸው ጉዳይ ነው።

ምናልባትም የእነዚህን መሰሎች ወንድሞችና እህቶች ዓይነተኛ ችግርና ድክመት ቀለል ባለ መልኩ ለማቅረብ ለቤት መሥሪያ የሚውል ባዶ መሬት በተመሩ ሰዎች መስለን እንመልከት። አንድ አዲስ ቤት የመገንባት ዕቅድ ያለው ሰው አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ቁሳቁስ ሁሉ ካገኘበት እንደሚያሰባስብ እነዚህም ክርስቲያኖች ከያሉበት ቤተክርስቲያን ያዳመጡትን ስብከት፣ ከየተካፈሉበት ሴሚናርና ከተከታተሉት የኃይማኖት ትምህርት ጉባኤ ያሙትን ዕውቀት ሁሉ ለእምነታቸው መገንቢያ ሊያውሉት ሲሞክሩ ይስተዋላል። መኃይመ ቤተ ሠሪ ያየውን ሁሉ «አይለፈኝ» ሊል እንደሚያግበለብስ፣ እነዚህ ጽኑ መሠረት የሌላቸው ክርስቲያኖችም ያለ ምንም መመዘኛ የሰሙትን ሁሉ ያምናሉ ማለት ነው። ይህም ለለየለት ውዥንብርና ግራ መጋባት ከመዳረግ በስተቀር ለክርስቲያናዊ ሕይወታቸው መታነጽ የሚያበረክተው አንዳችም ፋይዳ አይኖርም። ታዲያ ለዚህ መሰሉ ችግር እኛም ሆንን ወይም በቅርብ የምናቃቸው ወዳጆቻችን ተጋልጠው ይሆን? ይህስ ከሆነ ዘንዳ ራሳችንንም ሆነ እነርሱን በምን መንገድ ልንረዳ እንችላለን?

ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የተነሣሁት ይህን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳን ዘንድ ነው። የተሳካለትና ፍሬያማ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመመራት ልንከተላቸው የሚገቡ ስድስት ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች አሉ። እነዚህን በዕብራውያን 6፡1-2 ላይ ለፍረው የሚገኙ ናቸው።

የእነዚህን አስተምህሮዎች ጠቀሜታ በሁለት መንገድ አረጋግጫለሁ። በቅድሚያ በግል ሕይወቴ ውስጥ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ተጠቅሜባቸው ፍሬያማነታቸውን ያረጋገጥሁ ስሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ በአያሌ ወንድሞችና እህቶች ሕይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማስገኘታቸው የዓይን ምስክር በመሆኔ ነው። ይህን ከመለሰው ሐቅ በመነሣት ነበር በቅድሚያ ትምህርቱን በማስመልከት ከ1963 እስከ 1964 ዓ.ም. በራዲዮ መግለጫ መስጠት የጀመርኩት። ይሁን እንጂ ሕዝቡ ለትምህርቱ ልዩ ጉጉትና ፍቅር እንዳለው በማጤን ቀስ በቀስ በዚህ መልኩ ተቀናጅቶ ለንባብ እንዲበቃ አደረግሁ።

የመጽሐፉ ተፈላጊነት እጅግ እየጨመረ በመሄዱም ዓለም አቀፍ ዝናን ከማትረፍም ባሻገር በሃያ ቋንቋዎች ሊተረጎም በቅቷል። ከተተረጎመባቸው ቋንቋዎችም መካከል አረብኛ፣ ዕብራይስጥ፣ ራሺያኛ፣ ሃንጋሪያን፣ ኢንዶኔዥያኛ ፣ ቻይናኛና ወዘተ... ይገኙበታል። ከ1983 ኤ.አ.አ. አንስቶም በመላው የአሜሪካ ግዛት በዚህ መልክ ተዘጋጅቶ በኃይማኖት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተሰራጭቷል።

ለውድ አንባቢያን በመጨረሻ ላሳስብ የምወደው ነገር ቢኖር በቅድሚያ ጥናት ከመጀመራቸው በፊት በንጹሕ ልብና አዕምሮ ለመነሳሳታቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ ነው። ለጊዜውም ቢሆን ቀደም ሲል ያዝዟቸውን ሃይማኖታዊ ግንዛቤዎችና የሚያራምዷቸውን አስተሳሰቦች ወደ ጎን ሊሏቸው ይገባል። ከዚያ በተረፈ ግን በዚህ መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ለመከታተልና **የሕይወታችሁም መመሪያ** ለማድረግ እግዚአብሔር እንደሚረዳችሁ አልጠራጠርም። ስለዚህ በርቱና ግፉበት! እግዚአብሔር ከአናንተ አይለይምና ሁሉም ለመልካም እንደሚሆን እትጠራጠሩ!

ዴሪክ ፕሪንስ
ፎርት ሎደርዴል ፍሎሪዳ
ጃንዋሪ 8/1993 ዓ.ም.

ስለ ጸሐፊው ታሪክ በአጭሩ

የዴሪክ ፕሪንስ ወላጆች እንግሊዛዊ ቢሆኑም አርሳቸው ግን የተወለዱት በሕንድ አገር ነበር። ክፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ወደ እንግሊዝ ከመጡ በኋላ እጅግ ስመ-ጥር በሆኑት በኢቶን ኮሌጅና በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ በግሪክና በላቲን ቋንቋ ተመርቀዋል። እንደዚሁም ከ1940 እስከ 1948 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ዓመታት በካምብሪጅ ከሚገኘው ኪንግስተን ኮሌጅ የጥንታዊና የዘመናዊ ፍልስፍና ትምህርቶችን አስተምረዋል። ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲና በኢየሩሳሌም በሚገኘው የሒብሩ ዩኒቨርሲቲ፣ የዕብራይስጥና የአራማይክ ቋንቋዎችን አጥንተዋል። እነኚህን ከመሳሰሉት ቋንቋዎች ጎን ለጎን በርከት ባሉ የዘመናችን ቋንቋዎችም የተካኑ ታላቅ ምሁር ናቸው።

ዴሪክ ፕሪንስ ጌታ ኢየሱስን ያወቁት በ2ኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ በእንግሊዝ ሠራዊት ውስጥ በሕክምና ክፍል ተደልድለው ሰማገልገል ላይ በነበሩበት ወቅት ነው። ይህንንም ሕይወታቸውን የለወጠውን ልምምድ በማስመልከት የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

«ጌታን ለማወቅ ታላቅ ዕድል ካገኘሁበት ቀን አንስቶ ለምንጊዜም መመሪያዎቼ ካደረግኋቸው ሁለት መደምደሚያዎች ላይ ደርሻለሁ። የመጀመሪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው እንደሆነ ማወቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ፣ ተጨባጭና ጊዜ የማይሽረው መጽሐፍ መሆኑን ማመን ነው። እነዚህም ሁለት ግንዛቤዎች መላው ሕይወቴን ሊቀይሩት ችለዋል።»

ጦርነቱ ካለቀ በኋላም ቢሆን ዴሪክ ፕሪንስ በወታደራዊ መሪዎቹ ትዕዛዝ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ተደርጎ ነበር። የመጀመሪያ ሚስታቸው የሆኑትን ሊዲያንም ያገኙት በዚችው ከተማ ነው። በዚሁ ወቅት ባልና ሚስቱ

ስምንት ሕጻናትን በጉዲፈቻ ከማሳደጋቸውም በላይ በ1948 ዓ.ም. የአዲሲቷን እስራኤል ነጻ መንግሥት መመሥረት በቅርብ ሆነው ሰመከታታል ችለዋል።

ከዚያም ወደ ኬንያ በመምህርነት ለማገልገል በሄዱበት ወቅት አፍሪካዊት የነበረችውን ዘጠነኛ የጉዲፈቻ ልጃቸውን አግኝተዋል። በ1975 ዓ.ም. ባለቤታቸው ሲዲያ በሞት ከተለዩአቸው በኋላ ዴሪክ ፕሪንስ ሦስት የብቸኝነት ዓመታትን አሳልፈው በ1978 ዓ.ም. ሩት የተባሉትን የአሁኗን ሚስታቸውን አገቡ።

በአሁኑ ዘመን ካሉት ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን አንዱ የሆኑት ዴሪክ ፕሪንስ ከማናቸውም ቤተክርስቲያን ያልወገኑ፣ ለተለያዩ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎች ተገዢ ባለመሆን፣ ትምህርታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረታቸው አያሌ ተከታዮችን በመላው ዓለም ለማትረፍ ችለዋል። ለምሳሌ «ከዴሪክ ፕሪንስ ጋር በየዕለቱ» የሚሰው ሃይማኖታዊ የራዲዮ ትምህርታቸውን ክግማሽ በላይ በሆነው የዓለም ክፍል ተደማጭነት ከማትረፉም በላይ በሦስት የተለያዩ የቻይና ቋንቋዎች «ማንዳሪን፣ አሞንና ካንቶኒዝ» እንዲሁም በእስፓንኛና በራሺያ ቋንቋ ጭምር ይተላለፋል። እንዲሁም 400 የኦዲዮ ካሴትና 50 የቪዲዮ ካሴቶች ከሃምሳ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉመው ተሠራጭተዋል። ከአርባ በላይ የሚሆኑትም መጻሕፍቶቻቸው በሌሎች ታዋቂ የዓለም ቋንቋዎች ተተርጉመው ክብዙ አንባቢዎች እጅ ደርሰዋል።

«ግሎባል አውትሪች (Global Outreach) የተባለው ሚሲዮናዊ ድርጅታቸውም በሦስተኛው ዓለምና በኮሚኒስት አገሮች ለሚገኙ የተለያዩ የኃይማኖት መሪዎች፤ መጻሕፍቶቻቸውና ያስቀረጹአቸውን ካሴቶች በነጻ በማደል ሰፊ አገልግሎት ያበረክታል። ምንም እንኳን እኚህ ዝነኛ የኃይማኖት ሰው በአሁኑ ጊዜ ዕድሜያቸው ከሰማንያ ዓመት በላይ ቢሆንም፤ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በመላው ዓለም አሁንም በመዘዋወር ሰብዙ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል በማካፈል ወደ ክርስቶስ ያመጣሉ፤ ክታመሙትና ከተቸገሩትም ጎን በመቆም በምክራቸውና በትንቢታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርታቸው ያጸኑአቸዋል።»

የዚህ ዓለም አቀፋዊ የሆነው የዴሪክ ፕሪንስ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በሻርለት ናርዝ ካሮላይና አሜሪካ ውስጥ ሲሆን፤ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችም በእንግሊዝ፣ በካናዳ፣ በአውስትራሊያ፣ በኒውዚላንድ፣ በፊረንሳይ፣ በጀርመን፣ በሲንጋፖር፣ በኔዘርላንድና በደቡብ አፍሪካ ይገኛሉ።

የመጽሐፉ አቀነባበርና ጠቀሜታዎቹ

ይህ «የጽድቅ ሕይወት መሠረቶች» መጽሐፍ የተዘጋጀው ተጨባጭ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ለማስተላለፍ እንደመሆኑ የተቀነባበረውም በሚከተለው ዘዴ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፡- አስተምህሮዎቹ በየምዕራፉ ጥልቀት የቀረቡበት ክፍል አለ።

በሁለተኛ ደረጃ፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች የሠፈሩበት ክፍል አለ። ይኸውም በእያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ሠፍረው የሚገኙበት ገጽ ጋር ለማገናዘብ ይረዳ ዘንድ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ፡- በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ዋነኞቹ የክርስትና እምነት አስተምህሮዎች በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ እንደሚገኙ የተመላከተበት ክፍል ነው።

ክፍል 1



የእምነት መሠረት

ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው፥ ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ፡፡ ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤ ጎርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለመተሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም፡፡

ሉቃስ 6:47-48

መግቢያ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ

በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም የሚገኙት የክርስትና እምነት ተከታዮች ብዛት ቢያንስ አንድ ቢሊዮን አካባቢ ይገመታል፡፡ እንግዲህ ይህ ቁጥር በየትኛውም የዓለም ክፍል በሚገኙት የተለያዩ ዝርያዎች፣ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያቅፍ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከእነዚህ ብዙዎቹ በስም ብቻ ክርስቲያኖች ቢሆኑም እንደ ክርስቲያን ይቆጠራሉ፡፡ ስለዚህ በዓለም ከሚገኙት የኃይማኖት ዘርፎች መካከል ተቀዳሚውን ደረጃ የያዘው ክርስትና ነው ሰማለት ይቻላል፡፡

በመሠረቱ እነዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ ለእምነታቸውም ሆነ ለምግባራቸው ሥልጣን ያለው መመሪያ አድርገው የሚቀበሉት መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን በእስልምና ሃይማኖቶች ዘንድም እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ተቀባይነት አለው፡፡ በመሆኑም በዓለም ውስጥ ተፈላጊነት ካላቸው መጻሕፍት መካከል አንድም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስተካከል የለም፡፡ በተለይም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የማይዳሰሰው የጥበብ ዘርፍ ባለመኖሩ በማንኛውም የዓለም ሕዝብ ዘንድ ተነባቢነት ለማትረፉ የማያጠያይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ጥሩ የሆነ አጠቃላይ ዕውቀትን ለማግኘት የሚፈልግ ማንም ሰው የግድ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርበታል፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 39 መጻሕፍትን ያቀፈው ብሉይ ኪዳን በመባል የሚታወቀው ሲሆን፣ ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው በአመዛኙ በዕብራይስጥ ቋንቋና አልፎ አልፎም በአረማይክ ነበር፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ የሚታመነው 27 መጽሐፍትን የሚያጠቃልለው አዲስ ኪዳን ነው፡፡

ብሉይ ኪዳን የሚጀምረው በዓለምና በተለይም በአዳም መፈጠር ላይ ነው። አዳምና ሚስቱ ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው እንዲሁ ኃጢአት ወደ ዓለም ሊገባ እንደቻለና፣ በራሳቸውና በልጆቻቸው ላይ እንዲሁ ፍርድን እንዳስከተሉ መጽሐፉ ያብራራልናል። ከዚህም በመቀጠል የመጀመሪያዎቹን የአዳም ዝርያዎች ታሪክ ያስቀምጥልናል።

ከአስራ አንድ ምዕራፎች በኋላ ግን የልዩ ሕዝቦች አባት ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል ስለተመረጠው ስለ አብርሃምና በዘሩም አማካይነት ለመላው ዓለም ደህንነትን ስለሚያመጣው መሢህ ተገልጾ እናገኛለን። «እስራኤል» በመባል በእግዚአብሔር ስለተሰየመው የአብርሃም ልዩ ዝርያ የምናነበውም በዚሁ ክፍል ነው። እንግዲህ ብሉይ ኪዳን በተለይ የሚያተኩረው በዚሁ የተመረጠ ሕዝብ የሁለት ሺህ ዓመታት ታሪክ ነው።

በእነዚህ ረጅም ዘመናት መካከል ግን በጉልህ የምናጤናቸው ትልልቅ ቁም ነገሮች አሉ። በተለይም ስለ እግዚአብሔር ባህርይ፣ ከሕዝቦችም ሆነ ከግለሰቦች ጋር ስለሚያደርገው ግንኙነት፣ ስለ ፍቅሩና ስለ ፍትሑ፣ ስለ ጥበቡና ኃይሉ፣ ስለ ይቅር ባይነቱና ታማኝነቱ ሁሉ በዝርዝር የምንረዳው በዚሁ ክፍል ውስጥ ነው። ብሉይ ኪዳን በተለይ የሚያተኩረው ደግሞ እግዚአብሔር ከግለሰቦችም ሆነ ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ባለው ታማኝነት ላይ ነው። እግዚአብሔር በተለይም እስራኤልን እንደ ሕዝብ መምረጡ ለአብርሃም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት የዓለም አዳኝ የሆነውን መሢህ ለመላክ የለጠውን የተስፋ ቃል ተፈጻሚ ለማድረግ ነው። መሢሕ የሚለው ቃል መሠረቱ ዕብራይስጥ ሲሆን ትርጉሙም «የተቀባ» ማለት ነው።

ከዚህ የሚቀጥለው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ክፍል ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደምን በናዝሬቱ ኢየሱስ አማካይነት ተፈጻሚነት እንዳገኘ ያሳየናል። ይኸውም የናዝሬቱ ኢየሱስ «ክርስቶስ» ተብሎ መጠራቱ ተገልጧል። ይህ ስም ከግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም «የተቀባ» ወይም «መሢሕ» ማለት ነው። መሢሕ ሆኖ የመጣው ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተነገሩትን ትንቢቶች ሁሉ አንድ በአንድ ያሟላል። በመሆኑም ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የተለያዩ መጻሕፍት ሳይሆኑ ወጥነት ያለው የአንድ መጽሐፍ አካላት ናቸው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ የሚያስረዳን ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ደኅንነት ስላለው ዕቅድና ስለ ዕቅዱም ተፈጻሚነት ደረጃ በደረጃ የሚያብራራልን የሕይወት መመሪያችን ነው።

1

የክርስቲያኖች የእምነት መሠረት

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአንድ አማኝ ሕይወት በተደጋጋሚ ከቤት አሠራር ወይም ከሕንጻ ግንባታ ጋር ተነጻጽሮ እንደቀረበ እናያለን። ለምሳሌ በይሁዳ መልእክት 20 ላይ « ... ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ ...» የሚል ጥቅስ እናገኛለን።

ሐዋርያው ጳውሎስም አዘውትሮ በተመሳሳይ የገለጻ ዘዴ ይጠቀም ነበር። በ1ኛ ቆሮንቶስ 3:9-10 ላይ «... የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ ... እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ ... » ሲል፣ «በኤፌሶን 2:22» ላይ ደግሞ « እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ» ይላል። እንደዚሁም «በሐዋርያት ሥራ 20:32» «... ያንጻችሁ ዘንድ ለጸጋው ቃል አደራ ለጥቻችኋለሁ» ማለቱን እንመለከታለን። በእነዚህ ሁሉ ጥቅሶች ውስጥ የምናጤነው ፍሬ ነገር የአማኙ ሕይወት ከሕንጻ ሥራ ጋር ተመሳስሎ መቅረቡን ነው።

አንድን ሕንጻ ዘለቄታ ባለው መልኩ ለማቆም ወሳኙ የመሠረቱ ጥንካሬ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የመሠረቱ ጥንካሬ የሕንጻውን ክብደትና ግዝፈት ይወስናል። በተልካሻ መሠራት ላይ መቀለስ የሚቻለው እንደዚያው ደላላ ጎጆ ሲሆን በጠንካራ መሠረት ላይ ደግሞ ትልቅ ሕንጻን መገንባት ይቻላል። በመሠረቱና በሕንጻው መካከል ወሳኝ የሆነ ግንኙነት አለ። ትዝ እንደሚለኝ በኢየሩሳሌም ውስጥ በምኖርበት ጊዜ በአንድ አሥራዊ ስው የተሠራ ቤት ተከራይቼ ነበር። ይህ ስው የሚሠራው ቤት ከማዘጋጃ ቤቱ ያገኘው ፈቃድ የባለ ሁለት ፎቅ እንደ መሆኑ የማዕዘኑም ጥንካሬ ከዚሁ ጋር የተዛመደ ነበር። ሆኖም ግን ይህ ሦርያዊ ስው የበለጠ ከሚያከራየው ቤት ያለ አግባብ ገቢ ለመሰብሰብ በማቀድ ያለ ማዘጋጃ ቤቱ ፈቃድ አንድ ተጨማሪ ፎቅ በማከል ሠራ። ታዲያ እና በዚያው ቅጥ ውስጥ በመኖር ላይ እንዳለን ቤቱ ቀስ በቀስ በአንድ ጎኑ ማዘመም ጀመረ። ቀስ በቀስም እላያችን ላይ እስከ መደርመስ ሊደርስ ነበር።

ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው? መልሱ ቀላል ነው፡- የቤቱ መሠረት ያ ስው የተመኘውን ያህል ሕንጻ ለመሸከም የጠነከረ አለመሆኑ ነው።

ዘመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥም ተመሳሳይ የሆነ ሁኔታ ያጋጥመናል። አንዳንድ ክርስቲያኖች እጅግ የሚያስቀናና የተዋበ ክርስቲያናዊ ሕይወት የመኖር ፍላጎትና ዕቅድ ሊኖረን ይችላል። ሆኖም ግን ያ ምኞታችን ብዙም ሳይቆይ ክንቱና መና ሆኖ ይቀራል። በመጀመሪያው ላይ በምላሌነት እንደተጠቀምንበት ሕንጻ በቀላሉ ያዘማል። ከዚያም ሙሉ በሙሉ በመደርመስ ፍርስራሽ ብቻ ይቀራል። ያለ ጠንካራ እምነት የሚገነቡ ስዕሰቶችና ጸሎቶች እንዲሁም ዕቅዶች ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ አርባና ቢስ ሆነው ይቀራሉ።

በእነዚህም ፍርስራሾች ሥር ለሕንጻው መውደቅ ምክንያት የሆነውም ዋናው ምክንያት ይቀበራል። መሠረቱ በትክክል ባለመመሥረቱ ወይም ከለቅመ በላይ እንዲሸከም በመደረጉ ዕቅዱ ሁሉ ይከሽፋል።

ክርስቶስ የማዕዘኑ ዓለት

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ «ለክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረት እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ዕቅድ ምንድን ነው? » የሚል ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ ግልጽና ቁልጭ ያለ መልስ የምናገኘው በቅድሚያ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡11 ላይ ካስፈረው መልእክት ነው። «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠረት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።»

ይህን አባባል በይበልጥ በማጠናከር ደግሞ ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ኛው መልእክቱ 2፡6 ላይ ስለ ክርስቶስ የሚከተለውን ተናግሯል። «በመጽሐፍ፡- እነሆ፣ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ ... ተብሎ የሰፈረው ነው።»

ስለዚህ ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን ሁለቱም ለክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረቱ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያረጋግጡልናል። ከእርሱ በስተቀር ሌላ ማንም፣ ምንም፣ መሠረት ሊኖረን አይችልምና የምናራምደው ቀኖና፣ የምናዘወትረው ቤተክርስቲያን ወይም የካህናትና የአምልኮ ሥርአቶች እንዳቸውም የእምነት መሠረት ሊሆኑ አይችሉም። ክኢየሱስ በስተቀር ሌላ መሠረት የለምና። እስቲ ጌታ ኢየሱስ ራሱ በማቴዎስ 16፡13-18 ላይ የተናገረውን እንመልከት።

«ኢየሱስ ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፡- ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ። እነርሱም፡- አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት። እርሱም እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ፣ አንተ ጴጥሮስ ነህ፣ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።»

እርግጥ አንዳንዶች ከዚህ ጥቅስ በመነሳት፣ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን በጴጥሮስ ላይ እመሰርታለሁ ለማለት እንደተናገረና፣ የቤተክርስቲያንም መሠረቷ ይህ ሐዋርያ ስለመሆኑ አጥብቀው ይከራከራሉ። ይህ የቤተክርስቲያን የማዕዘን ድንጋይ የመሆን ጉዳይ በአያሌዎች ዘንድ ከፍተኛ ጭቅጭቅና ውዝግብ እስክትሳል። ስለዚህ ኢየሱስ «በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ» ሲል የተናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ በመተንተን ከትክክለኛው መልእክቱ ላይ መድረስ እጅግ ወሳኝ ነው።

ክርስቶስ ለጴጥሮስ የሰጠውን መልስ በማስመልከት በጥንታዊው የግሪክ ቋንቋ የተዘገበው ቃል ሁለት ፍቺዎችን ያዘለ ነው። በግሪክኛ «ፔትሮስ» ጴጥሮስ ማለት ጠጠር ወይም ትንሽ ድንጋይ ማለት ሲሆን «ፔትራ» ማለት ግን ዓለት ማለት ነው። ክርስቶስም ሲናገር፡-

«አንተ ፔትሮስ ነህ፣ በዚህች ፔትራ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ»። ምንም እንኳ ሁለቱ ቃላት የድምፅ መመሳሰል ቢኖራቸውም ትርጉማቸው ግን የተለያየ ነው። ጴጥሮስ ማለት ትንሽ ድንጋይ (ጠጠር) ማለት ሲሆን ፔትራ ግን ትልቅ ዓለት ማለት ነው። መቼም በአንዲት ጠጠር ላይ ቤተክርስቲያንን መመሥረት የማይመስል ነገር በመሆኑ ክርስቶስ፣ ጴጥሮስን በተራ ወይም በማንኛውም ድንጋይ መመሰሉ አልነበረም። ዓለት ግን ግዙፍና ጠንካራ

ድንጋይ እንደ መሆኑ፥ ክእርሱም እጅግ የሚበልጥና ለቤተክርስቲያን መሠረት ሊሆን የሚገባው አብሮት ያለ መሆኑን በማስገንዘብ ነው ክርስቶስ የተናገረው። ይህን አተረጓጎም ማናቸውም እመዛዛኝ ሕሊና ያለው ሰው ሊቀበለው የሚገባ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ በማያወላውል መልኩ የተደገፈ ነው። ምናልባትም ቤተክርስቲያን እንደ አንዳንዶቹ ግምት ይህን ጊዜ በጴጥሮስ ላይ ተመሥርታ ቢሆን ኖሮ የቱን ያህል ዋጋቢና ዘለቂታዊነት የሌላት በሆነችም ነበር። ለዚህም ብዙ ሳንርቅ በዚሁ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የምናገኘው ሌላ ታሪክ ማረጋገጫ ይሆንልናል። ኢየሱስ ወደ ፊት ከአይሁድ ሰለሚነሳበት ተቃውሞና ስለሚጠብቀው የመስቀል ሞቅ ለደቀመዛሙርቱ ባሳወቃቸው ወቅት የሚከተሰው ትርዒት ተፈጽሞ ነበር። «ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፡- አይሁንብህ፥ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገስጸው ጀመረ። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፡- ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን አንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አሰው።»

ከዚህ ምልልስ በግልጽ የምንረዳው፥ የጴጥሮስ አስተሳሰብ አንድም በሰዎች ምክር ስለመበከሉ ወይም አንደዚያ ለማለት በሰይጣን ለመገፋቱ ክርስቶስ የገሰጸው በመሆኑ የዘላለማዊቷ ቤተክርስቲያን የማዕዘን ድንጋይ ሊሆን ይችላል? ብሎ መጠየቅ ይቻላል።

እንደዚሁም በሌላ ወንጌል ውስጥ ይኸው ጴጥሮስ ክርስቶስን በእንዲት የቤት አገላጋይና በዙሪያቸውም በነበሩት ሰዎች ፊት በተከታታይ ሦስት ጊዜ እንደካደው ተዘግቦ እናገኛለን። ሌላው ቀርቶ ከትንሣዔና ከዕሰተ ጰንጠቆስጤ በኋላ እንኳን ጳውሎስ ስለጴጥሮስ በወንጌል ሙሉ በሙሉ ባለመተማመን ለአይሁዳዊያን ስለማድላቱ በመጥቀስ ወቅሶታል። ገላትያ 2:11-14

ስለዚህ ጴጥሮስን የቤተክርስቲያን ማዕዘን የሆነው ዓለት ነው ለማለት እንችልም። የሚወደድና የመሪነት ብቃት ያለው ሰው ቢሆንም ዳሩ ግን እንደማንኛውም ሰው ደካማና፥ ለተለያዩ ስህተቶች የተጋለጠ ነበር፤ ስለዚህ እውነተኛው የክርስትና እምነት መሠረት ሊሆን የሚችለው እንዱና ከኃጢአት ሁሉ የነጻው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ የሚያረጋግጡ አያሌ ጥቅሶችንም ከብሉይ ኪዳን ለማግኘት ይቻላል።

ለምሳሌ በመዝሙር 18:2 ላይ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የሚከተለውን ትንቢት ተናግሯል፡- «እግዚአብሔር ዓለቴ፥ አምባዬ፥ መድኃኒቴ፥ አምላኬ፥ በእርሱም የምታመንበት ረዳቴ፥ መታመኛዬና መጠጊያዬ ነው»

በመቀጠልም በመዝሙር 62:1-2 ላይ «ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን? »

«መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና፤ እርሱ መጠጊያዬ <ዓለቴ> ነው፥ እጅግም አልታወክም» ብሏል። እንደዚሁም በዚሁ መዝሙር ቁጥር 5-7 ላይ እሁንም፥ «ነገር ግን፥ ነፍሴ ሆይ፥ አንቺ ለእግዚአብሔር ተገዢ ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ናትና፤ እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና እርሱ መጠጊያዬ <ዓለቴ> ነው፥ አልታወክም መድኃኒቴና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው፤ የረድኤቴ አምላክ፥ <ዓለቴም> ተስፋዬም እግዚአብሔር ነው።» ሊል እናገኛለን።

ይህ አንግዲህ ሁሉንም ነገር ግልጽ እንደሚያደርግልን አያጠራጥርም። <ዓለቴ> የሚለውን ቃል ሦስት ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ስናገኘው «ደኅንነትን» በተመለከተ ደግሞ አራት ጊዜ እንደተጠቀሰ እናያለን። ይህም ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን «ዓለት» እና ደኅንነት» በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጣምረው የቀረቡ ቃላት መሆናቸውን ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት ተሟልተው የሚገኙት በአንድ ሰው ውስጥ ብቻ ነው። ያም ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ስለዚህ አባባል ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልግ ቢሆን እሁንም የሐዋርያው ጴጥሮስን ቃላት በድጋሚ ለመጥቀስ እንችላለን። ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 4:12 ላይ ለአስራኤል ሕዝቦች ስለ ጌታ ኢየሱስ በሚያስረዳበት ወቅት «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ሰም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» በማለት በማያሻማ መልኩ ገልጾታል። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ብቻውን ዓለት፥ ለዘመናት ጸንቶ የቆመና ለደኅንነታችን መተማመኛ የሆነው የመሠረት ድንጋይ ነው። በዚህም ላይ እምነቱን የሚመሠርተው እውነተኛ አማኝ «እግዚአብሔር ዓለቴ፥ እምባዬና መጠጊያዬ ነው፥ የሚያስፈራኝም የለም» በማለት እንደ ዳዊት በሙሉ ልቡ ሊናገር ይችላል።

ፊት ለፊት መቋቋም

ታዲያ እንድ ሰው በዚህ በዓለት በተመሰለው ክርስቶስ ላይ እንዱት መታመን ሊጀምርና ብሎም እምነቱን ለማጠናከር ይችላል? ለዚህ መልስ ለማግኘት ይረዳን ዘንድ ቀደም ሲል በክርስቶስና በጴጥሮስ መካከል የተካሄደውን የቃል በቃል ምልልስ ለዳግመኛ ጊዜ እንመልከት። ጴጥሮስ ለኢየሱስ «እንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ማቴዎስ 16:16 በማለት መልሶ ነበር። አስቲ በሁለቱ መካከል የተካሄደውን ውይይት በዓይነ ህሊናችን ልናየው እንሞክር።

በማስረጃዎች በመደገፍ እንዳስፈርነው እውነተኛው ዓለት ክርስቶስ ብቻ ነው። ሆኖም ግን ይህን ማለት ደግሞ ክርስቶስ ክሌሎች ፍጹም ራሱን ያገለለ ነው፥ ወይም አባባሉ ሐሳባዊ ብቻ ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም ከዚህ ልምድ በመነሳት አራት የዕድገት ደረጃዎችን ልናጤን እንችላለን።

በቅድሚያ፡- በክርስቶስና በጴጥሮስ መካከል ቀጥተኛና ግላዊ ግንኙነት ተመሥርቶ ነበር። የሚነጋገሩት ፊት ለፊት እንጂ በመሃላቸው ጣልቃ የገባ አማላጅ ሰው አልነበረም፤ ሌላ ሰው የተጫወተው ሚና የለም።

ሁለተኛ፡- በዚህ ሳቢያ ለጴጥሮስ ግላዊ መገለጥ ተደርጎለት ኢየሱስ ጴጥሮስን «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብጹዕ ነህ» በማለት ተናግሮታል። ይህ መገለጥ በምርምር ኃይል ወይም በመላምት የሚደረስበት አልነበረም። በምትኩ እግዚአብሔር አብ በቀጥታ ለጴጥሮስ ያደረገለት መንፈሳዊ መገለጥ ውጤት ነው።

ሦስተኛ፡- ጴጥሮስ በዚህ መልኩ የተደረገለትን መገለጥ በመረዳቱም፤ በሙሉ ልቡ አምኖበት ነበር።

አራተኛ፡- ይህን አምኖበት የተቀበለውን መገለጥ ጴጥሮስ በአደባባይ መስክሮለታል።

እነዚህ አራት ደረጃዎች የሚያመለክቱን እምነታችንን በዓለቱ ላይ መመሥረት የሚያጎናጽፈንን መንፈሳዊ ኃይል ነው። በዚህ ልምድ ውስጥ ሐሳባዊ፤ መላምታዊ ወይም በእእምሮ ደረጃ የተፈጸመ አንዳችም ነገር የለም። በእያንዳንዱ ደረጃ ውስጥ ተጨባጭ ልምምድ ስለመካሄዱ የማያጠራጥር ነው። የመጀመሪያው ክርስቶስን በቀጥታና ፊት ለፊት መገናኘት ሲሆን ሁለተኛው ስለ ክርስቶስ የሚኖረን መንፈሳዊ መገለጥ ነው። ሦስተኛው ደረጃ በክርስቶስ ማመን ሲሆን በአራተኛም ደረጃ ስለእርሱ በግልጽ መመስከር ነው።

ይህ ማለት እንግዲህ በግል ፊት ለፊት የተገናኘነው በክርስቶስ፤ የተገለጠልን ክርስቶስ፤ ያመንንበትና የመሰከርንለትም ክርስቶስ ነው ማለት ነው። በመሆኑም ለእያንዳንዱ አማኝ የእምነት መሰረቱ የሚሆነው የማዕዘኑ ድንጋይ ክርስቶስ ብቻ ነው።

መንፈሳዊ መገለጥ

ሆኖም ግን በዚህ አጋጣሚ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፡- ይህ ዓይነቱ ልምምድ በአሁኑ ዘመን ሊያጋጥም ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ማለትም ጴጥሮስ ፊት ለፊት ክርስቶስን ለመገናኘት ያለውን ዕድል ያህል የአሁኑም ዘመን ክርስቲያን ሊኖረው ይችላል ወይ? የሚለው ነው።

ለዚህም ዋነኛ ጥያቄ የሚኖረን አንድ መልስ ብቻ ሲሆን ይኸውም «ይችላል!» የሚል ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ሁለት ምክንያቶች ማየቱ ይበቃል፡- በቅድሚያ መረዳት የሚኖርብን ለጴጥሮስ በዚያን መልኩ የተገለጠለት ክርስቶስ በለብዓዊ ተፈጥሮው ይዘት አለመሆኑን ነው። ጴጥሮስ ቀደም ሲል በአናጢነት ሙያ ይተዳደር የነበረውን የናዝሬቱን ኢየሱስ ያውቀው ነበር። አሁን ግን የተገለጠለት ኢየሱስ፡- መለኮታዊ፤ ዘለዓለማዊና የማይለወጠው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ያስ ክርስቶስ ነው አሁንም በአብ ቀኝ በክብር ያለው። ከሐዋርያት ዘመን ወዲህ ሁለት ሺህ ዓመታት ያህል

ያለፉ ቢሆንም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም ለዘለዓለም የማይለወጥ ነው። በመሆኑም በዚያን ጊዜ ለጴጥሮስ በተገለጸለት ባህርዩ ዛሬም ከልባችን ለምንሻው ሁሉ ለእያንዳንዳችን በተመሳሳይ ሁኔታ ይገለጥልናል። ሁለተኛ፡- የክርስቶስ ለጴጥሮስ መገለጥ የተገኘው በስሜት ወይም በስብዓዊ ተፈጥሮ አልነበረም። ያንን ምሥጢር «ሥጋና ደም» አልገለጠለትም። በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አማካይነት የተካሄደ መንፈሳዊ መገለጥ ነበር። እነሆም ያ ለጴጥሮስ ምሥጢርን ያሳወቀ መንፈስ ቅዱስ በአሁንም ሰዓት በመላው ዓለም የክርስቶስን ማንነት ለህዝቦች እየገለጠ ነው። ኢየሱስም ይህን በማስመልከት ለደቀመዛሙርቱ ስለገባላቸው ቃልኪዳን በዮሐንስ 16:13-14 ላይ እንደሚከተለው ተዘግቦ እናገኛለን።

«ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚለማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል እርሱ ያከብረኛል፤ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» እንግዲህ ይህን መሰሉ መገለጥ ዘለዓለማዊና መንፈሳዊ በመሆኑ ዓለማዊ በሆነ አስተሳሰብ ማለትም በጊዜ ገደብ፤ በአካባቢ ሁኔታዎች ቦዘሀሳዊ ልምዶች፤ በቋንቋና በአለባበስ የተወሰነ አይደለም።

ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚኖረን የፊት ለፊትና ግላዊ ግንኙነት፤ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደሚፈጸምልን ማመንና መመስከሩ፤ ለክርስቲያኖች የእምነት መሠረት ከሆነው ከማዕዘኑ ድንጋይ ጋር ያለንን ጎብረትና አንድነት ያጠናክረዋል፤ ያጎለብተዋልም። የቤተክርስቲያን ክፍፍል፤ የኃይማኖት መሪዎች አለመግባባት፤ ቀኖናዊ ክርክሮችና የመሳለሉት ሁሉ ኃላፊ ሲሆኑ፤ በክርስቶስ አዳኝነት የሚኖረን እምነት ግን ዘለዓለማዊ ነው። ማንም ስው እምነቱን በዚህ ዓለት ላይ በመመሥረት ጊዜ ሊሸረውና ሊለውጠው የማይችል መተማመንና ድፍረት ይኖረዋል።

እምነትን ማስረገጥ

ሁላችንንም ቢሆን የሚያለደንቀን ነገር ቢኖር፤ ቀደምት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እርጋታና የጠለቀ እምነት ምስክርነት በምናጤንበት ጊዜ ነው።

በዮሐንስ 17:3 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- «እውነተኛ እምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት።» ይህ ማለት እንግዲህ፤ እግዚአብሔርን በደፈናው ሰማወቅ መሞከር ሳይሆን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ራሱን የገለጸልን መሆኑን መረዳትና ማመን ማለት ነው። እንደዚሁም ኢየሱስ ክርስቶስን በታሪካዊነቱ ወይም በታሳቅ መምህርነቱ ብቻ መቀበል ሳይሆን፤ እግዚአብሔር በእርሱ

ውስጥ እንዳለ ማመንና መመስከር ነው። አሁንም ዮሐንስ በአንደኛው መልእክቱ ምዕራፍ 5:13 ላይ የሚከተሰውን ጽፏል፦ «የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑት ይህን ጽፌላችኋለሁ።»

ቀደምት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ማመን ብቻ ሳይሆን በግልም ያውቁት ነበር። በኑሮአቸው የተገለጠው እምነታቸውም ስለክርስቶስ ማንነት ግልጽና የማያሻማ ዕውቀት እንደነበራቸው አሳይቶል።

በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 20 ላይ አሁንም ሐዋርያው ዮሐንስ እንደሚከተለው ጽፏል፦ «የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ፥ አውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቦናን እንደሰጠን እናውቃለን፤ አውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ አውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው።»

በእነዚህ የትህትና ነገር ግን የእርግጠኝነት ቃላት አማካኝነት የተላለፈልንን ታላቅ መልዕክት ከልብ ስናጤን መሠረታቸው ክርስቶስን ማወቅ ብቻ እንደሆነ እንረዳለን። ሐዋርያው ጳውሎስም በ2ኛ ጢሞቴዎስ 1:12 ላይ የሰጠው ምስክርነት ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው፦ «... ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ተቀብዬአለሁ ነገር ግን አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ።»

እዚህ ላይ አሁንም ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ ጳውሎስ የተናገረው «ስለማምነው አውቃለሁ» በማለት ሳይሆን «ያመንሁትን አውቃለሁ» ማለቱን ነው። የጳውሎስ እምነት ከሌሎች በተነገረ ሳይሆን በግሉ ባገኘው ልምድ ላይ የቆመ ነው። «ያመንሁትን አውቃለሁ» ብሎ በሙሉ ልቡ የተናገረለት በግል ስለሚያውቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከዚህም የእምነት ጥንካሬው የተነሳ፥ አሁንም ሆነ ለዘለዓለም ነፍሱን ከዚህ ብሩህ ዕድል ሊያወጣት የሚችል ማንም እንደሌለ አምኗል።

እምነትን ማወጅ

ለብዙ ዓመታት በታላላቅ የለንደን ከተማ አውራ ጎዳናዎች ላይ በመዘዋወር አስብክ ነበር። ታዲያ የማስተላለፈውን መንፈሳዊ ትምህርት ስጨርስ አድማጮቼን በግል በመቅረብ «ክርስቲያን ነህን?» የሚል ጥያቄ አቀርብላቸው ነበር። መልስ ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ከሆኑት መካከል ብዙዎቹ፦ «ይመስሰኛል» ወይም «ተስፋ አደርጋለሁ» ወይም «ወደ ፊት ስመሆን እሞክራለሁ» የሚል ምላሽ ሊሰጠኝ አንዳንዶቹ ደግሞ «ክርስቲያን መሆኔን አላውቅም» በማለት ይገልጹልኝ ነበር። የእነዚህ ሰዎች ሁሉ መልሶች በመሠረቱ ተመሳሳይነት ያለው ግልጽ «ክህደት» ይታይበታል። ክርስቶስን

በግል በማወቅ በእምነታቸው በጠንካራ መሠረት ላይ እምነታቸው እንዳልቆመ የሚያመለክት ነው።

እስቲ ለእንተስ «ክርስቲያን ነህን ?» የሚል ተመሳሳይ ጥያቄ ባቀርብልህ የምትሰጠኝ መልስ እንዴት ያለ ይሆን ? ይህን ምዕራፍ ከመደምደሜ በፊት ከኢዮብ 22:21 አንድ ጥቅስ በመጥቀስ መመሪያ ሊሆን የሚገባ ምክር ላካፍላችሁ እወዳለሁ፦ «አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ፥ ሰላምም ይኑርህ፤ በዚያም በጎነት ታገኛለህ።

2

በመሰረቱ ላይ መገንባት

በመቀጠል የምንወያይበት ጥያቄ የሚከተለው ይሆናል። ከክርስቶስ ጋር በግል በመተዋወቅ እምነታችንን ከመሠረትን በኋላ፣ እንዴት ነው እምነታችንን ልናጸናውና ልናሳድተው የምንችለው? በሌላ አነጋገር ይህ ጥያቄ በመሠረታችን ላይ የምንሠራው ቤት ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል? የሚል ሊሆን ይችላል።

ለዚህ ጥያቄ ተገቢ የሚሆነውን መልስ የምናገኘው በማቴዎስ 7:24-27 ውስጥ በልባሙና በሰነፉ ሰው በመመሰል ኢየሱስ ከተናገረው ምሳሌ ነው፦- *«ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሱም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፣ በዓለት ላይ ስለተመሠረተ አልወደቀም። ይህንንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሱም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፣ ወደቀም፣ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።»*

ከዚህ ምሳሌ ውስጥ ልብ ብለን ልናጤነው የሚገባ ፍሬ ነገር በሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በገነቧቸው ቤቶች ላይ የደረሰው አደጋ የተለያየ አለመሆኑን ወይም የአደጋው ክብደት የአንዱ ገዝፎ የሌላው ደግሞ የሚያንስ አለመሆኑን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የሁለቱም ሰዎች ቤቶች ለዝናብ፣ ለጎርፍና ለነፋስ ማዕበል ተጋልጠዋል። እንደዚሁ ሁሉ የክርስትናም ሕይወት ለአደጋ የተጋለጠ እንጂ በመሸሞንሞን የሚያልፉበት ልምምድ አይደለም። ይህንንም በማስመልከት በሐዋርያት ሥራ 14:22 ላይ የሚከተለው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፦- *«... ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል...»*

ያለ አንዳች ስደትና ያለ ምንም መከራ ወደ መንግሥቱ ሰማያት ሊያደርስ የሚችል ክርስቲያናዊ መንገድ ጨርሶ የለም፤ ወደ ተስፋይቱ ምድርም እያደርስም።

ታዲያ ወደ ምሳሌው ስንመለስ፣ በልባሙ ሰውና በሰነፉ ሰው መካከል ያለው ተጨባጭ ልዩነት ምን ይሆን? የሚለውን ጥያቄ አሁንም ትክክለኛ መልስ ልንለጥበት ይገባል። መልሱ አጭርና ግልፅ ነው። ይኸውም ልዩነታቸው ልባሙ ሰው ቤቱን በጠንካራ የማዕዘን ዓለት ላይ መመሥረቱ ሲሆን፣ ሰነፉ ሰው ደግሞ በአሸዋ ላይ ማቆሙ ነው። ልባሙ ሰው አስቀድሞ የሚያደርገውን በማወቅ ማዕበል ሊቋቋም የሚችል ሕንፃ ገነባ። ሰነፉ ሰው ግን በመታከት ያለ መሠረት የገነባው ቤት በቀላሉ በነፋስ ተጠራርጎ ተወሰደ።

መጽሐፍ ቅዱስ - የእምነት መሠረት

ለመሆኑ አንድን ሕንጻ በዓለት ላይ የመመሥረት ምሳሌ የሚያስተላልፍልን ትምህርት ምን ይሆን? ለመሆኑ ከእባባሉ ልናገኝ የምንችለው ግንዛቤ ምንድን ነው? ክርስቶስ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንዲሆን የሚከተለውን ምክሩን በቀላል ቃላት ገልጾልናል፦- *«ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።»*

እንግዲህ በዓለት ላይ መሥራት ወይም መገንባት ማለት በአጭሩ የክርስቶስን ቃል መስማትና ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው። በሕይወታችን ውስጥ ክርስቶስ ከገባና የእምነታችን መሠረት እስከ ሆነ ድረስ፣ ክዚያ በኋላ በዚህ በጸና ማዕዘን ላይ በእግዚአብሔር ቃል በመመራትና በመመሥረት ግንባትን ማነጽ እንችላለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መሪዎች ያስተላለፈውን ምክር በዚህ አጋጣሚ ማስታወሱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።
«አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ» የሐዋርያት ሥራ 20:32። ሐዋርያው እንዳስገነዘበው ፍሬያማ ለመሆን የምንችለው የእግዚአብሔርን ቃል እስካዳመጥን፣ እስከፈጸምነው፣ እስካጠናነውና ተግባራዊ

እስካደረግነው ድረስ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜም በልባችን በተጣለው ማዕዘን ላይ ጠንካራና ብርቱ የእምነት ሕንጻ ልንገነባ እንችላለን።

ይህ አባባል እጅግ ወሳኝ ወደ ሆነ የክርስትና እምነት ርዕሰ-ጉዳይ ያመራናል። ይኸውም በተቀዳሚ በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለው ግዙድና ምንድን ነው? ስለሚለው ሲሆን በመቀጠልም የምንመለከተው በእያንዳንዱ ክርስቲያንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ፥ በዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ «ቃል» ወይም «የእግዚአብሔር ቃል» ተብሎ እንደተጠራ እናገኛለን። ለምሳሌ ዮሐንስ 1:1 የሚከተለውን ይላል፦
«በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።»

በዚሁ በዮሐንስ 1:14 ላይ ደግሞ፦

«ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።» ተብሎ ተጽፏል።

እንደገናም በራዕይ 19:13 ላይ የሚከተለውን ጥቅስ እናገኛለን።
«በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል «ክርስቶስ»፥ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።»

ይህ የስም ማንነት የባህርይንም ማንነት ያመለክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል። ስለዚህ ሁለቱም መለኮታዊ፥ ሥልጣናዊና ፍጹም የእግዚአብሔር መገለጦች ናቸው። በሁለቱ መካከል ቅንጣት ያህል ልዩነት የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስን የመግለጡን ያህል፥ ክርስቶስም መጽሐፍ ቅዱስን ፈጽሞታል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የተጻፈ ቃል እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም የእግዚአብሔር የራሱ ቃል ነው። ከሥጋው በፊት ክርስቶስ በአባቱ ዘንድ የነበረ የአባቱ «ዘለዓለማዊ ቃል» ነው። ሥጋ በመሆኑም እግዚአብሔርን በተጻፉት ቃላት የገለጠው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እግዚአብሔርን ሥጋ በሆነ ቃል፥ በናዝሬቱ ኢየሱስ አማካይነት ገልጾታል።

የደቀ መዛሙርትነት ማረጋገጫ

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው ክርስቶስና መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ከሆኑ፥ አንድ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ያለውን ግንኙነት ዓይነት ከመጽሐፍ ቅዱስም ጋር ሊኖረው ግድ ነው ማለት ነው። ይህንንም በማስመልከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አያሌ ማስረጃዎች እናገኛለን። በቅድሚያ እስቲ ወደ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 እናምራ፦ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሊያስጠነቅቃቸው የምናየው በቅርቡ በሥጋ ከእነርሱ እንደሚለይና፥ ከዚያ በኋላ ግን በእርሱና በእነርሱ መካከል አዲስ የሆነ ግንኙነት እንደሚመሠረት ነው። ሆኖም ግን ለደቀመዛሙርቱ ይህ የክርስቶስ አባባል ምንም አልገባቸውም ወይም ሊቀበሉትና ሊያምኑበት አልፈለጉም ነበር። በተለይም ግራ የገባቸው ጉዳይ ክርስቶስ ከእነርሱ ተሰይቶ ተወስዶ እንደ ምን ዓይነት ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት የመቻሉ ሁኔታ ነበር።

ሆኖም ክርስቶስ ይህን በንግግሩ ግራ የመጋባታቸውን ሐቅ በመረዳት እንደሚከተለው ተናግሮቸዋል፦ *«ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም ሊያየኝም፤ እናንተ ግን ያዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።»* ዮሐንስ 14:19

ከዚህም በመነሳት ሐዋርያው ይሁዳ (የአስቆሮቱ ያልሆነው) *«ጌታ ሆይ፥ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጽ ያለህ እንዴት ነው?»* ቁጥር 22 በማለት ጥያቄ አቅርቦለታል። ይህም ጥርጣሬው በምን ዘዴና በእንዴት ያለ ሁኔታ ዓለም ሳያይህ ለእኛ ለደቀ-መዛሙርትህ ብቻ ራስህን ልትገልጥ ትችላለህ? የማለት ያህል ነው። ኢየሱስም ለዚህ ጥያቄ በቁጥር 23 ላይ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል።
«... የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።»

ከዚህ መልስ ውስጥ ሊጤኑ የሚገባቸው ቃላት በተለይ «ቃሌን ይጠብቃል» የሚሉት ናቸው። እውነተኛውን ደቀመዝሙር ከዓለማዊው ስመ ክርስቲያን የሚለየውም ይህ ትዕዛዝ ነው። የክርስቶስን ቃል የጠበቀ ብቻ ነው ደቀመዝሙሩ ሊሆን የሚችለው! እንደዚሁም ከዚህ ለክርስቶስ ከቀረበለት ጥያቄና ከእርሱም አመላለስ አራት ቁም ነገሮችን እንረዳለን። አሳቡን ግልፅ ለማድረግ ኢየሱስ የለጣቸውን መልስ ደግመን እናንብብ፦ *«የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።»* (ዮሐንስ 14:23)

የመጀመሪያው አንድን የክርስቶስ ደቀ-መዝሙር ከተቀረው ዓለም የሚለየው የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቁ ነው።

ሁለተኛው፦ የእግዚአብሔርን ቃል በመቀበል መፈጸሙ፥ ደቀ-መዝሙሩ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ማረጋገጫ መሆኑን ለእግዚአብሔርም ፍቅር ምክንያት መሆኑን፤

ሦስተኛ፦ ክርስቶስ ራሱን ለደቀ-መዝሙሩ የሚገልጠው ደቀ-መዝሙሩ የእግዚአብሔርን ቃል ሲታዘዝና ሲፈጽም መሆኑን፤

አራተኛ፦ እግዚአብሔር አብና ልጁም ወደ ደቀ-መዝሙሩ በመምጣት መኖሪያቸውን በእርሱ ዘንድ የሚያደርጉት በዚሁ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት መሆኑን ነው።

የፍቅር ፈተናው

ክርስቶስ ከሰጠን ከዚህ ትልቅ ስጦታ ጎን ለጎን ሐዋርያው ዮሐንስ በ1ኛው መልዕክቱ 2:4-5 ያስፈረውን በመቃጠል እንመለከታለን። «*እውቄዋለሁ የሚል ትእዛዙንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው፣ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፦*»

ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምንረዳው፥ ያለ ምንም ማጋነን ለአንድ ክርስቲያን ሕይወት ወሳኙ ነገር የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል ያለው ፈቃደኝነት መሆኑን ነው።

እስቲ እነዚህን መንፈሳዊ እውነታዎች ተጨባጭ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ እንመልከታቸው። በቅድሚያ አንድን ደቀ-መዝሙር ከዓለማውያን የሚለየው የእግዚአብሔርን ቃል መቀበሉ ነው ብለናል። ይህ የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያበስረናል። ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ ራሱን ይገልጥልናል ማለት ነው። እንደዚሁም ከአባቱ ከእግዚአብሔር በመሆን ማደሪያውን በእኛ ውስጥ ያደርጋል።

በሌላ አነጋገር ለእግዚአብሔር ቃል ያለን አክብሮት ለእግዚአብሔር ለራሱ የሚኖረን አክብሮት ነው። ማለትም ቃሉን ከምንወደው በላይ እግዚአብሔርን አንወደውም፤ ለቃሉ ከምንታዘዘው በላይ ለእግዚአብሔር አንታዘዝም። በመቀጠልም ቃሉን ከምናከብረው፥ በልባችንም ውስጥ እንዲሰፍን ከምንፈቅደው በላይ ለእግዚአብሔር የተሰየ ወይም የበለጠ ተገዥነት አይኖረንም ማለት ነው።

ለእግዚአብሔር የቱን ያህል ፍቅር እንዳለህ ለማወቅ የተጨነክበትና የተጠበብክበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ለዚህ መልሱን ብዙም ሳትመራመር ልታገኘው ትችላለህ። በቅድሚያ የእግዚአብሔር ቃል ለእኔ ምን ማለት ነው? ስትል ራስህን ጠይቀው። ለዚህ ለሁለተኛው ጥያቄ የሚኖርህ መልስ ለመጀመሪያውም ጥያቄ አግባባዊ መልስ ይሆንልሃል። በእግዚአብሔርና በቃሉ መካከል ልዩነት ስለሌለ፥ ቃሉን የምትወድ እስከሆንህ ድረስ እርሱንም ትወደዋለህ ማለት ነው። ይህ ማለት ልክ ቃሉን በምትወደው መጠን እንጂ ከዚያ አስበልጠህም ሆነ አሳንሰህ ልትወደው አትችልም!

የመገለጥ መንገድ

በአሁኑ ጊዜ ባለው የክርስትና ጎብረተሰብ ዘንድ ያለው ግንዛቤ እግዚአብሔር ከምንግዜውም ይልቅ በአሁኑ ወቅት ራሱን ለምዕመናን በተለያዩ መንገዶች በመግለጥ ላይ መሆኑን ነው። ይህም በሐዋርያት ሥራ 2:17 ላይ ለተናገረው ትንቢት ፍጻሜ መቃረብ ምልክትነት ነው። «*እግዚአብሔር ይላል፦ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሱ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎበዛዝቶችሁም ራዕይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያን ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።*»

በዚህ አጋጣሚ በትሕትና የተሞላ ምስጋናዬን ለእግዚአብሔር ላቀርብ እወዳለሁ። ምክንያቱም ከሥራዬ ባሕርይ የተነሳ በአፍሪካ፥ በእስያ፥ በአውሮፓ፥ በአሜሪካና በአውስትራሊያ አህጉሮች በተዘዋወርኩበት ጊዜ ሁሉ፥ የዚህን ትንቢት ቃል ተፈጻሚነት በዓይኔ ለማየት ብሎም ለመመስከር በመቻሌ ነው። በመሆኑም በመሉ ድፍረትና ያለ አንዳች ማመንታት ዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአሁኑ ጊዜ በስፋት ተግባራዊ እየሆኑ ናቸው አላለሁ። እግዚአብሔር በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኘውን ሕዝቡን በትንቢት፥ ራዕይ፥ በሕልምና... ወዘተ አማካይነት እያነጋገራቸው ነው።

ይህም ሆኖ ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው መገለጥ በምሉዕነት ቢሕርዩ የተጠቃለለው በእንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው ባይ ነኝ። ሌሎች መገለጦች ሁሉ ስለ ሐቀኝነታቸውና ትክክለኛነታቸው መመዘን ያለባቸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኘው ሥነመለኮታዊ ትምህርትና መገለጫ ውጪ ከሆኑ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይችልም።

በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5:19-21 ውስጥ ጳውሎስ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ተናግሯል፦ «*መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ።*»

እንደተባለውም እውነተኛ የሆኑትን የመንፈስ ቅዱስ መገለጫዎች መቀበል አለብን። ለማጥፋት ወይም ለማስተባበል መሞከሩ ግን በራስ ላይ ዕዳ መሸከም ነው። ይህም ስለተባለ ግን የተነገረውን ሁሉ አሜን ብለን መቀበል አለብን ማለት አይደለም። ነገሮችን ለማመዛዘንና ለመፈተን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ፈቅዶልናል። ስለዚህ መለኮታዊ ባሕርይ ከሚኖራቸው መገለጦች በስተቀር፥ የፈለገው ለው ስለተናገረ ብቻ አለስ ገለሉንም ልናምንበት ይገባል ማለት አይደለም።

ይህንኑ በማስመልከት ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ 8:20 ላይ እንደሚከተለው ያስገነዝበናል፦ *«ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም፡»*

ከዚህ የምንረዳው ለማናቸውም ነገር መለኪያው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ብቻ እንደሆነ ነው። ማንኛውም ትንቢት ልምምድ፥ መገለጥ ሆነ ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት፥ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ሊሆን አይችልም። እንደዚሁም ቅዱሱን ቃል የማሻሻል ወይም በላዩ ላይ የመጨመር ስልጣን የለውም። ከዚህ ውጪ አፈንግጦ፥ ለማስተማርም ሆነ ለመስበክ፥ ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ የሚሞክር ሁሉ የጨለማ ልጅ ነው ንጋት አይበራለትምና።

በተለይም በዚህ በያዝነው ዘመን በማንኛውም የሕይወት መስክ የመጽሐፍ ቅዱስ የበላይነትን ማረጋገጥ ያለብን ዘመን ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም መንፈስ ቅዱስ በተለየ መልኩና በሰፋት በመሰራት ላይ ነው። ሆኖም የአውነተኛ ክርስቲያኖች መጠን የመጨመሩን ያህል አስመሳዮችም በየስፍራው አቆጥቁጠው ይገኛሉ። ስለዚህ እነዚህን ሐሰተኛ ነቢያትና መምህራን ለመቋቋም ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ያሻል። ስለዚሁ የዘመናት ፍጻሜ በማስመልከት ክርስቶስ ራሱ እንደሚከተለው ያስጠነቅቀናል። *«በዚያን ጊዜ ማንም፦ እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም፦ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና፦ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ»* ማቴዎስ 24:23-24። ልክ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ጳውሎስም በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4:1-3 ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፦ *«መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ኃይማኖትን ይክዳሉ ይላልና፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፥ እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፥ አምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ፡፡»*

ጳውሎስ የሚያስጠነቅቀን በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኞች መምህራን በያሉበት እንደሚነሱና አማኞችን ለማሳሳት የሆነ ያልሆነ ዘዴ እንደሚፈጥሩ ነው። ሌላው ቀርቶ እንደተመለከትነው በኃይማኖትና በንጽሕና ሳቢያ፥ ጋብቻንና ምግብን እንኳ እስከመከልከል ይቃጣቸዋል። ከእነዚህ መሰሎች ሐሰተኞች ለመጠበቅ፥ ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ ብቻ ስለመሆኑም አጥብቆ ያስገነዝበናል።

በዚህ በእግዚአብሔር ቃል እስከተመራንና እስከተጋን ድረስ፥ ለለይጣናዊ መደለያዎችና ትንግርቶች በቀላሉ አንንበረከክም። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ምንጊዜም እንደማይለያዩ በዘመናችን ለማንኛውም አጋንንታዊ ተጽዕኖ አንሸነፍም። ቃሉና መንፈሱ በጋራ የሚሠሩ

ስለመሆናቸው በመዝሙር 33:6 ላይ የሚከተለውን ተጽፎ እናገኛለን፦ *«በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፤»*

እዚህ ላይ «እስትንፋስ» ተብሎ የቀረበው ቃል በዕብራይስጥ «መንፈስ» የሚያመለክት ነው። ሆኖም ግን በዚህ መልክ መቅረቡም የራሱ የሆነ ውበትና እውነታ አለው። የእግዚአብሔር እስትንፋስ መንፈሱ እንደመሆኑ፥ ቃሉ ከአፉ በሚወጣበት ጊዜ መንፈሱም አብሮ እንደሚወጣ ያመለክታል።

በእኛ እንኳን በሰብአዊ ፍጥረቶች ዘንድ ከአፋችን ቃል በሚወጣበት ጊዜ እስትንፋሳችንም አብሮ እንደሚወጣ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም የእግዚአብሔር ቃልና እስትንፋስ «መንፈሱ»ን አይለያይም። ይህንንም በይበልጥ ጉልህ አድርጎ የሚያስረዳን በዘፍጥረት 1:2 ላይ፥ *«...የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር»* የሚለው አገላለጽ ነው።

ከዚሁ ቁጥር በመቀጠልም፥ *«እግዚአብሔርም፦ ብርሃን ይሁን አለ»* የሚሉትን ቃላት እናገኛለን። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር አንደበት «ብርሃን» የሚለው ቃል ሲወጣ መንፈሱም አብሮት ወጥቷል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቃልና እስትንፋስ በዚህ መልኩ በአንደበት በመሆናቸው እግዚአብሔር ብርሃንን ለመፍጠር የነበረው ዓላማ ተሳካ። ይህን በመሰለ ታላቅ የፍጥረት ታሪክ ውስጥ የምናገኘው እውነታ በእያንዳንዱ ግለሰብም ውስጥ አለ። በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቃልና እስትንፋስ በአንድነት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዕቅድና ፈቃድ ያሟላል። ሆኖም ግን እነዚህን ሁለቱን ለማለያየት ከሞከርን፥ ማለትም መንፈሱን ከቃሉ በማግለል ብሎግነት ወይም ቃሉን ከመንፈሱ በመለየት ለማጥናት ከፈለግን ወይእግዚአብሔር ዕቅድ ውጪ በመንዛችን ዓላማችን ግቡን አይመታም።

ስለዚህ የመንፈሱን መገለጥ ከቃሉ ውጪ ለማግኘት የምንሞክር ከሆነ፥ ፍጻሜአችን አንድም ውድቀት አለበለዚያም ጭልጥ ያለ መናፍቅነት ይሆናል። ቃሉን ብቻም ያለ መንፈስ ቅዱስ እገዛ ማነብነቡ ውጤቱ ወገኖነትና አስመሳይነት ብቻ ይሆናል።

3

የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለተካተተው ትምህርት የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት በቅድሚያ በዮሐንስ 10:34-36 ውስጥ የሚገኘውን ጥቅስ ከልብ ማጤኑ እጅግ ጠቃሚ ነው። በጥቅሱ ውስጥ ክርስቶስ ከአይሁድ ጋር በመነጋገር እንዳለና፥ ስለ እግዚአብሔር ልጅነቱም ሊያስረዳቸው እንደሞከረ እናያለን። አባባሉንም ለማጠናከር ክርስቶስ አይሁድ «የሕግ መጻሕፍት» ከሚሏቸው ከአንዱ ከመዝሙር የሚከተለውን ጠቅሶ ነበር።

«ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፦ እኔ፦ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን ትሰድባለህ ትሉታላችሁን?»

ኢየሱስ «መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና» ብሎ የተናገረለት መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሆኑ፥ ምንጩም ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው ላለመሆኑ በግልጽ ያስረግጣል። እርግጥ መጽሐፉን በመጻፍና በማቀናበር በኩል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሥር ብዙ ሰዎች ተባብረዋል። ሆኖም ግን የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ወይም መገለጥ ከእነርሱ ሕሊና አልመነጨም። ያደረጉት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እንዲጽፉ የነገራቸውን በጽሑፍ ማስፈር ነው።

ኢየሱስ ቀደም ሲል እንዳየነው መጽሐፉ ያለው በጽሑፍ የሠፈረውን መጽሐፍ ቅዱስ በማስመልከት ነው። ያም ሆኖ ግን የእግዚአብሔር ሥልጣንና እድራጉቱ ሁሉ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቃልሏል ማለትም አይደለም። ለዚህም ቀላል ማስረጃ የሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ አልፎ አልፎ ስማቸው ያልተጠቀሰን ነቢያት በዋቢነት መጥቀሱ ነው።

ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው ዋናው ነገር፥ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊና ፍጹም እውነት ቢሆንም፥ ዘገባውን በተመለከተ በዋና ዋናዎቹ ፍሬ ነገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን ነው። መልእክቱ የታሰመው ለመላው የሰው ዘር እንደ መሆኑ ማንም ሰው አንብቦ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ የቀረበ ነው። የመጽሐፉም ይዘት ማዕከል የሰው ልጆች መንፈሳዊ ደህንነት ሲሆን፥ ይኸውም ከወደቀበት የኃጢአት ቀንበር ለማምለጥ በክርስቶስ በማመን ሊላቀቁ እንደሚችሉ በማሳየት ነው። እስቲ ከዚህ በማያያዝ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 10:35 ላይ የተናገረውን በድጋሚ እንመልከት። ይኸውም *«መጽሐፉ ሊሻር አይችልምና»* በማለት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መለኮታዊነትና ሥልጣናዊነት ያረጋግጣል። እርግጥ መጽሐፍ ቅዱስን በማስመልከት አያሌ ቅጾች በድጋፍም ሆነ በተቃውሞ ተጽፈዋል። ታዲያ ለምን የፈለጉትን ይበሉና ይጻፉ እንጂ ቃሉ የማይሻር ስለመሆኑ አንድ ጊዜ ራሱ በክርስቶስ አባባል የተደመደመ ነው።

ማናችንም እንደምናውቀው በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ሕዋውን በማቋረጥ ከጨረቃና ከሌሎችም ዓለማት ላይ ደርሰዋል። በሬዲዮ፥ በኤሌክትሮኒክስና በራዳር መሣርያዎች አካማካይነት አህጉር አቋራጭ ግንኙነቶችን በመፍጠር ላይ ናቸው። በሚሊዮን ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠሩ ርቀቶችን ከመቅጽበት በመሸፈን ላይ ይገኛሉ።

ታዲያ የእግዚአብሔር ፍጡራን የሆኑ ሰዎች እንኳን በተፈጠረላቸው አእምሮ በመታገዝ ይህን ከመሰለ የምርምር ውጤት ላይ ለመድረስ ከቻሉ፥ ፈጣሪያቸውንም ነገር ለማድረግ የማይሳነው እግዚአብሔር ከፍጡራኑ ጋር ከመናቸውም ሠው ሠራሽ መሳሪያዎች የረቀቀና የፈጠነ ግንኙነት ለማድረግ እንዴት ይሳነዋል?

ስለዚህ የዘመናችን የሳይንስ ፈጠራዎችና ግኝቶች፥ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ከጥርጣሬ ላይ ከመጣል ይልቅ በይበልጥ እውነተኛነቱን ያጎሉታል። ልባቸው ብሩህ ለሆነና አስተሳሰባቸውም ለተስተካከለ ሰዎች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ካለፈረውም በበለጠ ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር ለመገናኘት እንደማይሳነው መረዳቱ አይከብዳቸውም።

በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ስለመሆኑ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተዘግቦ እንደምናገኘው እግዚአብሔር ቃሉን በጽሑፍ እንዲያስፍሩለት የመረጣቸውን ሰዎች በረቀቀ ኃይሉ አማካይነት ይመራቸውና ይቆጣጠራቸው ነበር። ይህም ኃያል መንፈስ ቅዱስ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ በመባል ይታወቃል።

ለምሳሌ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ ጳውሎስ የሚከተለውን ተናግሯል፦ «*የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።*»

በዚህ ጥቅስ ውስጥ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት» የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ከአፉ የተነፈሳቸው ቃል በቃል እንደማለት ሲሆን ይህም ቀጥታ መንፈስ ከሚሰው ቃል ጋር ይያያዛል። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር መንፈስ የሚባሰው መንፈስ ቅዱስ፤ በዓይን ባይታይና በእጅም ባይዳሰስ ዳሩ ግን በረቀቀ ኃይሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ጸሐፊዎች ሁሉ እንደተቆጣጠረና እንደመራቸው ነው።

ይህን በሌላ አነጋገር የሚያስገነዝበን የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክትም ሆነ ትንቢት በማናቸውም መልኩ ከሰው አእምሮ ያልመነጨና ዳሩ ግን ምንግዜም በእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ነው። በመቀጠል ደግሞ ጴጥሮስ በ2ጥር 21 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተካሄደ በግልጽ ያብራራልናል፦ «*ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።*» «*ተነድተው*» የሚለው ቃል መመራትን የሚያመለክት ነው። ይህም በሌላ አነጋገር የዘመነ የሥነ - ሕዋ ሊቃውንት ወደ ሕዋው የሚልኳቸውን መንኩራኩሮች የሚበሩበትን አቅጣጫ እንደሚመሩና እንሚቆጣጠሩ ሁሉ እግዚአብሔርም መጽሐፍ ቅዱስን የሚጽፉትን ሰዎች እአምሮአቸውን በማነቃቃት አብርሆትን በመስጠት (የመንፈስ ቅዱስን) እንዲጽፉ አድርጓል። ታዲያ ሰው በምርምሩ የደረሰበትን ቁጥጥር ዓይነት እግዚአብሔርም በፍጡራኑ ላይ ሊያደርግ አይችልም ማለት ፍርደ ገምድልነት ነው።

በብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔርን አስትንፋስ በማስመልከት የቀረበ ሌላ ዘገባ እናገኛለን። ይህም የሰው ልጅ ወደ ሕዋው ከመምጠቁ አያሌ በመናት አስቀድሞ የተፈጸመ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማጤኑ አስፈላጊ ነው። በመዝሙር 12:6 ላይ ዳዊት እንደሚከተለው ይነግረናል፦ «*በምድርም ላይ እንደ ተፈተነ ለብት ጊዜ እንደተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።*»

በዚህ ላይ የምንመለከተው ሥዕላዊ ገለጻ አንጥረኞች የሚጠቀሙበትን የብር ማቅለጫ ያመለክታል። ይህ ምድጃ የሚሠራው ከሸክላ ቢሆንም ቅሉ ዳሩ ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘቱ የሚያስተላልፈው ሌላ መልዕክት አለው። የሸክላው ምድጃ የሚወክለው ለብዓዊ ተፈጥሮን ሲሆን ብሩ ደግሞ በሰዎች አማካይነት የሚተላለፈውን መለኮታዊ መልእክት ይወክላል። የብሩንም መጣራት የሚያረጋግጠው አሳት መንፈስ ቅዱስን የሚወክለው ነው። እንደዚሁም «ለብት ጊዜ» የሚሉት ቃላት፥ የእግዚአብሔርን ምሉእነትና አዘውትሮም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተመለከተው የመንፈስ ቅዱስን ፍጹምነት የሚያሳይ ነው።

አነሆም ይህ ገለጻ የሚያረጋግጥልን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሠፈሩት መልእክቶች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ እንደ መሆናቸው ፍጹማዊና፥ ከደካማው ለብዓዊ አስተሳሰብ ጠርተው የወጡና የነጠሩ መሆናቸውን ነው። ለባት ጊዜ የተጣራው ብር ፍጹማዊና የእግዚአብሔር መልእክት ተምሳሌት ነው።

ዘላለማዊና ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ

ምናልባትም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊዎች መካከል ስለእግዚአብሔር ቃል እውነተኛነትን እና ሥልጣን የዳዊትን ያህል የተረዳ ሰው አይገኝም ይሆን ይሆናል። ለምሳሌ በመዝሙር 119:89 ላይ፦ «*እቤሩ፥ ቃልህ በሰማይ ለዘለዓለም ይኖራል።*» ብሎ መናገሩ መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜ የሚገደብ ሳይሆን ለዘላለም እንደሚኖር ማስረጃ ነው። እግዚአብሔር ምድርንና ሰማይን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ያ ቃል በአርሱ ዘንድ ነበር። በዚያም በዘላለማዊነት የሚኖረው ቃል በሰው ልጆች በኩል ተላልፎ በምድራዊ የጊዜ ገደብ ሊተረጎም ቻለ። ሆኖም ይህች ምድር ካለፌች በኋላም ቢሆን፥ ያ ዘመን የማይሽረው የእግዚአብሔር ቃል ለምንጊዜም የጸና ሆኖ ይቆያል። ክርስቶስ ራሱም በማቴዎስ 24:35 ላይ ያስተላለፈው መልእክት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው።
«*ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።*»

ዳዊትም በድጋሚ በመዝሙር 119:160 ላይ የሚከተለውን ይነግረናል፦
«*የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው*
የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው።»

በተለይም ካለፉት ሁለት ምዕት ዓመታት አንስቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚካሄደው ሂስና ትችት በእጅጉ የበዛ ነው። ምንም እንኳን የዘመናውያኑ አቃቂር ብሉይንም ሆነ አዲስ ኪዳንን የሚዳስስ ቢሆንም በተለይ ትችቱ ያተኮረው ግን ቶራህና አምስቱ ብሔረ አሪት (ፔንታቱክ) ተብለው በሚታወቁት በዘፍጥረትና በአራቱ የሙሴ መጻሕፍት ላይ ነው።

ሆኖም ግን የሚገርመው፤ እነዚህ የዘመኑ ፈላስፋዎች ከመፈጠራቸው ሦስት ሺህ ዓመታት አስቀድሞ ዳዊት የሚከተሰውን ምስክርነት መስጠቱ ነው፡- «*የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው...*» ይህ ማለት እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ከኡራት ዘፍጥረት 1፡1 ጀምሮ እስከ ራዕይ የመጨረሻዋ መስመር ድረስ ያለው እውነት ነው ማለት ነው።

ይህንን ደግሞ ክርስቶስም፤ ደቀመዛሙርቱም ሆኑ አይሁዳውያን ሁሉ ቃል በቃል የሚያምኑበት ስለሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። ለምሳሌ ክርስቶስ በምድረ በዳ በሰይጣን በተፈተነበት ወቅት ሰይጣን ላቀረበለት ለሦስቱም ጥያቄዎች ክርስቶስ የሰጠው መልስ ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ «... *ተብሎ ተጽፏልና*» እያለ በመደምደም ነው። ሌላው የሚገርመው ነጥብ ደግሞ የቃሉን ሥልጣን ሰይጣን ራሱ እንኳን የማመኑ ጉዳይ ነው።

ክርስቶስ በማቴዎስ 5:17-18 ባለፈረው የተራራው ስብከት ውስጥ የሚከተለውን ተናግሯል፡- «*እኔ ሕግንና ነቢያትን ልሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። «ሕግንና ነቢያትን የሚለው ገለፃ የሚወክለው መላውን ብሉይ ኪዳን ነው። እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፤ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍምና ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።*»

አንዲት «የውጣ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዕብራይስጥ ቋንቋ የመጨረሻዋን አነስተኛ ፊደል ሲሆን ከእንግሊዝኛው የኮማ (Comma) ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለ አንዲት ነጥብ ትንሽነትም ሁላችንም የምንረዳው ነው።

ስለዚህ ክርስቶስ በዛ መልኩ መናገሩ፤ ብሉይ ኪዳንም ፍጹም ትክክለኛና ሥልጣን ያለው መሆኑን ስለሚረጋገጥ ነው። ይህንንም እቂሙን ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ ሁሉ እጠናክሮታል። ለምሳሌ በማቴዎስ 19:3-9 ውስጥ እንደምናነበው ፈሪሳውያን ስለ ጋብቻና ፍቺ ጥያቄ ባቀረቡለት ወቅት፡ በዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ በመንተራስ «... *ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው... የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?*» በማል ሌላ ጥያቄ ነበር የመለሰላቸው። «በመጀመሪያ» የሚለውን ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ የዘፍጥረት መጽሐፍን ያመለክታል።

እንደዚሁም ለዳቃውያን ስለመታን ትንሳኤ በጠየቁት ጊዜ እሁንም የመለሰላቸው በማቴዎስ 22:31-32 ላይ እንደለፈረው «*እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ፡ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን?* » በማለት በኡራት መጻሕፍት ላይ ተንተርሶ ነበር። ይህን የጠቀሰው ከዘጸአት 3:6 ቢሆንም ቃሉ የመነጨው ከሙሴ ሳይሆን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ስመሆኑ «*ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን*» በማለት አስገንዝቧቸዋል። እንግዲህ ይህ ጥቅስ የተዘገበው ከአሥራ እምስት

ክፍለ ዘመናት በፊት ቢሆንም አሁንም እንዳልተሻረ እንረዳለን። እስካሁን ለማየት እንደሞከርነው ክርስቶስ ያረጋገጠው የብሉይ መጻሕፍትን ትክክለኛነት ብቻ ሳይሆን ሥልጣን ያላቸውና የእርሱም ሕይወት ጭምር ለቀድሞዎቹ መጻሕፍት ተገዢ መሆኑንም ነው። ከልደቱ አንስቶ እስከ ሞቱና እስከ ትንሣኤው ያለው ታሪክ ሁሉ የተባለው ይፈጸም ዘንድ በሚል ሐረግ የተገለጠ አንድ ዋና የሚቆጣጠረው መመሪያ ነበር።

ለምሳሌ በኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ወቅት የነበሩት የሚከተሉት ክስተቶች የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ለመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ዘግቦአል። ክርስቶስ ከድንግል መወለዱ፤ በቤተልሔም ከተማ መወለዱ፤ ወደ ግብፅ መሰደዱ፤ በናዝሬት ስለማደጉ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባቱ፤ በአይሁዳዊያን ዘንድ ተቀባይነት ስለ አለማግኘቱ፤ በምሳሌዎች ስለ ማስተማሩ፤ ወዳጅ በነበረ ሰው አሳልፎ ስለ መሰጠቱ፤ በደቀ መዛሙርቱ ስለመካዱ፤ ያለ ምንም ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ እንዲጠላ ስለ መደረጉ፤ ከወንጀለኞች ጋር የተፈረደበት ስለ መሆኑ፤ በተጠማ ጊዜ ሆምጣጤ እንዲጠጣ ስለ መደረጉ፤ ሰውነቱ በጦር ስለ መወጋቱና የጎልቡቱ አጥንቶች ግን አለመሰበራቸው፤ ዘሃብታም ሰው መቃብር ስለ መቀበሩ፤ በሦስተኛው ቀን ከሞት ስለ መነሳቱ ሁሉ በብሉይ መጻሕፍት ትንቢት የተነገሩ ናቸው።

ይህ ዝርዝር ሁሉንም ነገሮች የሚያሟላ ባይሆንም፤ ያለ አንዳች ማወላወልና ማጋነን የክርስቶስ ሕይወት ከልደቱ እስከ ትንሣኤው ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ቁጥጥር ሥር እንደ ነበረ ያረጋግጥልናል።

ይህን መረጃ ክርስቶስ በእንደቡቱ ስለ ብሉይ ኪዳን እውነተኛነት ከተናገራቸው ጋር ስንደምረው ከአንድ መደምደሚያ ላይ ብቻ ያደርሰናል። ይኸውም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቃል በቃል የእግዚአብሔር መገለጥ ውጤቶች ናቸው የሚል ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፍጹም ትክክልና ሥልጣናዊ የሆኑ የእግዚአብሔር መገለጦች ካልሆኑ ጌታን እንደ አታላይ መቁጠር ነው።

እርስ በእርስ የማይቃረን ምሉዕና ብቁ ስለመሆኑ

አሁን ደግሞ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን በመሸጋገር የዚህንም መጽሐፍ ሥልጣን እንመለከታለን።

በተለይም ከሕሊናችን መፋቅ የሌለበት ትልቁ ቁም ነገር ክርስቶስ በዝሙት የተከሰሰችውን ሴት ከፊቱ በቀረበችበት ወቅት በመሬት ላይ ከጻፈው በስተቀር ሌላ አንድም ነገር በጽሑፍ ያላሰፈረ መሆኑን ነው።

ሆኖም ግን ደቀ መዛሙርቱን ትምህርቱንና አገልግሎቱን በማስመልከት በጽሑፍ እንዲያስፍሩትና በመላውም ዓለም እንዲያሰራጩት እንደሚከተለው አሏል፦

«ስለዚህ፥ *እነሆ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጻፎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ...*» ብሏል። «ጻፎች» የሚለው ቃል የሃይማኖታዊ ትምህርቶችን በጽሑፍ መልክ የሚያስቀምጡ ሰዎችን ያመለክታል። ይህም የሚያመለክተን ምድራዊ አገልግሎቱንና ትምህርቱን ደቀ መዛሙርቱ በጽሑፍ እንዲያስፍሩት ማዘዙ ነው።

እንደዚሁም ይህ ለትውልድ የሚተላለፈው ዘንባ ያለ ምንም ሐሰትና ነቀፋ በትክክል ስለ መስፈሩ እንዲረዳቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸዋል። «*አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው እጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።*» ዮሐንስ 14፡26)

እንግዲህ ከዚህ ሐቅ የምንረዳው አዲስ ኪዳንም እንደ ብሉይ ኪዳን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈ መሆኑን ነው። በተለይም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን በተመለከተ «*መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይና አዲስ ኪዳን) በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተጻፈ ነው*» በማለት ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል።

በዚህ እምነታቸው ሐዋርያት እጅግ የጸኑ እንደ መሆናቸው በማናቸውም አጋጣሚ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን አረጋግጠዋል። ለምሳሌ ጴጥሮስ በሁለተኛው መልእክቱ ምዕራፍ 3፡1-2 ላይ እንደሚከተለው ጽፏል፦ «*ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የምጽፍላችሁ መልዕክት ይህች ሁለተኛይቱ ናት። በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታን የመድኃኒትን ትዕዛዝ እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቡናችሁን አነቃቃለሁ።*» ከዚህ እባባል የምረዳው የብሉይ ኪዳን ነቢያት መልእክቶችና የሐዋርያት ትምሕርቶች ተነጣጥለው ሊታዩ እንደማይገባ ነው። ሁለቱም እኩል ሥልጣን ያላቸው ስለ መሆናቸው በግልጽ ለፍሯል። አሁንም ቢሆን ይኸው ሐዋርያ በዚሁ መልእክቱ ቁጥር 15 እና 16 ላይ የሚቀጥለውን መመሪያ አክሎበታል።

«*የጌታችንም ትዕግስት መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ። እንዲሁም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፥ በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ። በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ለሌሎች መጻሕፍት እንደሚያደርጉ ለነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።*»

ጴጥሮስ በዚህ መልእክቱ አማካይነት «እነዚህን ደግሞ በገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ» ብሎ በመግለጽ የጳውሎስ ትምህርቶችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለ መሆናቸው በማያወላውል መልኩ አረጋግጧል። እርግጥ ጳውሎስ ኢየሱስን

በምድራዊ ሕይወቱ አልተገናኘውም ነበር። ሆኖም ግን ስለ እርሱ የሰጠው ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠለት እንደሆነ እንረዳለን።

እንደዚሁ ሁሉ ወንጌላዊው ሉቃስ ከሐዋርያት አንዱ እንዳልሆነ የታወቀ ነበር። ሆኖም ግን በወንጌሉ ምዕራፍ 1፡3 ላይ ባስፈረው «*በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ*» በማለት ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ያለውን ብቃት አሳይቷል። «ከመጀመሪያ ተከትዬ» የሚለው የግሪኩ ቃል ትርጉም «ከላይ ከሰማይ» ማለት ነው።

ስለዚህ ብሉይና አዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ በምንመረምርበት ጊዜ የሁለቱንም መጻሕፍት ትክክለኛነትና ሥልጣን ለመጠራጠር ምንም ዕድል አይኖረንም። ሁለቱም የተጻፉት ከደካማው ሰብዓዊ አስተሳሰብ መንጭተው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ነው። በመሆኑም ሁለቱም መጻሕፍት እርስ በእርስ የማይጋጩ፥ ሙሉና ቡቂ ናቸው። እንደዚሁም ቅዱሳት መጻሕፍት ከሥነ አመክኖአዊ (ሎጂክ) ሆነ ከሳይንሳዊ አስተሳሰብ የሚቃረኑበት አንድም ነጥብ አይኖራቸውም።

4

የእግዚአብሔር ቃል አሠራር ቅደም ተከተሎች

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ አምነውበት በሚቀበሉት ዘንድ ስለሚያስገኛቸው ተጨባጭ ለውጦች ወይም ውጤቶች ነው።

በዕብራውያን 4:12 ላይ የሚከተለውን እናገኛለን፦ «... *የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም ሁለትም እፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው..*» ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቃል ብርታትና ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን የፈለገውን ለማድረግ ብቃትና ችሎታ አንዲሁም ኃይል ያለው መሆኑን ነው።

ከዚህ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በዮሐንስ 6:63 ላይ «... *እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው*» የሚል አገላለጽ እናገኛለን።

በተጨማሪም በ1ኛ ተሰሎንቄ 2:13 ላይ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለሚገኙት ክርስቲያኖች እንዲህ በማለት ጽፏል፦

«*ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ በእውነት እንዳለ በአናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።*»

ከዚህ የምንማረው የእግዚአብሔር ቃል እንደ ቀልድ ተነግሮ የሚረሳ ወይም ተጽፎ የሚዘነጋ አለመሆኑን ነው። ከዚህ በተቃራኒ የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትም መንፈስም ነው። በሚያምኑበት ዘንድ ሕያውና፥ ኃያል፥ ተግባራዊና ተጨባጭ በመሆን ይሠራል።

ለቃሉ የሚኖረን ምላሽ ወሳኝነት

ያም ሆኖ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ እንደሚያደርግልን ቃሉ ውጤታማ የሚሆንበት ደረጃ በግልጽ ምላሻችን እንደሚወሰን ነው። በዚህም ምክንያት ነው ያዕቆብ በመልእክቱ ምዕራፍ 1:21 ላይ እንደሚከተለው የጻፈው፦ «*ስለዚህ ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፥ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።*»

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነፍሳችን በመግባት የአዳኝነት ተልእኮውን ከማሳካቱ በፊት በበኩላችንም ልናሟላው የሚገባ ግዴታ አለ።

ያዕቆብም ይህን በማስመልከት ከሁለት ጥፋቶች ራሳችንን እንድናነሳ ያሳስበናል። «ርኩሰት» እና «ክፋት» እስከተጠናወቱን ድረስ ይብሱኑ ወደ ከባድ ጥፋትና ዝቅጠት ያመሩናል እንጂ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡን አይደሉም።

ለክፋት አንዱ ምንጩ አለመታዘዝ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሕጻን ልጅ አድርግ የምንለውን ትቶ ወደ ጥፋት ተግባራት ካመራ «ክፉ ልጅ!» ማለት እንዘልፈዋለን። ስለዚህም መሰሉ አድራጎት አጥፊነት በማንሳት ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 9:20 ላይ እንደሚከተለው አስጠንቅቋል።
«*ነገር ግን አንተ ሰው ሆይ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ*»

እንደገናም ይህን መሰሉ አድራጎት በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ መሆኑ ኢዮብን በሚከተሉት ቃላት እንደተናገረው እንመለከታለን፦ «*በውኑ የሚከራከር ሰው ሁሉን ከሚችል ጋር ይከራከራልን? ክእግዚአብሔር ጋር የሚዋቀስ እርሱ ይመልስለት*» ኢዮብ 40:2

ይህ ክርክርና ተሰይቶ የማይታይ ተግባር እንደ መሆኑ በእግዚአብሔርና በፍቅሩ መካከል ሊኖር የሚገባውን የፍቅር ግንኙነት ያሻክረዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ «የርኩሰትን» እና «የክፋትን» ተቃራኒ «ገርነት» እና «ትህትና» እንደሆነ ያዕቆብ ያስገነዝባል። ትህትና የጭምትነትን፥ የየዋሕነትን፥ የታዛዥነትን፥ የትዕግስትን፥ የታማኝነትን፥ በአጠቃላይም የልብና

የአእምሮ ንጽሕናን ባሕርያት በሙሉ አካቶ የያዘ ቃል ነው። ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ «ፈሪሃ እግዚአብሔር» ይባላል። የእግዚአብሔር ቃል በማክበርና በትሕትናም ለመፈጸም መነሳቱ የሚከተሉትን በረከቶች እንደሚያስገኝ በመዝሙር 25፥8:9:12 እና 14 ላይ ሠፍሮ እንመለከታለን።

«እግዚአብሔር ቸር ቅንም ነው፤ ስለዚህ ኃጢአተኞችን በመንገድ ይመራቸዋል፥ ገሮችን በፍርድ ይመራል ለገሮችም መንገድን ያስተምራቸዋል፥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማነው? በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል። እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው፥ ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል።
ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የእግዚአብሔርን ምሪት በረከት ለማግኘት ወሳኙ፥ በቃሉ ውስጥ እንደ ታዘዘው ገርነትና እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ለዎች ዘንድ የተለያየ ስሜት በማሳደር በዚያው መጠን የተለያየ ውጤት ያስገኛል። ስለዚህም ነው በዕብራውያን 4:12 ላይ እንደለፈረው የእግዚአብሔር ቃል «ሕያውና» «የሚሠራ» ብቻ ሳይሆን የለዎችንም የልብ አዝማሚያና የአስተሳሰብ አቅጣጫ ጭምር ለመመርመር ይችላል የተባለው። የእግዚአብሔር ቃል ማናቸውንም በውስጣችን የተቋጠረውን ምሥጢር በማፍረጥረጥ ገሃድ ያወጣዋል። በዚህም ማንነታችንን ያረጋግጣል።

ይህን ይበልጥ ተአማኒነት ባለው መልኩ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1:18 ላይ እንደሚከተለው ገልጾታል፦
«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።»

የእግዚአብሔር ቃል አንድ እንደ መሆኑ ለሁሉም የሚያስተላልፈው መልእክት ተመሳሳይ ነው። ሆኖም ግን ልዩነት የሚያስከትለው የእኛ የአድማጮቹ ሁኔታ ወይም ምላሽ ነው። በጥቅሉ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር ቃል ለጥፋት የሚያዳርሣቸው፥ ሌሎቹን ለደኅንነት የሚያበቃቸው ይሆናል።

ይህም በይበልጥ የተብራራው፥ የእግዚአብሔር ቃል በዕብራውያን 4:12 ላይ እንዳለፈረው *«ሁለትም አፍ ካለው ለይፍ ሁለ ይልቅ የተሳለ»* በሚለው መልኩ በመገለጹ ሲሆን፥ ያለምንም ጥርጥር እንደ ተቀባዩ ምላሽ አንድም ወደ ፍርድ አለበለዚያም ወደ ደህንነት የሚያመራ ይሆናል። ክርስቶስም ስለዚህ በማቴዎስ 10:34-35 ላይ እንደሚከተለው ብሏል፦
«በምድር ላይ ለሳምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሊይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ለውን ከአባቱ ሴት ልጅንም ከእናትዋ ምራትንም ለአማትዋ እለይይ ዘንድ መጥቻለሁና»

ክርስቶስ በምድር ላይ ሊልከው የተዘጋጀው ሰይፍ በዮሐንስ ራዕይ 1:16 ላይ የተጠቀሰውና ከአፉ የሚወጣው በሁለት ወገን የተሳለ «ስለታም ሰይፍ» ያለው ነው። ይህ ሰይፍ በምድር ላይ በሚያርፍበት ለዓት ለቃሉ እንደሚኖራቸው ምላሽ የአንድን ቤተሰብ አባላት እንኳን ሳይቀር የሚከፋፍል ይሆናል።

እምነት

እስቲ ከዚህ በመቀጠል የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ልባቸው በንጹሕ ሕሊናና በትሕትና አምነው ስለሚቀበሉት ለዎችና ስለሚያስገኝላቸውም ውጤት እንመልከት።

የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል የመጀመሪያው ውጤት እምነት ይሆናል። ይህም በሮሜ 10:17 ላይ እንደሚከተለው ተብራርቷል፦
«እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።»

በዚህ መንፈሳዊ ሂደት ውስጥ ሊሟሉ የሚገባቸው ሦስት ነገሮች አሉ። በቅድሚያ የእግዚአብሔር ቃል፥ ሁለተኛው ቃሉን ማዳመጥና ሦስተኛው እምነት ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ ሊነገር ሊደመጥ ወይም መጽሐፉ ሊነበብ ይገባል። ይህም ስለ መልእክቱ በይበልጥ የመረዳት ጉጉት ከማሳደሩም በላይ በቃሉ ወደ መጎልበት ያመራል። ከዚያም ወደ መጨረሻው ደረጃ ማለትም ወደ እምነት ያመራል።

የምንሰማው ቃል ከነፍሳችን ጋር አስኪዋሃድ ጥቂት ጊዜም ቢሆን መፍጀቱ አይቀርም። አለበለዚያ ግን የተጠናከረ እምነት ሳይኖረን ይችላል። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ እንደምንመለከተው የብዙ ስመ ክርስቲያኖች ችግር ቃሉን ለማጥናትና ለመረዳት በቂ ጊዜ ባለመውሰዳቸው ነው። በቤተክርስቲያናትም ሆነ በየግል ቤታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ለመከተል የሚሞክሩት ለማለመለልና የግብር ይውጣ ያህል ስለሆነ በእምነት ለመታነጽ አይችሉም። በዚህ አጋጣሚ እምነት ስንል መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት ብሔሚማኖን፥ በአለቃችን፥ በፖለቲካ ድርጅታችንና በጋዜጣ ወዘተ... ካለን እምነት ለይተን መመልከት ይኖርብናል። መንፈሳዊ እምነት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚኖረን በራሳችንም ምርጫ ሳይሆን ዳሩ ግን በቃሉ መተማመን የምናገኘው ስወደፊቱም የምናነሳስተው ነው። ለምሳሌ በ1ኛ ዜና መዋዕል 17:23 ላይ ተገልጾ የምናገኘው የዳዊት በእግዚአብሔር ላይ የነበረው መንፈሳዊ እምነት ለሁላችንም ጥሩ አርአያ ሊሆን ይችላል።
«አሁንም፣ አቤቱ ስለ ባርያህና ስለቤቱ የተናገርኸው ለዘላለም የጸና ይሁን ፣ እንደተናገርህ አድርግ።»

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በእነዚህ ሁለት ቃላት ይገለጻል «እንደተናገርህም አድርግ።» የዚህኑ ዓይነት የጸና እምነት መግለጫ የምናገኘው

ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ እንደምትጸንስ መልአኩ ገብርኤል ከተናገራት በሥራት በኋላ ከሰጠችው ምላሽ ነው።

«እነሆኝ የጌታ ባርያ አንደ ቃልህ ይሁንልኝ» ሉቃስ 1:38 ይህ «አንደ ቃልህ ይሁንልኝ» የሚለው የአምነት መግለጫ በሁላችንም ልቦና ሊሰፍንና ያለማወላወል ልንመራበት የሚገባ ነው። ማርያም በሰማችው ቃል ማመን ብቻ ሳይሆን ያ ቃል ይሚላ ዘንድ ወደ ቃሉ ባለቤት በአምነት ተማጸነች።

አንግዲህ በመጠኑም ቢሆን ከላይ እንደተመለከትነው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለሚኖር ጤናማ ግንኙነት መሰረቱ አምነት ነው። ይህን በበለጠ የሚያጠናክርልን ዕብራውያን 11:6 ይሆናል፦

«ያለ አምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚየደርስ እግዚአብሔር አንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።»

ከዚህ የምንመለተው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ የመጀመሪያ ምላሹ አምነት አንደሆነ ነው። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ (የሚመጣ) አስቀድሞ ማመን አለበት።

አዲስ (ዳግም) ልደት

ከአምነት በመነሰተል የምንቀዳጀው ልምምድ አዲስ (ዳግም) ልደት ሲሆን ይህም በነፍሳችን ውስጥ ጠልቆ የሠረጸው የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ውጤት ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ያን ያህል በጎነትን አንደሚያደርግ ያዕቆብ በመልእክቱ 1:18 ላይ አንደሚከተለው አረጋግጧል። «ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አዲስ ዓይነት መንፈሳዊ ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በነፍሱ ውስጥ ይተከላል። ይህንንም በአምነት ይቀበላል። ስለዚህም ነው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ 1:23 ላይ ክርስቲያኖችን በሚከተለው መልክ የገለፀው፦

«ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።»

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮም አንደረጋገጠው የአንድን ፍሬ ምንነት የሚወስነው ዘሩ ነው። የስንዴ ዘር የስንዴ ፍሬ ሊያስገኝ፤ የብርቱካንም ዘር ብርቱካን ብቻ ያስገኛል።

ዳግም ልደትም ቢሆን ወሳኙ ይህ ሕግ ነው። ዘሩ ምንጊዜም መበስበስን የማያውቀው የማይሻርና የማይለወጠው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቃል ነው። ይህን የመሰለው ዘር በአምነት አማካይነት ልብ ውስጥ እስከተዘራ ድረስ የሚያስገኘውም ፍሬ እንደ ዘሩ የማይፈርስና የማይበሰብስ፤ ዘላለማዊና መለኮታዊ ይሆናል። እንደ እውነቱ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ዳግመኛ

የተወለደው ክርስቲያን የሚያገኘው ሕይወት የእግዚአብሔርን ሕይወት ይሆናል። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ዮሐንስ በ1ኛ መልእክቱ ምዕራፍ 3:9 ላይ እንደሚከተለው የጻፈው፦

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አይደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።»

ዮሐንስ የሚያመለክተን ክርስቲያኑ አዲስ ሕይወት በመቀዳጀቱ ሳቢያ ያን ያህል ድል አድራጊ እንደሚሆን ነው። የእግዚአብሔር ቃል ዘር ውጤት መሆኑ ያንን ለው ማንም ምንም ሊያሸንፈው አይችልም። መፍረስና መበስበስም ስለማይበግረው ያ ሕይወት ንጹሕና ቅዱስ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ለምንጊዜውም ኃጢአት ያለ መሥራት ዋስትና አለው ማለት አይደለም። ማንኛውም ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አዲስ ባሕርይን ይላበሳል። በኤፌሶን መልእክት 4:22-24 ላይ ጳውሎስ «አዲሱ ሰው» በማለት ሲጠራው ስለዚህ ያልበቃውን ለው ግን «አሮጌው ሰው» ብሎታል።

በእነዚህ በሁለቱ ዓይነት ለዎች መካከል ፍጹም ሊዛመድ የማይችል ልዩነት አለ። «አዲሱ ለው» ጻድቅና ቅዱስ ሲሆን «አሮጌው ሰው» ግን የከፋና የረከሰ ነው። ይህም ከአዳም ኃጢአተኛነት ከወረሰው ባህርይ ባለመላቀቁ የተነሣ ክፋትን ለማድረግ በመፈለጉ ነው።

በአውነተኛው ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ግን «አሮጌው ሰው» ተደምሰሶ «በአዲሱ ለው» በመተካቱ ለላምና ፍቅርን ጽድቅንና ድል አድራጊነትን ይቀዳጃል። ሆኖም ግን ክርስቲያኑ የሚያመነታ ሆኖ ራሱን «ከአሮጌው ለው» ቁጥጥር ሥር አስካዋለው ድረስ ያለ ምንም አማራጭ የሚኖረው ዕድል ለውድቀትና ለኃጢአት መጋለጥ ይሆናል።

ሁለቱን ዓይነት ለዎች በሚከተለው መልኩ በአጭሩ ለማነጻጸር ይቻላል፦ ከማይለወጠውና ከማይበሰብሰው የእግዚአብሔር ቃል ዳግመኛ የተወለደ አውነተኛ ክርስቲያን መላ ሕይወቱን በኃጢአት ላይ ድል አድራጊነትን እንደተቀዳጀ ይኖራል። ዳግም ያልተወለደው ግን በኃጢአት እንደተጨማለቀ አስነ ዕለተ ሞቱ ይደርሳል። ለወደቀውና ለተበላሸው ለራሱ ባህርይ ባርያ ሆኖ ይቀራል።

መንፈሳዊ ምግብ

ቀደም ሲል የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ መቀበል ነፍሳችንን ሙሉ በሙሉ በመለወጥ ለአዲስ ሕይወት እንደሚያበቃን ተመልክተናል። ይኸውም፦ ያ አዲስ ሕይወት በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ደቂቃ አንስቶ ተስማሚ የሆነ ምግብ ማግኘት የሚያሻው የመሆኑ እውነታ ነው። ለምሳሌ አንድ ሕፃን

ሊወለድ ጤነኛ ቢሆንም፥ ሕይወቱን ለማቆየት ወዲያውኑ ተመጣጣኝ ምግብ ሊሰጠው ያሻል። አሰበሰዚያ ግን ከስቶና መንምኖ ይሞታል።

በመንፈሳዊው ሕይወትም ቢሆን የሚያጋጥመን ሥዕል ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ ሰው ዳግመኛ ከተወለደበት ደቂቃ አንስቶ አዲስ የተፈጠረው መንፈሳዊ ባሕርይ መንፈሳዊ ምግብ ያሻዋል። ለዚህም ተስማሚ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ እግዚአብሔር ራሱ በቃሉ አማካይነት አዘጋጅቶ ለግሶናል። ያም ምግብ እንደ አድገት ደረጃችን ቀስ በቀስ እየጨመረ የሚሄድ እንጂ በአንድ ጊዜ ወይም ወዲያውኑ ተጠቃልሎ የሚወሰድ አይደለም።

በዚህ የዕድገት ሂደታችን ውስጥ በቅድሚያ ልንለማመደው ስለሚገባው መንፈሳዊ ምግብ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ምዕራፍ 2፡1-3 ላይ እንደሚከተለው ገልጾልናል፦

«እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ ለመዳን በአርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕጻናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።»

ለአንድ ሕጻን ልጅ ከተወለደ በኋላ በሕይወት ለመቆየት የግድ የወላጅ ወይም የላም ወተት የሚያሻውን ያህል፥ በእምነት ዳግመኛ ስተወለደውም ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ ለመቆየትና ለማደግ መንፈሳዊ ወተት ያስፈልገዋል። እንደዚሁም ሕጻኑ የሚወሰደው ወተት ለተህዋስያን ተጋልጦ በሽታ እንዳያስከትልበት ጥንቃቄ የመሻቱን ያህል፥ አዲሱም ክርስቲያን የሚመገበው መንፈሳዊ ወተት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በሆነ የሐሰተኛና የመናፍቃን ትምህርት እንዳይበረዝ ተመሳሳይ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

ይህም እስከሆነ ድረስ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳስገነዘበን ሁሉ የክርስቲያኑ ሕይወት በተንኰል፣ በግብዝነት፥ በቅንዓትና በሐሜት ከመበከል የጸዳ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ የአዲሱ ሰውነት ባህሪያት ሳይሆኑ የአሮጌው ሰውነት መለያ ጠባያት ስለሆኑ ከልባችን ተጠራርገው ሊወጡና በቅድስናና በንጹሕ ልብ ልንኖር ይገባል። ይህን እስካሳየን ድረስ እግዚአብሔር ቀስ በቀስ በእምነታችን እንድንበስግና እንድንጎለብት ሁኔታዎችን ያመቻችልናል። ለዚህም ታላቅ መጽናኛ የሚሆነን፥ ሰይጣን ክርስቶስን በመፈታተን ድንጋዩን ወደ ዳቦ እንዲለውጠው በጠየቀው ወቅት የሰጠውን መልስ ከልብ ማጤኑ ነው። *«ሰውም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፏል አለው።»* ማቴዎስ 4፡4

እዚህ ላይ ክርስቶስ ግልጽ ያደረገው ነገር ለምድራዊ ሕይወት ዳቦ የሚያሻውን ያህል ለመንፈሳዊ ደህንነታችንም ወሳኙ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ነው። ብቸኛው የነፍሳችን ምግብና መጠጥ ይኸው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ክርስቶስም እበክሮ እንዳስገነዘበው «ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ» የሚለው መላውን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያመለክት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማጤኑ እጅግ ወሳኝ ነው።

ጆርጅ ሙለር የተባለው ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስን በዓመት ውስጥ እጅግ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በማንበብ የታወቀ ሰው ነው። የዚህ ሰው እምነት ታላቅና አገልግሎቱም ፍሬያማ መሆኑ የዚህ ውጤት ነው። ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን መጽሐፍ ቅዱሳችንን አዘውትረን የምንገልጠው? አስቲ እንዲያው ስንቶቻችን ነን የመጽሐፍ ቅዱሳችንን መጻሕፍት ቅደም ተከተል የምናውቀው? ለመሆኑ ከደቂቀ ነቢያት መካከል የስንቶቹን መጻሕፍት በዓይናችን እንኳን ገልጠን አይተነው ይሆን? እንኳንስ እነ ነህምያን ሊያጠኑና መልዕክታቸውን ሊረዱ ቀርቶ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገኝም የማያውቁ ክርስቲያኖች ሞልተዋል። እነዚህ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕጻንነት ለዘላለም ቢኖሩ የሚያስደንቅ አይደለም። እነርሱ ተገቢ ባልሆነ አመጋገብ ለሚመጣ የእድገት ዝግመት አሳዛኝ ምሳሌዎች ናቸው።

ለመኖር ዳቦና ወተት ብቻ ላይሆን የእግዚአብሔርንም ቃል በየዕለቱ መመገብ ያሻናል። ይህንንም በማለመልከት በዕብራውያን መልእክት ውስጥ በአይሁዳውያን ላይ የተለነዘረውን ወቀሳ እኛም ልንማርበትና ልንታረምበት ይገባል። አይሁዳውያን ለዘመናት ቅዱሳት መጻሕፍት ቢኖሯቸውም በዚሁም ቢኩራሩም ዳሩ ግን በመንፈስ ጨቅላ ነበሩ። ስለዚህም ነው በሚከተለው መልኩ ሰውቀሳ የተጋሰጡት።

«ብዙዘው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነት ትምህርትን እንዲያስተምራችሁ አንደገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።» ዕብራውያን 5፡12-14

ይህ ወቀሳ በዛሬውስ ጊዜ የሚገኙትን ዕልፍ አዕላፋት የለም ክርስቲያኖች አይመለከት ይሆን? በየቤታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ቢኖራቸውም፥ አዘውትረውም ከቤተክርስቲያን የማይሰዩ ቢሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል ያን ያህል ያውቁት ይሆን? ስለ ክርስቶስ ለማያውቀው አረማዊ ለመመስከር ወይንም ;ነጢአተኛውን ወደ ንስሐ ለመምራት የሞከሩበት ጊዜ ይኖራልን? በዘመናችን ክርስቲያን አባልነታቸው ብዙ ዘመናት ያሳለፉ ይሁኑ እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከጨቅላ ሕጻን ተሰይተው ሊታዩ ይችላሉ? አዎን! በክርስቲያናዊ ዕውቀታቸውና ተግባራቸው በልጽገው በመገኘት ፋንታ አሁንም እንደ ሕጻን ወተት በመጋት ላይ ናቸው!

እነሆ በዚህ ደረጃ ተተግነው ሞቆም እንደማይገባቸው በዕብራውያን ላይ የሠፈረው መልእክት በግልጽ ያስገነዝባቸዋል። ከመንፈሳዊ ጨቅላነት የመላቀቂያው ቀላሉ ዘዴ እአምሮን ለማሠራት ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት ነው። የተለተካከለ መርሐ ግብር በመንደፍ የእግዚአብሔርን ቃል በዕቅድና ያለማቋረጥ ማጥናት በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሳልና የበለጸገን ሊያደርገን ይችላል።

5

የእግዚአብሔር ቃል የሚያቀዳጃቸው አካላዊና መንፈሳዊ ተሐድሶዎች

ቀደም ባለው ጥናታችን ስለ ሦስት መንፈሳዊ ለውጦች ተነጋግረናል። የእግዚአብሔር ቃል እምነትን እንደሚያስገኝ፣ እምነትም የእግዚአብሔርን ቃል በመቀበልና ትእዛዛቱንም በመፈጸም እንደሚመለክር አውስተናል።

ሁለተኛ፦ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ንጹሕ ዘር በመሆን ለአዲስ ወይም ለዳግመኛ ልደት እንደሚያበቃ፣ ከዚህም መንፈሳዊ ለውጥ የተነሣ አማኙ «አዲስ ሰው» በመባል የመጠራት ዕድል እንደሚያገኝ አውግተናል።

ሦስተኛ፦ የእግዚአብሔር ቃል ለመንፈሳዊ ዕድገታችን ወሳኝና አስፈላጊ በመሆኑ ምንጊዜም ልንመገበውና ጤናማና ብርቱ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለማጎልበት ዕለት ዕለት እንዳይለየን ስለማስፈለጉ፣ በዝርዝር አጥንተናል።

ሥጋዊ ፈውስ

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የምንመለከተው ለመንፈሳዊ ሕይወት ግንባታ፣ ለነፍሳችን ጥንካሬና ብርታት የእግዚአብሔር ቃል የማስፈለጉን ያህል ለአካላዊ ደህንነታችንና ጤንነታችን በዚያው መጠን እንደሚያሻን ነው። ይህንን ለማብራራት በቅድሚያ መዝሙር 107:17-20 እንመልከት፦

«ስለ ዓመጻቸው ሰነፉ፣ ስለ ኃጢአታቸውም ተቸገሩ። ሰውነታቸው መብልን ሁሉ ተጸየፈች ወደሞትም ደጆች ቀረቡ። በተጨነቁም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፣ ከመከራቸውም አዳናቸው። ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፣ ከጥፋታቸውም አዳናቸው።»

ዳዊት በዚህ መዝሙር ውስጥ የሚያመለክተን ሰዎች ከኃጢአታቸው የተነሳ ያን ያህል በመዳከማቸው ምግብ እንኳን ለመውደድ አለመቻላቸውን ነው። በዚህ መሰሉ ተስፋ ቢስ ሁኔታ ውስጥ ወድቀው ቢገኙም ወደ እግዚአብሔር እንዲያድናቸው በመማጸናቸው ሲፈውሳቸውና ከአካላዊ ጉስቁልናቸው ሲያሳርፋቸው እናያለን። ለመሆኑ ይህን የመዳን ጸጋውን ለሰዎች እንዲደርስ የሚያደርገው በምን ዘዴ ይሆን? በእንድ መንገድ ብቻ ሲሆን ያም በቃሉ አማካይነት ነው። ይህንንም የሚያረጋግጥልን አሁንም በዚሁ መዝሙር ውስጥ የምናገኘው ጥቅስ ነው፦
«ቃሉን ላከ ፈወሳቸው ከጥፋታቸውም አዳናቸው።»

በተሰይም በምሳሌ 4:20-22 ላይ ከሰፈሩት ሦስት ጥቅሶች የምንረዳው ተጨማሪ ሐቅ፣ የእግዚአብሔር የፈውስ መድኃኒቶች በጥቅሶቹ አማካይነት ቁልጭ ብለው መቅረባቸውን ነው። እነዚያ ቃላት በምድር ከሚገኝ ከማናቸውም ለው ለራሽ ወይም ተፈጥሮአዊ መድኃኒቶች ይልቅ ፈዋሽነታቸው የማያጠራጥር ነው።

ዓለማዊ ሐኪም እንኳን ቢሆን ስለሚያዘው መድኃኒት እወሰለዱ እንዲት እንደሆነ፣ በየቀኑ ባለማቋረጥ መወሰድ እንዳለበት፣ ሰንት ጊዜ መደጋገም እንደሚኖርበት... ወዘተ በጽሑፍ መመሪያ ይሰጥበታል። እንግዲህ እግዚአብሔርም ለእኛ የሚሰጠን መድኃኒት በተመሰሳይ ሁኔታ መመሪያ የታከለበትና ሥርዓት ባለው መንገድ የሚወሰድ መድኃኒት እንጂ እኛ በየግላችን እንዳሰኘን የምናነሰና የምንጥለው አይደለም።

ለመሆኑ እነዚህ መመሪያዎች ምን የሚሉ ይሆኑ? መመሪያዎቹ አራት ሲሆኑ የሚከተሉትን ትእዛዛት ያቀፉ ናቸው፦

1. «ንግግሬን አድምጥ»
2. «ጆሮህን አዘንብል»
3. «ከዓይንህ አታርቃት»
4. «በልብህም ውስጥ ጠብቃት»

አሁን እነዚህን ትእዛዛት ጠለቅ ባለ መልኩ እንመልከታቸው።

የመጀመሪያው መመሪያ «ንግግሬን አድምጥ» የሚል ነው። ይህን ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ የሚኖርብን በፍጹም ተመስጦና በጥንቃቄ መሆን እለበት ማለት ነው። ቃላቱ ያዘሉትን መልእክት በግልጽ ልንረዳውና ወደ ውስጣችንም ሰርጾ እንዲገባ ልንፈቅድለት ይገባል። እኛ ግን ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል የምናነበው ሐሳባችንን ሳናሰባስብ በተምታታ አእምሮ ነው። ኢየሱስ እንዳለው ግማሹ አእምሮአችን «በምድራዊ ነገሮች» ላይ

ሊያተኩር፤ የተቀረው ክፍል ብቻ ነው ምንባቡን የሚከታተለው። ምናልባትም በየዕለቱ ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ ሳይሆን ከአንድም ሁለት ምዕራፎች እናነብ ይሆናል። ሆኖም ግን ሐሳባችን በያለበት ስለሚባክን አንድም ግንዛቤ ሳይኖረን ጊዜያችንን በከንቱ እናሳልፈዋለን።

ታዲያ ለቃሉ ያለን የመከታተል ብቃት በዚህ መልኩ እስከተወሰነ፤ የእግዚአብሔር ቃል ሊያስገኝልን የሚገባው ፈውስ ውጤት አልባ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ሰዓት ኢየሱስ ስለ ጸሎት አቀራረበባችን እንደመከረን ሁሉ ፍጹም ተገልለንና በራችንን ዘግተን መሆን አለበት። ይህም ማለት ግንኙነታችን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ እንጂ ከምድራዊ ነገሮች ጋር መሆን የለበትም ማለት ነው።

ሁለተኛው መመሪያ «ጆሮህን አዘንብል» የሚል ነው። በመሠረቱ ይህ ትዕዛዝ በቅድሚያ ታዛዥነትንና ትህትናን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ሊያስተምረን የሚፈልገውን ለማዳመጥና ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለብን። ለምሳሌ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከግብጽ ቢያወጣቸውም እነርሱ ግን ትእዛዛቱን ላለመቀበል ዓምፀው ነበር። ከዚህም የተነሳ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት ለአርባ ዓመታት ያህል በምድረ በዳ ተንከራትተዋል። ታዲያ በዚያን ወቅት የፈጸሙትን ጥፋቶች በማስመልከት በመዝሙር 78:41 ላይ፦ «*እግዚአብሔርንም ፈተኑት፥ የእስራኤልንም ቅዱስ አሳዘኑት*» በሚል መልኩ ተወቅሰዋል። እግዚአብሔር ብዙ ሊያደርግላቸው ይፍቀድ እንጂ እስራኤላውያን ግን እምነት በማጣታቸው የእስራኤልን ቅዱስ ወሰኑት። በአሁንም ጊዜ ቢሆን ብዙዎች ከርስቲያኖች ከዚህ መሰሉ ስሕተት ላይ ሊወድቁ ይታያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በስፈሩት የእግዚአብሔር ቃላት ከመታመንና ከመመራት ይልቅ ክብርና ዝናን በሚሹ የቤተክርስቲያን መሪዎች አስተምህሮ በመማረክ፤ ወይም ለሐሰተኞችና ለመናፍቃን ትምህርት ጆሮአቸውን በመስጠት ከትክክለኛው መስመር በመራቅ ሲጓዙ ይታያል። ኢየሱስም ቢሆን በዘመኑ የነበሩትን የኃይማኖት መሪዎች ግብዝነት በማጤን እንደሚከተለው ወቅሷቸው ነበር፦

«.... ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ። ... የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት አያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።» ማቴዎስ 15:6 እና 9

ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስም በተመሳሳይ ሁኔታ ለአይሁድ ወገኖችና ልማዶች ተገዢ ነበር። ሆኖም ግን በደማስቆ መንገድ ላይ ክርስቶስ ከተገለጠለት በኋላ ከእነዚህ መሰሎች አሳሳች ትምህርቶችና ወጥመዶች ተገልሎ ነበር። በቆራጥነቱም በመተማመኑ በሮሜ መልእክቱ 3:4 ላይ እንደሚከተለው መስክሯል፦ «... *ለው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ይሁን።*» እኛም እንደ ጳውሎስ በረከትን የምንሻ ከሆነ፤ እግዚአብሔር ያዘዘንን ልንፈጽም፤ የሚጠላውን ልንጠላ ይገባል።

ሦስተኛው መመሪያ «ከዓይንህ አታርቃት» የሚል ሲሆን፤ ማራቅ የማይገባንም የእግዚአብሔርን ቃል ስለመሆኑ መረዳት ያሻል። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ልንረዳው ወይም ልንመስከተው ይገባል። በተሳሳተ መልኩ ማየቱ ግን ከውሸጉብር ላይ ይጥላል። ይህን በበለጠ የሚያብራራልን ወንጌላዊው ስሚዝ ዊግልስወርዝ በአንድ ወቅት፤ «የብዙ ክርስቲያኖች ችግር ዓይነ ሽውራራ ከመሆናቸው ላይ ነው። በአንዱ ዓይናቸው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ሊያነቡ በሌላው ዓይናቸው ግን የዓለማዊውን ነገር ይቃኛሉ።» በማለት የተናገረው ነው።

በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት አካላዊ ፈውስን ለመቀዳጀት ሁለቱንም ዓይኖቻችንን በማጥራትና በማስተካከል በእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ላይ ልናተኩር ይገባል። በክርስቲያኖች ዘንድ አዘውትሮ ሊፈጸም የሚታየው ስሕተት ፈውስ ባላገኙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ምክንያት ከእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ዘወር ማለታቸው ነው። ይህን በማድረጋቸው የራሳቸውም እምነት ያናወጣል። መለኮቲዊውን ፈውስም ለመቀበል ሳይችሉ ይቀራሉ። ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ 1:6-8 ላይ የሚከተለውን ምክርና ማስጠንቀቂያ ይለግሰናል፦ «... *የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው*»

ይህ ዓይነት ፈተና በሚመጣበት ወቅት የሚከተለውን የዘዳግም 29:29 ጥቅስ ማስታወስ ይጠቅማል፦

«ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።»

አንዳንድ ክርስቲያኖች ለምን አካላዊ ፈውስ እንደማያገኙ ምሥጢር ሆኖ ይቀራል። ምክንያቱንም የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሆኖም ግን እኛ ለምን እንደዘያ ሆነ ብለን ልንመራመር ወይም ምሥጢሩ ለምን አልተገለጠልንም ብለን በእግዚአብሔር ላይ ልናኮርፍ አይገባም። ይልቁንስ ኀኛ ማተኮር ያለብን በግልጽ ልንረዳቸውና እርግጠኛ ልንሆንባቸው በምንችለው ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆን አለበት። እነዚህም እግዚአብሔር ለእኛም ሆነ ለልጅ ልጆቻችን እንሚፈጽምልን ቃል የገባልን የተስፋ ቃሎች ናቸው። በእርሱም እንደ መተማመናችን የተስፋ ቃሎቹን ተፈጻሚነት በሙሉ ልብ መጠበቅ፤ የምንጊዜም መብታችን ነው። እኛም «የሕጉን ቃሎች እናደርግ ዘንድ» የውርስ መብታችን የተጠበቀ ስለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን ይገባል። የዘመኑ የሥነ አእምሮ ምሁራን ሁለት የማስተማሪያ «በሮች» እንዳሉ ይናገሩሉ። አንዱ «የጆሮ በር» ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ «የዓይን በር» ነው። ታዲያ ይህን የማስተማር ጥበብ እግዚአብሔር ቀደም ሲል የገለጸልን መሆኑን የምናውቀው ስንቶቻችን እንሆን?

የእግዚአብሔር ቃል ራሱ «ጆሮህን አዘንብል»፥ «ከዓይንህ አታርቃት» ሲል መመሪያ አልለጠንም? ስለዚህ እንደ ዘመናዊው አባባል እኛም ለእግዚአብሔር ቃል «የጆሮ በራችንን» እና «የዓይን በራችንን» ክፍት ልናደርግለት ይገባል።

አራተኛው መመሪያ «በልብህም ውስጥ ጠብቃት» የሚለው ሲሆን በተለይ ልባችንን የሚያመለክት ነው። በጆሮ የምንለማውና በዓይናችን የምናየውን ለማገናዘብ ልባችንን ልናዘጋጀው ወይም ክፍት ልናደርገው ይገባል። «በልብህም ውስጥ ጠብቃት» በሚለው ጥቅስ አማካይነት የተሰጠንን ትዕዛዝ ለመፈጸም በመድኃኒትነት የቀረበልንን መመሪያ መቀበል ግድ ነው። ስለዚህም መመሪያ ወሳኝነት በመጽሐፈ ምሳሌ 4:23 ላይ እንደሚከተለው ተገልጸ እናገኛ ለን፦

«እጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።»

ይህ ጥቅስ በሌላ አባባል፥ ልባችን ማናቸውንም የሕይወታችንን አቅጣጫ ይቆጣጠራል እንደ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ እስከተቀበልን ድረስ ማለትም በጆሮና በዓይናችን በር በትክክል እንዲገባ እስከፈቀድንለትና ልባችንንም በመክፈት እስካስገዛንለት ድረስ፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደገባልን ሁሉ ለነፍሳችንም ለሥጋችንም መድኃኒትና ፈውስ ይሆናል። ምናልባትም ይህን ግልጽና ቁርጥ ያለ መደምደሚያ የሚጠራጠሩ ቢኖሩ፥ ከሚከተለው በግል ከደረሰብኝ ታሪክ ተጨማሪ መጽናኛ ያገኛሉ ብዬ አምናለሁ።

በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በእንግሊዝ ጦር ኃይል ሥር ለማገልገል በለሜን አፍሪካ ተመድቤ ነበር። በዚያም ወቅት ነበር ማናቸውም የሕክምና አርዳታ ሊያድነው ያልቻለ የቆዳ መሳላጥና የደም ሥር መታወክ ሕመም ያደረብኝ። በዚህም ከመማረሬ የተነሣ ከሆስፒታሉ በመሰናበት ከወጣሁ በኋላ ከአንድ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደርሼ ነበር። ይኸውም በምንም ዓይነት መልኩ ዳግመኛ የሐኪሞችን አርዳታ ላለመጠየቅ ሲሆን፥ በዚያ ምትክ ግን በመጽሐፈ ምሳሌ 4:20-22 ላይ እንደ ሰፈረው የፈውስ እምነቴን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ አደርጋለሁ፥ በየዕለቱ ለሦስት ጊዜ በአንዲት ብቸኛ ክፍል ውስጥ ወደ አምላኬ ክልብ የመነጨ ጸሎት አቀርባለሁ፥ እንደዚሁም በተሰጠን የተሰፋ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ለሥጋዬ መድኃኒት በመሆን እንዲፈውሰኝ ያላቋረጠ ልመናዬን አቀርባለሁ የሚል ነበር።

ከሕመሜ ሥቃይ በተጨማሪ፥ በዚያን ወቅት የነበረው የምግብ ሁኔታ፥ የአየሩ ጠባይና የተፋፋመው ጦርነት ፍጹም ለላምን የሚነሣ ነበር። ብዙዎች ጤናማ ለዎች እንኳን በያለበት እንደ ዝንብ መርገፍ የጀመሩበት ወቅት እንደ ነበረ ይታወሰኛል። ያም ሆና ግን አምላኬን አዘውትሬ በመገናኘ ቴና እንደተስፋውም ቃል ምሕረቱን እንዲልክልኝ በመነገዘዜ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሕመሜ ሁሉ በተአምር ዳንኩኝ።

እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባኝ ነገር፥ ይህን ታሪክ ማስተላለፌ የሐኪሞችን አገልግሎት ለማንቋሸሽ ወይም አላስፈላጊነት ለማሳየት አንዳልሆነ ነው። በተጨማሪም ደግሞ እኔው ራሴ በጦሩ የሕክምና ክፍል ውስጥ ተመድቤ እሠራ እንደነበረም ለእንባቢዎቼ ማስታወስ ይገባኛል። ሆኖም ግን አንድ የደረስኩበት ማጠቃለያ ሐሳብ አለ፥ ይኸውም የሕክምና ሳይንስ እርዳታ እስከተወሰነ ደረጃ እንጂ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ያህል ፍጹም የሆነ የመፈወስ ኃይል እንደሌለው ነው።

ይህ የእኔ ምስክርነት ሲሆን፥ ከሌላም አብያተ ክርስቲያናት አባላት የደረሱኝ ተመሳሳይ ታሪኮች አሉ። ለምሳሌ አንዲት የፐሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባል ሌት ወይዘሮ እግዚአብሔር ስለ አደረገላቸው ተአምራዊ ፈውስ በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ሲመሰክሩ ሰምቻለሁ። የሚገርመው ደግሞ እኚህ ሌት ወይዘሮ በምሳሌ 4:20-22 ላይ የተመሠረተ የምስክርነት ቃላቸውን የሚያሰሙበት ወቅት፥ ከአድማጮቻቸው እንዲ የሆኑ ሌት ደግሞ ከመቅጽበት ጉሮሮአቸውን ከሚያለቃያቸው ነቀርሳ በሽታ እንደ ተሳቀቁ በዓይኔ ለማየት ችያለሁ። ይህን በመሰሰሉት ድንቅና ተአምራት በመገፋፋቴም ለአንድ ሳምንት ያህል «የእግዚአብሔር የመድኃኒት ብልቃጥ» በሚል ርዕስ ልዩ የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅቼ ነበር። በዚህ ትምህርትና ምክር በመረዳት ብዙ ለዎች ከህመማቸው ለመፈወስ እንደቻሉ በጻፉልኝ ደብዳቤዎች አረጋግጠውልኛል። ለምሳሌ ያህል አንዲት የራዲዮ መልእክት አድማጭ መልእክቱን ካደመጠች በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል መድኃኒት በመመሪያው መሠረት ለመውሰድ ወሰነች፥ ከሦስት ወራት በኋላም ለእኔ በፃፈችው ደብዳቤ በ25 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአስከፊ የቆዳ በሽታ መፈወሷን ነግራኛለች።

እነሆ ከዚህ ልምድ በመነሳት አሁንም ቢሆን የሚከተሉት የመዝሙር 107:20 ቃላት እየተፈጸሙ ናቸው ለማለት በቅቻለሁ፦ *«ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፥ ከጥፋታቸውም አዳናቸው»*

እንደዚሁም ይህን የእግዚአብሔርን ቃል የማዳን ኃይል እንደኔ ያዩና የመሰከሩ ከርስቲያኖች ሁሉ፥ ከርስቶስ ለኒቆዲሞስ የተናገራቸውን ቃላት በሙሉ ልባቸው ደግመው ሊናገሩዋቸው ይችላሉ። *«እውነት እውነት ለልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለንና ያየነውንም እንመሰክራለን ...» ዮሐንስ 3:11።*

በተመሳሳይ ሁኔታም ከተያዘበት ሕመም ለመፈወስ የሚሹ በመዝሙር 34:8 ላይ ዳዊት እግዚአብሔርን እንደለመነው ሁሉ እነርሱም ሲማጸኑት ይችላሉ። *«እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም፤ በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው።»*

እስቲ አንተም ይህን የእግዚአብሔርን ቃል አዳኝነት በራስህ ላይ ሞክረው! እንዴት እንዴትም እንደሚሠራ እይ! እንደ ምድራዊ መድኃኒቶች የእግዚአብሔር መድኃኒት ለክንፈር አይኮመጥጥም፥ አይጎመዝዝም፥ አይመርም! ወይም ደግሞ እንደ ዘመኑ ስቃይ ማስታገሻዎች የታመመውን የአካል ክፍል በማደንዘዝ በሌላው የሰውነታችን ብልት ላይ ያልታሰበ ጦስ አያስከትልም። የእግዚአብሔር ቃል ከዚህ ሁሉ የጸዳና የነጻ፥ ዘላለማዊነትም ያለው ፍቱን መድኃኒት ነው። እግዚአብሔር እንደሚያዘው ቃሉን አስከ ተቀበልነው ድረስ ለሥጋችንም ለነፍሳችንም በጎነት ያስገኛል።

አእምሮአዊ አብርሖት

የእግዚአብሔር ቃል በአእምሮአችን ሊሰለጥን ልዩ ሰውጥ ለማስገኘት ይችላል። ይህም በመዝሙር 119:130 ላይ እንደሚከተለው ተገልጾአል።
«የቃልህ ፍቺ ያበራል፦ ሕጻናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»

በዚህ መዝሙር ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል በአእምሮአችን ላይ ሁለት ለውጦች እንደሚያስከትል ተጠቁሟል። ይኸውም «ያበራል» እና «አስተዋዮች ያደርጋል» ዘሚሉት ቃላት አማካይነት ነው።

በአሁኑ ዘመን ከማናቸውም ነገር ይልቅ የሰው ልጅ የሚሽቀዳደመው የጊዜውን ከፍተኛ ዕውቀት ማካበት ነው። ሆኖም ግን ይህን ዓይነቱ ምድራዊ ዕውቀት የአእምሮ አብርሆትን ወይም አስተዋይነትን የሚያተርፍ አይደለም። ደግሞም በተለይ ብርሃንን የሚተካ አንዳችም ነገር እንደሌለ በማንም ዘንድ የታወቀ ነው።

እንደዚሁ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል በተስተካከለ መልኩ አንዳችም ምድራዊ ዕውቀት በአእምሮአችን ላይ ለውጥ ሊያስገኝ ወይም ምትክ ሊሆን አይችልም።

እርግጥ ምድራዊ ዕውቀት ጠቀሜታ የለውም ለማለት አንችልም። ታዲያ ይህ ሐቅ እንዳለ ሆኖ አንድ የማይዘነጋ ታላቅ ነጥብ ግን ይህን መሰሉ ዕውቀት በሁለት መንገዶች ጠቀሜታ ላይ ሊውል የመቻሉ ጉዳይ ነው። የዘመኑ ዕውቀት በሰላ ቢላዋ ሊመሰል ይችላል። ታዲያ ቢላዋ ደግሞ ሁለት ዓይነት አገልግሎቶች ሊኖሩት ይችላል። በአንድ በኩል ምግብ በማዘጋጀት ረገድ ጠቀሜታ ሊኖረው በሌላ በኩል ደግሞ በዚያው ቢላዋ አንዱ ሰው ሌላውን ሊያርደውና ሊገድሰው ይችላል።

የእግዚአብሔር ምራት እስካልታከለበት ድረስ፥ ዘመናዊው ዕውቀትም እንዲሁ የጥፋት መሣሪያ ሊሆን ይችላል። በዓለማችን ላይ በተነሡት አስከፊ ጦርነቶች ላይ በሰው እጅ የተሠሩቱ አውዳሚ መሣሪያዎች ምን ያህል ክፋትና ጥፋት እንዳደረሱ የታወቀ ነው። አሁንም ቢሆን በዓለም ላይ በማንገርበብ ላይ ያለው የኒውክሊየር ጦርነት መጫርና የሰው ልጅ ከምድረ ገጽ መጥፋት ነው።

በሌላ በኩል ግን የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጅ በተፈጥሮ አእምሮው በመመራመር ሊደርስ የማይችልበትን ልዩና ከፍተኛ መገለጥ ሊያስገኝለት ይችላል። በቅድሚያ የፈጣሪውንና የአዳኙን የእግዚአብሔርን እውነታ ለማወቅ ሊያስችለው፥ በተጨማሪም የተፈጠረበትን ዓላማ፥ የተፈጥሮውን ውስጣዊ ባሕርያት የተፈጠሩበትን ዓላማና የመጨረሻውን ግብ ለመረዳት ያስችለዋል። ይህንንም አስካወቀ ድረስ ሰሕይወት የሚኖረው ትርጉምና አመለካከት የተለየ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ግንዛቤው፥ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ዕቅድ እንደሚመራና ያንንም ዕቅድ ለማሟላት ስላለው ድርሻ፥ ድርሻውንም በማሟላቱ ስለሚያገኘው ሽልማት ግልጽ መረዳት ይኖረዋል። የእግዚአብሔር ቃል በሰው ልጅ አካል ላይ የሚያመጣውን ተጨባጭ ሰውጥ ያህል በአእምሮውም ላይ ያስገኛል። ለምሳሌ እኔ ትምህርቴን የተከታተልኩት በዓለም ውስጥ ዝነኛ ከተባሉት ዩኒቨርስቲዎች አንዱ በሆነው በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ነው። ለከፍተኛ ዲግሪዬም በተለይ የተከታተልኩት የፍልስፍና ትምህርት ሲሆን፥ ይህም የጥንቱንም ሆነ የዘመኑን ፈላስፎች ትምህርት ያጠቃለለ ነበር። ታዲያ በዚሁ መስክ ብቻ ከሰባት ዓመታት በላይ ባሳልፍም ስለሕይወት ምንነት አሳማኝ የሆነ ትርጉም ለመገብየት አልቻልኩም ነበር። ላይ ላዩን ለሚያየኝ እንደ ጎበዝ ተማሪ ልቆጠር እንጂ ውስጣዊ ሁኔታዬ ግን የተራቆተ ነበር። ከዚህም የተነሳ ነበር እንደ መጨረሻ አማራጭ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የጀመርኩት። የማገርመው ታዲያ ብሉይ ኪዳንን ጨርሼ አዲስ ኪዳንን ማንበብ ሳልጀምር ነበር የእግዚአብሔር ቃል በአእምሮዬ ሊሰርጽና፥ የደህንነትን ብርሃን ለማየት የቻልኩት። በዚያን ጊዜም ያሰፈው ኃጢአቴ ሁሉ ይቅር እንደሚባልልኝ ብቻ ሳይሆን፥ ውስጣዊ ሰላምንና ዘላለማዊ ሕይወትን እንደተቀዳጀሁ ሙሉ እምነት አደረብኝ። በዩኒቨርስቲ ባሳሰፍኳቸው ዓመታት ስፈልገው የነበረውን የሕይወት ምሥጢር በጥቂት ወራት ውስጥ አገኘሁት።

በበኩሌ ዘዚህ ምዕራፍ አማካይነት ለማስተላለፍ የሞከርኩትን ትምህርት በሚቀጥለው በዕብራውያን 4:12 ጥቅስ መዝጋቱ ተገቢ መስሎ ይታየኛል።
«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም (ኃይል)፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል።»

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ይህ ገለጻ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሚስማማ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የማይዳሰሰው አንዳችም የሕይወት መልክ የለም። ወደ መንፈሳችንና ነፍሳችን ወይም ወደ ልብና አእምሮአችን ጠልቆ ከመግባትም አልፎ ግዙፋን የአካላችንን ክፍል ሁሉ ይዳስሳል፥ ጡንቻዎቻችንንና ጅማቶቻችንንም ሁሉ ይቆጣጠራል።

እንግዲህ በአጠቃላይ እስካሁን በቅደም ተከተል በቀረቡት ምዕራፎች እንዳየነው በልባችን አርሻ ውስጥ እንደ ዘር የተተከለው የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ እምነትን፣ ቀጥሎም የዘለዓለም ሕይወትን፣ ከዚያም ለአዲሱ ሕይወታችን ምግብን፣ ለአካላችን ፈውስን፣ ለአእምሮአችንም ብሩህነትንና መረዳትን እንደሚሰጥ ግልጽ ነው ማለት ነው።

6

የእግዚአብሔር ቃል ድል አድራጊነት ድል በኃጢአት ላይ

ከብሉይ ኪዳን አባቶች መካከል ማንም ከዳዊት አኩል ስለእግዚአብሔር ሥልጣንና ኃይል መረዳት ነበረው ለማለት አይቻልም። ስለዚህ በሌሎቹም ትምህርታችን አዘውትረን ከመዝሙሮች ውስጥ እንደ መጥቀሳችን ሁሉ አሁንም በኃጢአትና በሰይጣን ላይ ስለሚኖረን ድል በማስመልከት ዳዊት የተናገረውን እንጠቅሳለን።

«አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።» *መዝሙር 119:11* «ሰወርሁ» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ የሚያመለክተው ሃብትን ወይም ንብረትን እንደማካበት ወይም ማከማቸት ነው። ዳዊትም እንደዚያ በማለቱ ቃሉን ደብቋል ወይም በውስጡ እንዳይንጸባረቅ አምቆ ይዞታል ማለት አይደለም። በዚህ ምትክ ግን ለዚያ ልዩ ፍቅርና አክብሮት ላለው ለእግዚአብሔር ቃል ማከማቻ እንዲሆን በማንም የማይበከል የጸዳ ሥፍራ በውስጡ ማዘጋጀቱን ለማመልከት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል አምነው ስለሚቀበሉት ምን ያህል ኃይልና መመከቻ ጋሻ እንደሚሆናቸው አሁንም ዳዊት እንደሚከተለው ይገልጸዋል፦

«የሰውን ሥራ እፈ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው፤ ስለከንፈሮችህ ቃል ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠበቅሁ።»

ዳዊት «የሰውን ሥራ» ሲል ማናቸውንም ሰብዓዊ ግንኙነቶች በማውገዝ ደረጃ አይደለም ክእነዚህ ግንኙነቶች መካከል አንዳንዶቹ ጤናማና ገንቢ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ ይችላሉ። የተቀሩት ደግሞ ወደ ጭንቀትና ውድቀት የሚያመሩ በሰይጣን የተጠነሰሱ ሲሆኑ ይችላሉ። እንግዲህ አዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ባለውና ወደ መንፈሳዊ ውድቀት በሚያመራው ሥራ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት ማወቅ ይቻላል? የሚለው ነው። ለዚህ መልስ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መመዘኛ ወይም መፈተኛ አድርጎ በማቅረብ ነው የሚል ይሆናል።

ለምሳሌ የሚከተሉት ጥያቄዎች አዘውትረው የሚነሱ ናቸው፡- ለአንድ ክርስቲያን መደነስ ይፈቀድለታልን? ሲጋራ ማጨስስ? ቁማር መጫወት? የተከለከለው ለምንድን ነው? ... ወዘተ። ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ለእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ወይም ማህበረሰብ መተው የለበትም። መቼም ሆነ በየትኛውም ሥፍራ ቢሆን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር መገምገም አለባቸው።

ለምሳሌ በአንድ ወቅት ከአፍሪካ የመጡ ልጃገረድ ተማሪዎች መደነስ የተፈቀደ ስለ መሆን አለመሆኑ ጥያቄ አቅርበውልኝ ነበር። እኔም ከግል አስተሳሰቤና አመለካከቴ በመነሳት ልመልስላቸው ወይም የትምህርን ዕድል የሰጣቸውን ሚሲዮናዊ ድርጅት የሥነ ሥርዓት ደንብ በመጥቀስ መሆን ያለበትን ልገልጽላቸው አልሞከርኩም። በዚያ ምትክ ግን ያደረኩት ነገር መጽሐፍ ቅዱሱን በማውጣት 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡31 እንዲያነቡት መጋበዝ ነው። *«እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።»* በመቀጠልም ቆላስይስ 3፡17ን እንዲያነቡት አደረግኩኝ፡- *«እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።»* ከእነዚህም ሁለት ጥቅሶች በመነሳት ማንኛውም ክርስቲያን ሊመራባቸው የሚገባው ሥነ ምግባሮች የሚከተሉት መሆኑን አብራራሁላቸው።

አንደኛ ማንኛውም የምንሰራውን ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመሥራት ለእግዚአብሔር ምስጋና ልናቀርብበት የምንችል መሆን ይኖርበታል። እንግዲህ በአጭሩ ልንሰራው የምንችለው ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያስገኝና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እስክ ሆነ ድረስ ተቀባይነት የሚያተርፍልን ይሆናል። እኔም ለእነዚያ ልጃገረዶች የሰጠኋቸው መልስ ይህን የሚመስል ነበር። በዳንስ ምሽቱ ላይ በመገኘታቸው እግዚአብሔርን የሚያከብሩትና፥ በመደነሳቸውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመሰግኑት እስከሆነ ድረስ በዕቅዳቸው እንዲገፋበት፥ ይህ ካልሆነ ግን እንዲቀሩ መክርኳቸው።

እንደ መንፈሳዊ አባትነቴ ለእነዚያ ወጣቶች ትክክለኛ መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት ሲኖርብኝ፥ መመሪያውን ተግባራዊ ማደርጉ ግን የአያንዳንዳቸው ምርጫና ውሳኔ ነበር።

እንደዚሁ ሁሉ ስለምንበላውም ሆነ ስለምንጠጣው፥ ሲጋራ ስለማጨስ አለማጨሳችን ለመወሰን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መንተራስ አለብን። ለውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደመሆኑ በንጽሕና ልንጠብቀው ይገባል። ኮርስቲያን ሰንሆን ከሰይጣን ‘ባት ተላቀን በክርስቶስ ደም ስለታጠብንና ስለ ነጻን ራሳችንን በቅድስና መጠበቅ አለብን። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡16-17 መልእክቱ ላይ እንደሚከተለው ያስገነዘበን፡- *«የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ይህም እናንተ ናችሁ።»* እንደገናም በዚሁ መልእክቱ ምዕራፍ 6፡19-20 ላይ እንደሚከተለው ተናግሯል፡- *«ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ሰራሳችሁ ለይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።»*

አውንም ክዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3-4 ላይ የሚክተለውን ጽፏል፡- *«ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ክዝሙት እንድትርቁ፥ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት እይደለም እንጂ...»*

እነዚህን በመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክሮች በመመራት ለዘመናት ብዙ ክርስቲያኖች ትንባሆ ክማጤስ ተቆጥበዋል። በዚህም ጥንቃቄአቸው የተነሳ በማያምኑት ዘንድ እንደ ኋላቀርና ወግ አጥባቂ ሲታዩ ነበር። ሆኖም ግን ዘመናዊው የህክምና ሳይንስ እንዳረጋገጠው፥ ሲጋራ ማጨስ ለቀሳፊው የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንደሚያጋልጥ ነው። በአጭሩ ሲጋራ አለማጤስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን ሳይንሳዊም ነው ማለት ነው። በገንዘብ በኩል ለከፍተኛ ኪሳራ ክመዳረጉም በላይ ለሥቃይ ሞት ስለሚያበቃ በዚህ ዓይነቱ ሱስ አለመጠመድ ጥንቁቅነትና ማስተዋል እንጂ ወግ አጥባቂነትና ኋላቀርነት አይደለም። እንግዲህ የሲጋራ ሱስ እንዲስፋፋ የሚጥሩ ድርጅቶች፥ በተሰያዩ የማግባቢያና የመሰቢያ ማስታወቂያዎች ብዙ ብር የሚያፈሱ የትንባሆ አምራች ድርጅቶች በሌሎች ሥቃይና ሞት ለመክበር የሚሹ፥ በተዘዋዋሪ መንገድ «ነፍስ ገዳዮች» ናቸው ማለት ነው።

ይህን የሰጋራ ኩባንያዎች ወንጀል፥ ከጥቂት ዘመናት በፊት በባሪያ ሽያጭ ይተዳደሩ ክነበሩት አውሮፓውያን ወንጀል ጋር ሳወዳድረው በበኩሌ የበለጠ ክባድ አድርጌ አቆጥረዋለሁ።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ሌላው አደገኛ ሱስ በመጠጥ መጠመድ ነው። ዛሬ ብዙዎች የመኪና አደጋዎች፤ እንዲሁም የአካልና የአዕምሮ በሽታዎች የሚከሰቱት መጠጥን ያለመጠን በሚጠጡ ሰዎች አማካይነት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። በዚህም በኩል ቢሆን አውነተኞቹ ክርስቲያኖች በአልኮል ሱስ ላለመጠመድና ራሳቸውን ለተለያዩ የርኩሰት ተግባራት ላለማጋለጥ ብርቱ ጥንቃቄ አድርገዋል፤ አሁንም ያደርጋሉ። አዲሱና «ዘመናዊው መቅሰፍት» ኤድስ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በመላው ዓለም ላይ መጥቷል። በጋብቻ የጸኑና ክርኩሰት ራሳቸውን ያራቁ ክርስቲያኖች ራሳቸውንና ልጆቻቸውን ከዚህ አስከፊ በሽታ ጠብቀዋል። በሌላ በኩል፤ «አማራጭ የሕይወት ዘዬ» ተብሎ የሚፈከርለት ግብረ ሰዶም አማራጭ የሞት ዘዬ እንደሆነ ተረጋግጧል። ክርስቲያኖች ግን ከነዚህ ርኩሰቶች ራሳቸውን ያርቃሉ። ለዚህም ዋናው መመሪያቸው በመጽሐፍ ቅዱስ እንደታዘዘው ሰውነታቸውን የተቀደሰ አድርገው ለመጠበቅ ካላቸው ቆራጥነት የተነሳ ነው። በዚህ በአሁኑ ፈታኝና ቀውጢ ወቅት ይህንን መሰሉን ብርታት በመላበሳቸው፤ አምላካቸውን ልክ እንደ ዳዊት ሁሉ ሊያመሰግኑትና የሚከተሉትንም የዳዊት የጽናት ቃላት ሊያስተጋቡ ይገባል፡- *«የሰውን ሥራ እሬ እንዳይናገር ፈታዴ ነው፤ ሰለ ከንፈሮችህ ቃል፣ ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠበቅሁ።»* መዝሙር 17:4።

ድል በሰይጣን ላይ

የእግዚአብሔር ቃል ከላይ እንደተገለጸው በኃጢአት ላይ ድልን የሚያቀዳጅ ብቻ ሳይሆን ሰይጣንንም ለማሸነፍ ብቸኛው የጦር መሣሪያችንም ነው። ስለዚህም ነው ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ 6:17 ላይ የሚከተለውን ያለፈረው፡- *«የመንፈስን ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።»* በመሆኑም ለአንድ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል ጠላቶቹን ድል ለማድረግ ሌላ መተማመኛ የለውም። በዚሁ በኤፌሶን ምዕራፍ 6 ውስጥ የተጠቀሱትን ሌሎችም የክርስቲያኑ የጦር መሣሪያዎች፤ ማለትም የወገብ መታጠቂያው፤ የጽድቅ ጥሩሩ፤ የእግር መጫሚያው፤ የእምነት ጋሻው፤ ሁሉም ጠላትን ለመከላከል የምንጠቀምባቸው ናቸው። ብቸኛው የማጥቂያ መሣሪያችን ግን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የመንፈስ ሰይፍ ነው። ሆኖም ግን ክርስቲያን ይህን የእግዚአብሔር ቃል በሚገባ አስካልተረዳው ድረስ፤ በጦርነት ፍልሚያ ላይ በትክክል ሊጠቀምበት አይችልም። ለሰይጣንንና አጫፋሪዎቹን የጨለማ ኃይላት ለመዋጋት በግድ የእግዚአብሔርን ቃል መቀበልና መለማመድ ያሻል። ስለዚህም ነው በክርስትና ታሪክ ውስጥ ሁሉ እንደ ታየው ሰይጣን አዘውትሮ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ምንነት፤ ሥልጣኑና ኃይሉን እንዳይረዱና እንዳይለማመዱት የተለያዩ መሰናክሎችና ጋሬጣዎች የሚዘረጋባቸው።

በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ሰይጣንን ድል በማድረግና፤ በማሳደድ ረገድ ታላቅ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰምሳሌ በሉቃስ 4:1-13 እንደምንመለከተው ሰይጣን ክርስቶስን በሦስት መንገዶች ተፈታትኖት ነበር። ሆኖም ግን ኢየሱስ ድል ያደረገው ወይም የተዋጋው መንፈሳዊ ሰይፍ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ነው። ክርስቶስ አያንዳንዱን ፈተና ለመቋቋም የተጠቀመባቸው ቃላት በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ናቸው። ይህንንም በማስረገጥ አያንዳንዶቹን ጥቅሶች «ተብሎ ተጽፏል» በሚሉት ቃላት ደምድሟቸዋል።

ሉቃስ ግልጽ እንደሚያደርግልን ሰይጣን ክርስቶስን ለመፈታተን የአቀራረብ ዘዴዎቹን ይቀያይር ነበር። ያም ሆኖ ግን ውጤቱ ሽንፈት ነበር። ሰምሳሌ በሉቃስ 4:1 ላይ የሚከተለውን እናነባለን፡-

«ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፤ በመንፈስም ወደምድረ በዳ ተመርቶ፤ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ።»

ሆኖም ግን ከዚህ ፈተና በኋላ በሉቃስ 4:14 ላይ፡- *«ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤»* የሚል እናነኛለን።

ክርስቶስ በሰይጣን ከመፈተኑ በፊት «መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት» ነበር። ሆኖም ግን በእግዚአብሔር የታቀደለትን አገልግሎት ለመጀመር አስቀድሞ ሰይጣንን ድል ሊያደርገውና «በመንፈስ ኃይል» ሊመራ ያሻው ነበር። እዚህ ላይ ሁለት የአገላለጽ ልዩነቶችን እናጤናለን፡- ይኸውም በ«መንፈስ ቅዱስ መሞላት» እና «በመንፈስ ኃይል» ማገልገል መካከል ያለው ነው። ኢየሱስ ሁለተኛውን ኃይል ሊቀዳጅ የተቻለው ለሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተንተራሰ መልስ በመስጠት ድል ካረገው በኋላ ነው።

ይህን ትምህርት ዛሬም ቢሆን ክርስቲያኖች ከልብ ሊያጤኑት ይገባል። ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ቢሞሉም ቅሉ፤ ዳሩ ግን በመንፈስ በመመራት «በመንፈስ ኃይል» አግዚአብሔርን ሊያገለግሉት አይታይም። ለዚህም ምክንያቱ የክርስቶስን ፈለግ ለመከተል ባለመቻላቸው ነው። ሰይጣንን ለማሸነፍ በቃሉ ሰይፍ ለለማይጠቀሙ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላታቸውን ዕድል ተግባራዊ ሳያደርጉትና እግዚአብሔርን ለማገልገል ሳይጠቀሙበት ይቀራሉ።

የክርስቲያኑ የማጥቂያ መሣሪያ የመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ ብቻ ነው። ደግሞም በገሃድ እንደሚረጋገጠው አንድ ወታደር ያለ ጦር መሣሪያው በቀላሉ በጠላት ሊጠቃ ይችላል። ለክርስቲያኑም ቢሆን እንደዚሁ ነው። ከዚህ ውጭ ያለ ማናቸውም መንፈሳዊ መከላከያ ወይም ልምምድ በእግዚአብሔር ቃል የመጠቀምን ልምድ ሊተካው አይችልም። የጥንታ ቤተክርስቲያን አባቶች የቱንም ያህል በትምህርታቸው ያልገፉ ቢሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል በመከተልና ከጠላቶቻቸው ጋር በመንፈሳዊ ሰይፍ በመዋጋታቸው ድልን ለመቀዳጀት በቅተዋል። ሰምሳሌ ሐዋርያው ዮሐንስ ዕድሜው አጅግ በገፋበት ወቅት ለወጣት ክርስቲያኖች መመሪያ እንዳሆን የሚከተለውን ጥብቅ

ማስገንዘቢያ በ1ኛ መልእክቱ 2:14 አማካይነት እንዲደርሳቸው አድርጓል፦ *«ጎበዞች ሆይ፥ ብርቱዎች ስለሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፋውንም ስለአሸነፋችሁ አጽፍላችኋለሁ።»*

ዮሐንስ ስለእነዚህ ጎበዛዝት ሦስት ግልጽ ባህርያት አስፍሮልናል። የመጀመሪያው ብርቱዎች መሆናቸውን የሚመለከት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በእነርሱ ውስጥ ስለመኖሩ ነው። በሦስተኛው ደረጃ የጠቀሰው ክፋውን (ሰይጣንን) ለማሸነፍ መቻላቸውን የሚገልጽ ነው። እንግዲህ እነዚህ ወጣት ክርስቲያኖች ሰይጣንን ድል ለመምታት የቻሉት፥ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣቸው በመኖሩ ባገኙት ሥልጣንና ኃይል አማካይነት ለመሆኑ የማያጠራጥር ነው። በሌላ አነጋገር መንፈሳዊ ጉልበታቸው ይኸው የእግዚአብሔር ቃል ነው ማለት ነው።

በዚህ አጋጣሚ ልናነሳው የሚገባው ጥያቄ ከአሁኑስ ዘመን ወጣት ክርስቲያኖች መካከል ስንቶች ይህን የመሰለ ኃይል ተጎናጽፈዋል? የሚለውን ነው። መልሱም አሳዛኝ በሆነ መልኩ፥ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ይሆናል። ለዚህም ምክንያቱ በአጭሩ ለዚህ ውጤት የሚያበቃውን ኃይል ባለመቀበላቸው ነው። በመሆኑም በሚያሳዝን የታሪክ ምዕራፍ ላይ መገኘታችን የሚያጠራጥር አይደለም። ለዚህ ደግሞ በጥፋተኝነት ተጠያቂዎቹ ወላጆቻቸው ነን። ወጣቶችን ከሕፃንነታቸው አንስቶ በእግዚአብሔር ሐልዎት ኮትኩተን በማሣደግ ምትክ፥ በንቀት ዓይን እናያቸዋለን። «የልጅ ነገር» በሚሉት ፈሊጥ በመመራት ዉሎ ነገሮችን ልናካፍላቸውም ሆነ በተለይም በእግዚአብሔር ቃላት አበልጽገን ልናላድጋቸው አንዳችም ጥረት አናደርግም። ይህንንም አስመልክቶ ለሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 11:10 ላይ *«ሕፃንነትና ጉብዝና ከንቱዎች ናቸውና ...»* በማለት ሮሮ ያሰማናል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እኛ ወላጆች ልጆቻችንም በተራቸው እንደ እኛ አዛውንት እንሚሆኑ በመረዳት ከወዲሁ በመንፈሳዊ ብቃቶች ተንከባክበን ልናላድጋቸውና ልናጎለምሳቸው ይገባል። እንዲሁም ሁለቱንም ጸታዎች በተመለከተ የማበላለጥ መንፈስ ሊኖረን አይገባም። የገዘነኛው ወንጌላዊ የዊሊያም ቡዝ ልጅ ካትረን ቡዝ በአንድ ወቅት «ነፍሥ ጸታ የላትም» በማለት ግንዛቤዋን አስፍራለች። በመሆኑም በክርስቲያኖች ዘንድ፥ ዕድሜንና ጸታን ምክንያት በማድረግ አንዳችም የማበላለጥ መንፈስ ሊንጸባረቅ አይገባም። የክርስትና እምነት ወሳኝ ባህርያት ኃጢአትን በመናዘዝ፥ በማያወላውል እምነት፥ በታዛዥነት፥ በመሥዋዕትነትና በፍቅር ይገለጻል። እነዚህ ነገሮች ለሉትም ሆነ ለወንድ አንድ ናቸው። በመሆኑም ለጸታና ለዕድሜ ልዩነት ምንም ክብደት አይሰጠውም።

እርግጥ ለዚህ መሰሉ ችግር በአንዳንዶች ዘንድ እንደ መፍትሔ ተደርጎ የሚቆጠረው ልጆችን ለኃይማኖት ትምህርት ወደ መንፈሳዊ ክሌጆች መላክ ነው። ሆኖም ግን እነዚህን መሰሎቹ ወላጆች መረዳት ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር፥ የአሁኑ ጊዜ መንፈሳዊ ክሌጆች ስሙን ብቻ ከመያዛቸው በስተቀር በአብዛኛው የሚያስተምሩት ስለ ዓለማዊ ጉዳዮች መሆኑን ነው። ስለዚህ መሰሉ ችግር ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስያስ 2:8 ላይ እንደሚክተለው አስጠንቅቆናል፦

«እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ለው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠንቀቁ።»

ይኸው ሐዋርያ፥ ጢሞቴዎስንም በሚከተለው መልኩ ያስጠነቅቀዋል፦ *«ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በውሸት ዕውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመጽ ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፥ የተሰጠህን እደራ (ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ማለት ነው) ጠብቅ፥ ይህ ዕውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለእምነት ስተዋልና።»* 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:20። ይህ ማስጠንቀቂያ ለአሁኑም ትውልድ የሚሠራ ነው። ለአንድ ወጣት በመንፈሳዊ ክሌጅ ውስጥ ትምህርት ተከታትሏል ማለት፥ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ተረድቶ ተግባራዊ ለማድረግ በቅቷል ማለት አይደለም። እንደዚሁ ሁሉ የአንድ ለው ይህን መሰሉን ከፍተኛ ትምህረት መከታተል የአንድ ቤተክርስቲያን መጋቢን ለመተካትም ሆነ የሚጠበቅበትን መንፈሳዊ ግዴታዎች ሁሉ ለመወጣት ያስችለዋል ማለት አይደለም።

ከአዲስ ኪዳን እንደምንረዳው፥ ለመንፈሳዊ ትምህርቶች ማለለራጫ እምብርቱ የበጎበረተሰቡ ውስጥ የሚገኘው ቤተክርስቲያን ነው። በመሆኑም ይህን ድርጅት በምንም መንገድ ቢሆን በሌላ ተቋማት ሊተካ አይችልም። ደግሞም ሐዋርያት አባቶቻችን ቤተክርስቲያንን ለዚህ ደረጃ ያበቁት በዚሁ መንገድ በመመራታቸው ነው። ስለዚህ ለአሁኑ ትውልድ የሚያስፈልገው እጅግ የተራቀቀ ትምህርት ሳይሆን፥ መሠረታዊ የማድረጊያው ዘዴ ነው።

በዚህ መንገድ ስንመራ ብቻ ነው የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ልናጠነክራት፥ የመስቀልን ድል አድራጊነት ልናበሥርና፥ የጌታን ትእዛዛት ለማሟላት የምንችለው። ይህን እስካደረግን ድረስ፥ በሚከተለው መልኩ በራእይ 12:11 የተገለጸችውን ዓይነት ድል አድራጊዋን ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ችለናል ማለት ነው።
«እነርሱም (ክርስቲያኖች) ከበጉ ደም የተነሳ ስምስክራቸውም ቃል የተነሳ (ሰይጣንን) ድል ነሱት።»

በዚህ ውስጥ ለድል አስፈላጊ የሆኑ ሦስት መሰረታዊ ነገሮች እናያለን፦ ደም፥ ቃል፥ ምስክርነት። ደሙ፥ ክርስቶስ ለእኛ ሊል በመስቀል ላይ የተቀበለውን ሞትና ከዚህም የተነሳ የተቀዳጀውን ሥልጣንና ኃይል ያመለክታል። ቃሉ ደግሞ፥ ክርስቶስ ደሙን በማፍሰስ እኛን የዋጀን ስለመሆኑ ለመረዳት ያስችለናል። እንደዚሁም ለቃሉ መመስከራችን ደግሞ ክርስቶስ በመስቀሉ በሰይጣን ላይ የተቀዳጀውን ዓይነት ድል እኛም በሰይጣን ላይ እንደሚኖረን ያረጋግጥልናል።

ስለዚህ በሰይጣን ላይ ስለምናገኘውም ድል አንስተን በምንጋገርበት ሰዓት የርዕሳችን ማዕከል አሁንም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉን በትክክል ካልተረዳን የክርስቶስን ደም የማዳን ኃይል ለማወቅ አንችልም። የምንሰጠውም ምስክርነት ፋይዳ ቢስ ይሆናል። ይህን መመሪያ የማትከተል ቤተክርስቲያን ደግሞ፥ በነቢዩ ሆሴዕ ዘመን ስለነበረችው እስራኤል እግዚአብሔር እንደሚከተለው የተናገረው ወቀሣ አርሷንም የሚመለከት ይሆናል፦

«ሕዝቤ ዕውቀት ስለጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል፤ አንተም ዕውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ...» ሆሴዕ 4:6 የእግዚአብሔርን ቃል የማትቀበል ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀች ትሆናለች፥ በቀንደኛ ው ጠላቷ በሰይጣንም እጅ ትጠፋለች።

7

የእግዚአብሔር ቃል የማንጻት ኃይል

ከኃጢአት መንጻት

የእግዚአብሔር ሐል ከማያጎናጽፋቸው ታላላቅ ውጤቶች መካከል መንጻትና ቅድስና ይገኙበታል። ይህን በማብራራት ረገድ በቁልፍ ጥቅስነት የማያገለግለን፥ ኤፌሶን 5:25-27 ነው። *«ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ... በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሰዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።»*

ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ልናጤናቸው የሚገቡ አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦች አሉ። በቅድሚያ በመንጻትና በቅድስና መካከል ያለውን የቅርብ ዝምድና የምንመለከት ሲሆን፥ አንደዚሁም ሁለቱ የቱንም ያህል የተያያዙ ቢሆንም ዳሩ ግን ልዩነት እንዳላቸው ነው።

ይህንንም በሚከተለው መልኩ ለማስፈር እንሞክራለን። የተቀደሰው የግድ የነፃ ሊሆን አስፈላጊ ሲሆንም ስለ ነጻ ግን አስቀድሞ ተቀድሷል ማለት አይደለም። በመሆኑም የቅድስና እንዱ አካል መንጻት ቢሆንም ቅሉ፥ ዳሩ ግን ቅድስና ከዚያም የሚያልፍ ነው ማለት ነው።

ወደ ኤፌሶን ምዕራፍ 5 እንደገና ስንመለስ ሌላም ልናጤነው የሚገባ ፍሬ ነገር እናገኛለን። ይኸውም «...እንጽቶ እንዲቀድሳት፡» የሚለውን ሲሆን በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ቤተክርስቲያንም ሆነች እያንዳንዱም ክርስቲያን መቤዠትን ቢያገኝም ድኅንነትን ሙሉ በሙሉ ለመቀዳጀት ግን መንጻትና መቀደስ እንደሚያሻው ነው። ጳውሎስ ግልጽ እንዳደረገልን ቤተክርስቲያን የክርስቶስ እጮኛ ለመሆን የሚያስችላትን ብቃት ለመቀዳጀት የምትችለውን... «እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር...» ስትሆን ነው።

እንደዚሁም ከዚህ ጥቅስ ውስጥ የምናገኘው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ፥ «በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር...» የሚለው ሲሆን፥ ይህም የሚያመለክተው ለንጽሕናም ሆነ ለቅድስና ወሳኙ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለመቤዠት ሞትን ከመቀበሉም በፊት ቢሆን፥ ለደቀመዛሙርቱ ያረጋገጠላቸው ነገር የእርሱን ቃል በማዳመጥና በመከተል የነጹ እንደሚሆኑ ነው። ለዚህም ዮሐንስ 15፡3ን እንመልከት፡-
«እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ።»

በዚህ አጋጣሚ ግልጽ እንዲሆንልን የሚያሻው ለመንጻት ሁለት ኅን ለኅን የሚሄዱ ኃይሎች እንደሚያስፈልጉን ነው። እነርሱም፡- በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደምና፥ በቃሉ ውኃ መታጠብ ናቸው። ክርስቶስ በደሙ በመቤዠትና በቃሉ በማጠብ፥ ንጹሕና ቅዱስ አድርጎናል።

እነዚህን ሁለት ወሳኝ ነጥቦች ዮሐንስ በሚከተለው መልኩ ከክርስቶስ ጋር አዛምዷቸዋል፡- *«ብውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በውኃና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ ኢይደሰምኅ» 1ኛ ዮሐንስ 5፡6።*

በዚህ መልእክቱ ዮሐንስ ግልጽ ያደረገልን የክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት በታላቅ መምህርነቱ የተወሰነ ብቻ ሳይሆን ብቸኛው አዳኝ መሆኑንም ጭምር ነው። ለእነዚህ ለሁለቱም የክርስቶስ ተግባራት ምስክሩ መንፈስ ቅዱስ እንደመሆኑ ለቃሉና ለደሙ እውነትነት፥ ሥልጣንና ኃይል መስክሯል። በመሆኑም መምህርነቱ ክአዳኝነቱ፥ አዳኝነቱ ከመምህርነቱ ተለይቶ ሊታይ አይችልም።

ከኃጢአታችን የሚያነጻንና የሚዋጀንን የደሙን ኃይል ሳንለማመድ ዝም ብለን የክርስቶስን ትምህርት መቀበሉ በቂ አይደለም። በሌላ መልኩ ደግሞ የተዋጀነው በክርስቶስ ደም መሆኑን የሚያውጁ ሁሉ ዘወትር በቃሉ ለመታጠብ ራሳቸውን መስጠት አለባቸው። ከክርስቶስ ደምና ከቃሉ የማንጻት ኃይል ጋር ተነጻጻሪ የሆኑ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችን እናገኛለን። ለምሳሌ በዘጸአት 30፡17-21 ላይ የደም መሥዋዕት ከሚቀርብበት የነሐስ መሠዊያ ጎን ለጎን ንጹሕ ውኃ የያዘ የመታጠቢያ ሣህን እንደሚገኝ ክመገለጹም በላይ ጠቀሜታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውን ከናስ ሥራ፤ በመገናኛው ድንኳንና በመሠዊያው መካከል አርሰህ አድርገህ ውኃውን ትጨምርበታለህ። አሮንና ልጆቹም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ይታጠቡበታል። ወደ መገናኛው ድንኳን በገቡ ጊዜ፥ ለእግዚአብሔርም የእሳት መሥዋዕት ያቃጥሉ ዘንድ ወደ መሠዊያው ሊያገለግሉ በቀረቡ ጊዜ፥ እንዳይሞቱ ይታጠቡበታል። እንዲይሞቱም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ይታጠቡ፤ ይህም ሰእርሱ ከእርሱም በኋላ ሰዘሩ የዘላለም ሥርዓት ይሆንላቸዋል።»

ይህን ነለጸ ከአዲስ ኪዳን ጋር ስናዛምደው የነሐሱ መሠዊያ የክርስቶስን ደም በመስቀል ላይ መፍሰስ ሲወክል፥ በሳህኑ ውስጥ የሚገኘው የመታጠቢያ ውኃ ደግሞ የክርስቶስን ቃል መንፈስን የማንጻት ሥልጣን ያሳያል። ሁለቱም ለነፍሳችን ዘላለማዊ ደህንነት የሚያስፈልጉ ናቸው። በዚህ ዕድል ያለማቋረጥ መጠቀም ሊኖርብን ይህን እስካላደረግን ድረስ፥ በሁለቱ የአሮን ዓመጻኛ ልጆች ላይ የደረሰው ፍርድ በእኛም ላይ ይወርዳል።

ቅድስና

ስለ መንጻት በመጠኑም ቢሆን ከተነጋገርን፥ በመቀጠል ደግሞ ወደ ሁለተኛው ደረጃ ማለትም ወደ ቅድስና እንሸጋገር። ቅድስና የሚለው ቃል የአንድን ሰው ቅዱስ ወይም ብጹዕ መሆን የሚያመለክት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምንረዳው ለቅድስና አምስት ወሳኝ ነገሮች መሟላት አለባቸው። እነርሱም፡- አንደኛ የእግዚአብሔር መንፈስ፥ ሁለተኛ የእግዚአብሔር ቃል፥ ሦስተኛ መሥዋዕት ማቅረቢያ፥ አራተኛ የክርስቶስ ደምና አምስተኛ እምነት ናቸው።

እነዚህ ወሳኝ ነጥቦች በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ መቅረባቸውን በመቀጠል እንመለከታለን።

በመንፈስ ቅዱስ በኩል ስለሚገኘው ቅድስና ጳውሎስና ጴጥሮስ ሁለቱም ጽፈውበታል። ለምሳሌ ጳውሎስ በሁለተኛው ተሰሎንቄ መልእክቱ ምዕራፍ 2፡13 ላይ የሚከተለውን ይነግረናል።
«...ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አሰብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና።»

በመቀጠል ደግሞ ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ 1፡2 ላይ እንደሚከተለው ይላል፡- *«እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት...»* እንግዲህ ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምንመለከተው ጳውሎስና

ጴጥሮስ «ቅድስና ከመንፈስ ቅዱስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ በኩል» እንደሚገኝ ማመልከታቸውን ነው።

ይህንንም ክርስቶስ ራሱ ለአባቱ ባደረገው ጸሎት አማካይነት አረጋግጦልናል፡- *«በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው»* ዮሐንስ 17፡17። እዚህ ላይ የምንመለከተው ነገር ቅድስና በእግዚአብሔር አማካይነትም እንደሚገኝ ነው። በመሠዊያው አማካይነት የሚገኘውንም ቅድስና በማቴዎስ 23፡19 ስለ ፈሪሳውያን ሲናገር እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- *«እናንተ ደንቆሮዎች፤ እውሮች ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን? ወይንስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው?»* እዚህ ላይ ክርስቶስ የሚናገረው ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ስለተሰጠው ትምህርት ነው። ለእግዚአብሔር የቀረበው መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ በመቀመጡ ብቻ የተቀደሰና የተለየ እንደሚሆን ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ እንምናየው የስጦታውና የመሠዊያው ባሕርይ የተለየ ቢሆንም መሠረተ ሃሳቡ ግን ያልተሰወጠና ስጦታውን የሚቀድሰው መሠዊያው ነው የሚል ነው።

በክርስቶስ ደም በኩል ስለሚገኘው ቅድስና በዕብራውያን 10፡29 ላይ በግልጽ ሰፍሯል። በዚህም መልእክት ላይ የቀረበው ንጽጽር፤ አንድ የደህንነትን በረከቶች ስላወቀና ሆኖም ግን በአዳኙ ለማመን ስላልፈለገ ሰው ሆኖ፤ ስለእንደዚህ ዓይነቱ ሰውም እንዲህ ብሎ ይጠይቃል። *«የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ፤ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስሰኛል?»*

ይህ ጥቅስ በግልጽ የሚያመለክተው በእምነቱ የጸና ሰው፤ እንደምን በአዲሱ የቃል ኪዳን ደም መፍሰስ በማመን በክርስቶስ ደህንነትን እንደሚላበስ ነው። አሁንም በሐዋርያት ሥራ 26፡18 ላይ ጳውሎስ በክርስቶስ አንደበት ቅድስና በእምነት መሆኑ እንደ ተረጋገጠለት ይመሰክርልናል፡-
«በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ...» ይህ ጥቅስ በክርስቶስ ያለን እምነት ራሱ ሲቀድሰን እንደሚችል ይነግረናል። ከእነዚህ የተለያዩ ጥቅሶች በመነሳት ከአምስት የድምዳሜ ነጥቦች ላይ እንደርሳለን። ይኸውም በአዲስ ኪዳን ቅድስና የሚገኘው፤ በመንፈስ ቅዱስ፤ በእግዚአብሔር ቃል እውነት፤ በመስዋዕቱ መሠዊያ፤ በክርስቶስ ደምና በክርስቶስ በማመን መሆኑን እንረዳለን።

ይህን አባባል በመጠኑም ቢሆን እንደሚከተለው እናብራራዋለን፡- በቅድሚያ ቅድስና የሚመነጨው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም በተመረጠው ሰው አእምሮ ውስጥ ይህን ስሜት በእግዚአብሔር ቃል በኩል እንዲቀረጽ ያደርጋል በዚህም መንፈስ የተመራው ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር በመለየት ኃጢአቱን በመናዘዝ የቀድሞ ክፋቱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል።

በዚያም ሳቢያ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም ያነጻውና ብሎም ለቅድስና ያዘጋጀዋል። ሆኖም ግን ከላይ የተዘረዘሩት እራቱ የቅድስና መሠረቶች መንፈስ ቅዱስ ቃሉ መሠዊያውና ደሙ በእያንዳንዱ አማኝ ተግባራቸውን የሚወጡት በአምስተኛው ላይ ተመሥርተው ነው። እርሱም እምነት ነው። በቅድስና ሂደት ውስጥ የጸጋውን ሥራ የሚያስተገበርበትን የእምነት ሕግ አያስለውጥም።

እንግዲህ ለዚህ ሁሉ ማሠሪያው እምነት ነው ማለት ነው። ይህንንም በማጠናከር ማቴዎስ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡- *«ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ ለለው።»* ማቴዎስ 8፡13። የእግዚአብሔር ቃል በዚህ የቅድስና ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ሦስት ዋና ዋና ሚናዎች ይጫወታል፡-
አንደኛ፡- በቅድሚያ ቅድስና አሉታዊና አወንታዊ ገጽታዎች አንዳሉት ልንረዳ ይገባል። አሉታዊ ጎኑ ራሳችንን ንጹሕ ካልሆነና አንደ ኃጢአት ከሚቆጠር ማናቸውም ተግዘር በማግለል መልኩ የሚገለጽ ነው። አወንታዊ ገጽታው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅድስና ለመጋራት በመብቃታችን የሚታይ ነው።

ብዙውን ጊዜ ስብከቶች በሚደመጡበት ወቅት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የምናገኘው ለቅድስና አሉታዊ ጎኖች ነው። ብዙ ክርስቲያኖችም የሚማረኩት «ይህንን አታድርግ» በሚለው ትዕዛዝ ላይ እንጂ «አድርግ» በሚለው የእግዚአብሔር፤ ቃል አይደለም። ለምሳሌ በኤፌሶን 5፡18 ላይ ከሰፈሩት መመሪያዎች በይበልጥ የምንማረከው «መንፈስ ይሙላባችሁ» በሚለው አወንታዊ ትዕዛዝ ሳይሆን፤ «በወይን ጠጅ እትሰከሩ» በሚለው አሉታዊ ትዕዛዝ ነው። ይህ አንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት የሚኖረንን ሚዛናዊ አተራረብ እንደ ማፋለስ የሚቆጠር ነው።

ብዕዕና ወይም ቅድስና ማለት ግን ከክፋት ተግባራት መራቅ ብቻ ላይሆን ከዚያም በላይ የሚጠይቀው መሥዋዕትነት እስ። ለምሳሌ በዕብራውያን 12፡10 ላይ እግዚአብሔር፤ «.... *ለቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል»* ተብሎ ተገልጾልናል። እንዲሁም ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ 1፡15-16 ላይ እንደሚከተለው ያሳስበናል፡-
«ዳሩ ግን፡- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።» ከዚህ የምንረዳው ቅድስና የእግዚአብሔር የማይለወጥና ዘላለማዊ ባሕርይ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት ከዓለም ከተወገደም በኋላ በቅድስና ይኖራል። እኛም በእግዚአብሔር ልጅነታችን ልንካፈለው የሚገባው ይህንን የእግዚአብሔር የቅድስና ባሕርይ ነው። ስለዚህ ሽንጢአት መሸሽ ወደ ቅድስና የሚያመራ መንገድ እንጂ በራሱ ቅድስና አይደለም።

ስለ ቅድስና አሉታዊ ጎኖች ጳውሎስ በሚከተለው መልኩ አብራርቶልናል። «እንግዲህ፤ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች

አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» ሮሜ 12:1-2

በዚህ አስታዊ የቅድስና ሂደት ውስጥ ልናልፍባቸው የሚገቡ አራት ደረጃዎች አሉ።

አንደኛ፦ ስውነታችን ቅድስናን ያገኝ ዘንድ፥ በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ። የመሥዋዕት ማድረጊያ ዕቃ በላዩ ላይ ያለውን እንደሚቀድስ አይተናል።

ሁስተኛ፦ ይኸንን ዓለም አለመምሰል፥ ይህም ከክንቱነትና ከኃጢአት ራስን መለየት ነው።

ሦስተኛ፦ አእምሮአችንን በማደስ፥ አስተሳሰባችንን ሁሉ ከዓለማዊ ወደ መንፈሳዊ ነገሮች መለወጥ አለብን።

አራተኛ፦ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዕቅድ በግል ደረጃ መረዳት አለብን። አሮጌውን ሥጋችንን በመግደልና በአዲስ ሰብዕናና አስተሳሰብ በመተካት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ልንረዳና ስንፈጽመው ይገባናል። ሆኖም ግን አምንታዊ የሆነውን የቅድስና ገጽታ ለመቀዳጀት፥ ጳውሎስ በሮሜ 8:29 ላይ ባስፈረልን መመሪያ ልንጠቀም ያሻል፥ «ልጁ በብዙ ወንድሞቹ መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናል።»

እንግዲህ ስቅድስና የመጨረሻው ግባችን ክርስቶስን ስመምሰል መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ራሳችንን ከዓለማዊ ነገሮች ማግለልና እንደ ዓለማዊ ስዎች አለማሰብ የቅድስና አስታዊ ጎኑ ሲሆን፥ ክርስቶስን በመምሰል ራሱ እንዳደረገው ማድረግና እንደ ተናገረው መናገር፥ እንደ አሰበው ማሰብ ግን አወንታዊ ገጽታው ነው።

የቅድስና አስታዊ ገጽታ ለብቻው ዋጋ ቢስ ስለ መሆኑ ጳውሎስ በቆላስያስ 2:20-22 እንደሚከተለው ገልጾታል፦
«ለዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ እንደ ስው ሥርዓትና ትምህርት፦ አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዞት በዓለም እንደሚኖሩት ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በማድረግ ሲጠፉ ተወስነዋልና።»

ፍጹም ቅድስና በሰው ሠራሽ ሕጎች ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ቃል በመፈጸምና ክርስቶስን በመምሰል ላይ የተደገፈ ነው። ይህንንም ዓለታዊ ጎን ጴጥሮስ በሚከተሉት ውብ ቃላት አጠቃልሎአቸዋል፦

«የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ሰለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ዕውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች ቡተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተነበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።» 2ኛ ጴጥሮስ 1:2-4። ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ልናጤናቸው የሚገቡ ሦስት ነገሮች አሉ።

አንደኛ፦ እግዚአብሔር ስተቀደስ ሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ አሟልቶ የሰጠን መሆኑን መረዳት አለብን። ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱ አስቀድሞ ከሰጠን ውጪ ሌላ ነገር በተጨማሪ እንዲሰጠን ልንጠይቀው አይገባም፤ ማድረግ ያለብን እርሱ በመላት ላዘጋጀው ራሳችንን ማቅረብ ነው።

ሁስተኛ፦ ይህ የእግዚአብሔር ምሉዕ ስጦታ በቃሉ አማካይነት የሰጠን መሆኑን መረዳት አለብን። ከእኛም የሚጠበቀው በቃሉ የተሰጠንን ተስፋ ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው።

ሦስተኛ፦ ይህን የተስፋ ቃል ተግባራዊ የምናደርግበት መንገድ ሁለት ገጽታዎች ማለትም አለታዊና አዎንታዊ ጎኖች እንዳሉት መረዳት ያሻናል። ከማናቸውም ዓለማዊ ስግብግብነትና ርኩሰት ራሳችንን በማግለል የቅድስናን አለታዊ ጎን በቅድሚያ በማሟላት፥ በመቀጠል ደግሞ የእግዚአብሔርን የቅድስና ባሕርይ መጋራት ይኖርብናል። እንግዲህ እነዚህ ሁለቱም ጸጋዎች በቃሉ አማካይነት በቅድሚያ ተሟልተው የተሰጡን ስለ መሆኑ ማመን ይኖርብናል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደምናነበው ያዕቆብ ያየው ከምድር ወደ ስማይ የተዘረጋ መሰላል ተምሳሌትነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናገኘው የተስፋ ቃል አካል ነው። እኛም በእግዚአብሔር ቃል በመተማመን ደረጃውን በተሸጋገርን መጠን ወደ መንግሥተ ስማይ እንቀርባለን። ማለትም ከምድራዊ ባሕርያት በመላቀቅ የእግዚአብሔርን ጸጋ በበለጠ እየተላበስን እንሄዳለን።

ቅድስና የሚገኘው በእምነት ነው። እምነታችን ደግሞ ምንጊዜም ሕያውና እያደገ የሚሄድ መሆን አለበት። ስለዚህም ነው ኢየሱስ ወደ አባቱ፦ «ለእውነትህ ሁድሳቸው፥ ቃልህ እዉነት ነው» በማለት ስለ እኛ የጸለየልን። ዮሐንስ 17:17

8

የእግዚአብሔር ቃል ገላጭነት

ባለፉት ትምህርቶቻችን የእግዚአብሔር ቃል አስካመንንበት ተግባራዊ አስካደረግነው ድረስ፣ በውስጣችን የተለያዩ ውጤቶች እንደሚያስከትል ተመልክተናል።
እነኚህም ሰባት ውጤቶች የሚከሉት ናቸው፦

1. እምነት
2. አዲስ ልደት
3. የተሟላ መንፈሳዊ ምግብ
4. አካላዊ ፈውስና ጤናማነት
5. አእምሮአዊ አብርሆት
6. በጋጢአትና በሰይጣን ላይ ድል
7. ንጽህናና ቅድስና።

ከዚህ በተጫማሪም የእግዚአብሔር ቃል በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንደሚሠራ እንመለከታለን።

መስታወታችን ነው

ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ መንፈሳዊ መስታወታችን በመሆን የማገልገሉ ሐቅ ነው። ይህንንም በማስመልከት ያዕቆብ በመልዕክቱ 1:21-22 ላይ በቅድሚያ *«ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ... ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ»* በማለት ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል። ይህንን እስካላደረግን ድረስ ግን ራሳችንን በክንቱ እናታልላለን። ራሳችንን እንደ መጋቢና ካህን፣ እንደ ወንጌላዊና ደቀ መዝሙር ብንቆጥረውም ቅሉ ምንም ዓይነት ተግባራዊ በረከቶችንና ጥቅሞችን በሕይወታችን አንለማመድም። ይህንን እንዲህ በማለት ልናጠቃልለው እንችላለን፣ የእግዚአብሔር ቃል በተግባር የሚሠራው ቃሉን ተግባራዊ በሚያደርጉት ላይ ነው።

ያዕቆብ ቀደም ሲል ከሰጠን ማስጠንቀቂያ በማስከተል የሚከተለውን ገለጻ ያቀርብልናል። *«ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስታወት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፣ ወዲያውም እንደምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፣ በሥራው የተባረከ ይሆናል።»* ያዕቆብ 1:23-25።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል ከመስታወት ጋር እንዳነጻጸረው እንመለከታለን። ተፈጥሮአዊው ወይም ሰው ሠራሹ መስታወት ውጪያዊውንና ተሰዋዋጭ የሆነውን ፈራሹን አካላችንንና ገጻችንን ብቻ ሲያሳየን፣ የእግዚአብሔር ቃል መስታወት ግን ውስጣዊ ወይም መንፈሳዊ ማንነታችንን ያንጸባርቃል። ስለዚህም እጅግ ጠቃሚ አላብ እንድ ሰው በሚከተለው አባባል ተጠቅሟል። «ማስታወስ የሚኖርብን ታላቁ ቁም ነገር መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስም በተራው እኛን የሚያነበን (የሚመረምረን) መሆኑን ነው።»

እኔም ብሆን ያስፍክበትን ልምድ ላስታውሰው፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የጀመርኩት እንደ ፍልስፍና ተማሪነቴ በተጠራጣሪነትና በኢአማኒነት ነበር። ሰማንበብም የፈለግኩት በዓለም ውስጥ ካሉት የፍልስፍና ትምህርቶች እንደ አንዱ በማድረግ ነበር። ሆኖም እነዚያ የማንላብጣቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ቀስ በቀስ በውስጤ ለውጥ ማስከተላቸው አልቀረም ነበር። በመሆኑም ያ የምኩራራበት ምድራዊ አውቀቴ መፍረክረክ ጀመረ። በእርሱም በኩል ይስማኝ የነበረው ማን አህሎኝነትና ትምክህት ተቦረቦረ።

አንደ እውነቱ ከሆነ በራሴ ምርምር ብቃት ማንኛውንም የተሰወረ ምስጢር እደርስበታለሁ የሚል እምነት ነበረኝ። እንዲያውም የጥንት የግሪክ ፈላስፋ እንዳለው «ሰውሰም ነገር መለኪያው ሰው ነው» የሚለው አባባል የእኔም መርሆ ለመሆን በቅቶ ነበር። ሆኖም ግን አነዚያ እንደ ቀልድ

ልመለከት የምችላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ቀስ በቀስ ሕይወቴንም አስተሳሰቤንም ለወጡት። እኔም እንደ መጽሐፈ ዳንኤል ብልጣሶር «በሚዛን ተመዘንህ፥ ቀለህም ተገኘህ» የሚለው ጽሑፍ ከፊቴ ተሰቅሎ መቆየቱን እንደተረዳሁ፥ መንፈሳዊ ዕረፍት በማጣቴ መላው ትኩረቴን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ አደረግሁኝ። ለወትሮው ደስታ የሚያጎናጽፉኝ ዓለማዊ ዋዛና ፈዛዛዎች ሁሉ ከአጠገቤ ተወገዱ። ከእነዚህም ጉድፎች በእርግጥም መላቀቄን የተረዳሁት ራሴን መንፈሳዊ መስታወት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ስገመግመው ነበር።

ለብዙ ወራት ያህል ተስፋ በመቁረጥ በሐዘንና በብስጭት ባህር ውስጥ እንዳልዋኘሁ ያህል፥ በመጨረሻ ላይ በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ሕያውን የእግዚአብሔር ቃል፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ተገናኘሁት።

በልማዳዊው ሁኔታ ስው ወደ መስታወት የሚመለከተው ስለ አካላዊ ገጽታው ሁኔታ ለመረዳት ነው። የፊቱን መቆሸሽ፥ የጸጉሩን መንጨባረር፥ የጥርሱን መበላሸት ...ወዘተ በመሥታወቱ ነጸብራቅ ሊመለከትና ጎደለኝ የሚለውን ሁሉ ለማስተካከል ይችላል። አምን መጽሐፍ ቅዱስ የነፍሳችን መስታወት ነው። ይሁን እንጂ በሕይወታችን የሚያመጣው ለውጥ በአቀባበላችን ላይ የተወሰነ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል መስታወት መንፈሳዊ ጉድፈታችንን ወይም ጉስቁልናችንን ያሳየናል። ሆኖም ግን ያንን ዕድፍ ልናጠራው የምንችለው በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ከዘደላችን የሚያነጻን፥ መተላለፋችንንም ይቅር በማለት፥ ከመንፈሳዊ ደዌያችን የሚፈውሰን ታላቁ ሐኪማችን ክርስቶስ ብቻ ነው። በአፋጣኝ ተግባራዊ በሆነ መልኩ የቃሉ መስታወት የሚያሳየንን ጉድለታችንን ለማስወገድ ስንወሰን ይቅርታን፥ መንጻትን፥ ፈውስንና እግዚአብሔር ለእኛ ያቀዳቸውን ባርኮቱች ልንቀደጅ እንችላለን።

ሆኖም ግን ብዙ ሰዎች በዚህ ታላቅ ዕድል ሊጠቀሙበት አይታይም። አርግጥ ለጊዜውም ቢሆን ከሚንጸባረቀው መንፈሳዊ ምስላቸው አኳያ፥ ምን ያህል ኃጢአተኞችና በደለኞች መሆናቸውን ይረዱት ይሆናል። ከዚህም በመነሳት ሐዘንና ጸጸት ያድርባቸው ይሆናል። ወደ ቤተ ክርስቲያንም በመሔድ በእግዚአብሔር የመሥዋዕት መንበር ፊት ሊጸልዩ፥ ሊያስቅሱ፥ ብሎም ኃጢአተኛነታቸውን ሊናዘዙ ይችላሉ። ሆኖም ግን አብዛኛውን ጊዜ ክቤተ ክርስቲያኑ ከመውጣታቸው በፊት የቀድሞውን ስብእናቸውን ለመላበስ ጊዜ አይወስድባቸውም። የእግዚአብሔር ቃል እንደ መስታወት በመሆን ከሚያሳያቸው ድክመታቸው ሙሉ በሙሉ ለመንጻት ዕለት በዕለት ያላቋረጠ የንጽሕና እርምጃ በመውሰድ ምትክ፥ «ታጥቦ ጭቃ» እንደሚባለው ተመልሰው ይልከሰከላሉ።

ይህ ምንኛ የሚያሳዝን ሥዕል ነው። እንደ እውነቱ የእግዚአብሔር ቃል መስታወትነት የሚያመለክተን ኅስቁላውን ኅናችንን ብቻ ሳይሆን

መልካሙንና ብሩሁንም ጭምር ለመሆኑ ጥቂት በመታገስና መሥዋዕትነት በመክፈል ልናየው በተገባ ነበር። ክርስቶስን ባለ ማግኘታችን ገጻችን ደስ የማያሰኝ የሆነውን ያህል እርሱን በማግኘታችን ደግሞ ውብና ድንቅ እንደሚሆን ለመመስከርም በተገባን ነበር። በቆሸሸውና በተቀዳደው የኃጢአት ማቅ ምትክ፥ ብርሃን የተላበሰ የደህንነት ካባ መደረባችንን ልናውቅ በተገባ ነበር። በአጠቃላይም በእርጌው ለውነት ምትክ አዲስ ለው መሆናችንንም ልናምንበት ይገባ ነበር።

ለዚህ ብቃት የሚያደርሰን ብቸኛው ጎዳና ኃጢአተኛነታችንን መረዳት፥ ከልብ መጸጸትና ንስሐ መግባት ነው። በዚሁም ላይ በዕለት ከዕለት ኑሮአችን በእግዚአብሔር ቃል አስክ ተመራን፥ በመስታወቱ ውስጥ የምናየው ምስል አርጌው ለውነታችንን ሳይሆን፥ በክርስቶስ የተቀዳጀነው «አዲስ ለውነት» ነው። ይህም ታማኝ የሆነው መስታወት በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:17-18 ላይ የተገለጸውን ገሃድ ያደርግልናል፦ *«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አርጌው ነገር ሉልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከለጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው።»*

እንግዲህ የአርጌው ለውነታችንን በአዲስ ለውነት መተካት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነገር «ከእግዚአብሔር» ስለ መሆኑ እንረዳለን። በክርስቶስ አዲስ ለው የሚያደረገን እግዚአብሔር እንጂ አንዳችም የእኛ አስተዋጽኦ አይደለም። ጳውሎስ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 21 ላይ ሐሳቡን በማጠናከር እንደሚከተለው አስፍሯል። *«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።»*

እስተ፡ በክርስቶስ አማካይነት ስላገኘነው ለውጥ በዚህ አጋጣሚ እናጢን! በእኛ ኃጢአት የተነሳ ክርስቶስ ኃጢአት በመሆኑ በእግዚአብሔር ጽድቅ እኛም ጻድቃን ሆንን። የእግዚአብሔር ጽድቅ አንዳችም ነውርና እንከን የሌለበት፥ ከኃጢአት ፍጹም የጸዳ ነው። በመስታወቱም ውስጥ የምናየው ገጻችን እንደዚሁ የጠራ ነው።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ገለጻ በመኃልይ በለለሞን ምዕራፍ 4:7 ላይ እናገኛለን። ይኸውም ሙሽራው ክርስቶስ እጮኛው ለሆነችው ቤተክርስቲያን የሚናገረው ነው።
«ውዴ ሆይ፥ ሁለንተናሽ ውብ ነው። ነውርም የለብሽም።»

ከዚህ ቅኔያዊ ገለጻ የምንረዳው የጠራው መስታወት በክርስቶስ ያገኘ ነውን ፍጹም ጽድቅ እንደሚያላየን ነው።

በዚህ መስታወት ውስጥ ያለ መስልቸት በየጊዜው ራሳችንን ማየት እንደሚገባን ጳውሎስ በሚከተለው መልኩ ያጠናክረዋል፦ *«እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያብለጨለጭን*

መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ አንመሰል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን::» 2ኛ ቆሮንቶስ 3:18

ለማጠቃለል ጳውሎስም ሆነ ያዕቆብ ስለ እግዚአብሔር ቃል መስታወት ለእኛ ለአማኞች የሚያስገነዝቡን፥ መስታወቱ የሚያንጸባርቀው ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ በክርስቶስ የተወንደልንን ኃጢአተኞነታችንን ሳይሆን፥ በእምነት የምንጎናጸፈውን የእግዚአብሔር ክብር ነው:: ይህንንም ክብር ለማየት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሊያድርና በመስታወቱ ውስጥ ወደ ሚንጸባረቀው ምስል ሊሰውጠን ያሻል:: ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4:17-18 ላይ በድጋሚ የሚጠቅሰው ይህንኑ ሐሳብ በማጠናከር ነው:: *«የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው::»*

ዘላለማዊ ውጤት ከሚኖራቸው ነገሮች ላይ ዓይናችንን ልንነቅል አይገባም:: እነዚህንም ልናያቸው የምንችለው በመስታወቱ ውስጥ ስለሆነ ትኩረታችን ሁሉ ወደዚያ ሊሆን ይገባል:: ያን ጊዜ ብቻ ነው ማናቸውም ችግርና ድከመታችን ሁሉ ሊወገድ የሚችለው::

በዕብራውያን 11:27 ላይ ሙሴ ከግብጽ በመሸሽ ለአርባ ዓመታት ያህል በእረኝነት በምድረ በዳ እንዳሳለፈ እናነባለን:- *«የንጉሡን ቊጣ ሳይፈራ የግብፅን አገር የተወ በእምነት ነበር፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና::»*

እዚህ ላይ ሙሴ ያን የመሰለውን ችግር እንዴት ለመቋቋም ቻለ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ሆኖም መልሱ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁልጭ ብሎ የምናገኘው ነው:- *«የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና::»* ሙሴን ያበረታው በማይታየው በእግዚአብሔርና በአዳኙ ዘላለማዊ ድል አድራጊነት በመተማመኑ ነው:: እንግዲህ ለእኛም ቢሆን ይህ ዓይነቱ አምነት ከተመሳሳይ ጽናትና ቆራጥነት ላይ ሊያደርሰን ይችላል:: በመሆኑም እንደ መስታወት በሚታየው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ራሳችንን ዕለት በዕለት ልናየው ይገባል:: በዚህም በትክክል እስክ ተጠቀምንበት ድረስ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን ስለሚሠራ ፍሬያማና የተቀደሰ ሕይወት እንመራለን::

ፈራጃችን ነው

በመጨረሻም ላይ የእግዚአብሔር ቃል ዳኛችን ስለ መሆኑ ልናውቅ ይገባል:: በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተንጸባርቆ እንደምናገኘው የዳኝነት ሥልጣን ዘዘላለማዊው ብርሃን በእግዚአብሔር አጅ ያለ ነው:: ለምሳሌ በዘፍጥረት 18:25 ላይ አብርሃም እግዚአብሔርን፥ *«የምድር ሁሉ ፈራጅ ዘትን ፍርድ አይፈርድምን?»* ሲል እናገኘዋለን:: እንደዚሁም በመጽሐፈ መሳፍንት 11:27 ላይ ዮፍታሔ፥ *«ፈራጁ እግዚአብሔር ... ዛሬ ይፍረድ»* እንዳለ እንመለከታለን:: አሁንም በመዝሙር 58:11 ላይ *«በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ::»* የሚል ጥቅስ እናገኛለን:: በመጨረሻም በኢሳይያስ 33:22 *«እግዚአብሔር ፈራጃችን ነው»* ተብሎ በግልጽ እናያለን:: ወደ አዲስ ኪዳን ስንሸጋገር ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ዳኝነት ሙሉ የሆነውን መገለጥ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ በዮሐንስ 3:17 ላይ ክርስቶስ፥ *«ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና»* በማለት ስለ እግዚአብሔር የፍርድ ጠባይና መንገዶች ግልጽ አድርጎልናል:: እንደዚሁም በ2ኛ ጴጥሮስ 3:9 ላይ:-

«ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል::» ተብሏል::

እነዚህም ሆኑ ሌሎችም ተመሳሳይ ጥቅሶች የሚያመለክቱን እግዚአብሔር የምህረትና የደህንነት አምላክ እንደሆነና ብሎም ፍርዱን ለማምጣት እጅግ ታጋሽ እንደሆነ ነው:: ሆኖም ፍርዱ ያንም ያህል የዘገየ ቢሆንም በመጨረሻ ላይ ግን መምጣቱ የማይቀር ነው:: ዳኛው እግዚአብሔር አብ ለመሆኑ 1ኛ ጴጥሮስ 1:17 *«ለሰውም ፊት ሳያዳላ በአያንዳንዱ ላይ እንደሰራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ...»* በሚል መልኩ ተገልጿል:: ሆኖም ግን ይህን ፍርድ ተግባራዊ የሚያደርገው ልጁ ስለ መሆኑ ክርስቶስ ራሱ በዮሐንስ 5:22-23 ላይ እንደሚከተለው ይነግረናል:-

«ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ሰንኪ አይፈርድም::»

በመቀጠልም በቁጥር 26 እና 27 ላይ ክርስቶስ:- *«አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና:: የሰውም ልጅ ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው::»* ተብሏል::

አብ ፍርድን ከራሱ ወደ ልጁ ማሸጋገሩ ልጁም እንደ አርሱ አኩል እንዲከበር በመፈለጉ ነው:: እንደዚሁም ክርስቶስ የሰው ልጅ እንደመባሉ፥ የሰውን ደካማ ባህርያት ያውቃልና ፍርዱም በዚያው መጠን የሰመለ ይሆናል:: ሆኖም ግን ወልድም በተራው ፍርድን ለእግዚአብሔር ቃል እንዳስተላለፈ እንመለከታለን:: ስለዚሁም ዮሐንስ 12:47-48 ላይ:- *«ዓለምን ላድን እንጂ ዘዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል»* ብሎ ክርስቶስ እንደተናገረ እናያለን:: ይህ እንግዲህ አድልዎ የሌለበትና ማንኛውንም ሰው የሚመለከት ይሆናል:: በኢሳይያስ 66:2 ጌታ እንዲህ ይላል:- *«እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው፥ ይላል እግዚአብሔር ፤ ነገር ግን ወደ እዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ ዘቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ::»*

ሰው በእግዚአብሔር ቃል ፊት ለምን እንደሚንቀጠቀጥ በአዲስ ኪዳን መገለጥ ብርሃንነት መረዳት እንችላለን። የእግዚአብሔር ቃል (የመጽሐፍ ቅዱስ) ገጾች በምናነብበትና ትምህርቱን በምንሰማበት ወቅት ራሳችንን ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ቆመን እናገኘዋለን። በዚያም ሰተቀበሉት፥ ሰሰው ዘር ሁሉ ሰሰተመደበው መለኮታዊ ፍርድ ደረጃና መመሪያ ይገሰጥላቸዋል።

ሰሰዚህም ክርስቶስ በማቴዎስ 5:18 ላይ የሚከተለውን ብሏል፦ *«እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እሰኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እሰኪፈጸም ድረስ።»*

በመቀጠልም በዚሁ ምዕራፍ በማቴዎስ 24:35 ላይ፦ «ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም» ብሏል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ መጽሐፍ በሆነው ዮሐንስ ራእይ ላይ፥ የክርስቶስ ቃል ፍጻሜ ሊያገኝና ሰማይና ምድር በሚያልፍበት ሰዓት የእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን እንደሚዘረጋ የሚገልጥ ትንቢት እናነባለን።
«ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ሰፍራም አልተገኘላቸውም። መታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ አርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ መታንም በመጻሕፍት ተጽፎ አንደ ነበረ አንደ ሥራቸው መጠን ተከፈለ። ባሕርም በአርሱ ውስጥ ያሉትን መታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በአነርሱ ዘንድ ያሉትን መታን ሰጡ፥ አያንዳንዱም አንደ ሥራው መጠን ተከፈለ።» ዮሐንስ ራእይ 20:11-13።

በዚያን ጊዜ የሚፈርደው አንዱ ዳኛ ክርስቶስ እንደተናገረው ምንጊዜም የማይሰወጥና የማይሻረው የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል። ይህም በመዝሙር 119:160 ሰተናገረው ትንቢት ፍጻሜ ይሆናል፦
«የቃልህ መጀመሪያ አውነት ነው። የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ሰዘሳሰም ነው።»

ይህ እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር ቃል ፍጹምነትና፥ በጽድቅ ሰስ መፍረዱም ሰሁሉም ለው መለጠቱ የሚያረጋግጥልን እንደ መሆኑ፥ እኛም በዚሁ በምድራዊ ሕይወታችን እንደ ቃሉ በመኖር ሰጽድቅ እንጂ ሰክፋት እንዳንሠራ ያሰጠነቅቀናል። ጳውሎስም በተመሳሳይ መንገድ፥ *«ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር»* 1ኛ ቆሮንቶስ 11:31።

ራሳችንን መመርመር ማለት እያንዳንዱ የሕይወታችንን መስመር ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ማስተካከል ማለት ነው። ይህን እስካደረግን ድረስ ክርስቶስ በዮሐንስ 5:24 ላይ ቃል እንደ ገባልን ተፈጻሚ ይሆናል፦ *«እውነት አውነት አላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።»*

ይህን መሰል ሌላም የመተማመኛ ቃል በሮሜ 8:1 ላይ እናነኛለን።

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።» ከእግዚአብሔር ፍርድ ሰመዳን ምን ማድረግ አለብን? ቃሉን መስማት፥ በሕይወታችን የዋሆችና ሰንሰሐም የተዘጋጀን መሆን ይገባናል። ክርስቶስም የእኛን ፍዳና ኃጢአት እንደ ተሸከመ ማመን አለብን። ይህን እስካደረግን፥ ቃሉ ከዘላለማዊ ፍርድና ሥቃይ ሁሉ በማዳን ሰዘላለማዊ ሕይወት ያበቃናል።

ይህ ሁሉ የሚከናወነው በቃሉ አማካይነት ነው። ብንንቀውና ብንጦለው በመጨረሻው ቀን ቃሉ ይፈርድብናል። ብንቀበለውና ብንታዘዘው ግን ፍጹም የሆነ ይቅርታንና ሙሉ ደህንነትን በመስጠት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያጎናጽፈናል።